ሜፕል ሊፍ ፉድስ ኮርፖሬሽን
ብራንደን

ከ፡ ጃኒዋሪ 12፣ 2020
እስከ፡ ዲሴምበር 31፣ 2024

የፕሬዚዳንት መልዕክት

ውድ አባል፣

የዩኒየን የጋራ ስምምነት ልክ እንደ የመብቶች ቻርተር ነው። በስራዎ ላይ ያለዎትን መብቶች ይገልጻል፣ ያስጠብቃል፣ ያረጋግጣል። ሊከፈልዎት የሚገባዎትን ደመወዝ እና ሊያገኙት የሚገባዎትን ጥቅማ ጥቅሞች (ቤኔፊትስ) መጠን ይደነግጋል። በስራ ቦታ ላይ ያለዎትን የመከበር መብት በወረቀት ላይ ያሰፍራል።

ሊያገኙት የሚገባዎትን ደመወዝ፣ ጥቅማ ጥቅም (ቤኔፊትስ)፣ እንዲሁም መብቶችዎን ማወቅዎ አስፈላጊ ነው። እባክዎ ይህን ስምምነት ጊዜ ወስደው አንብበው ይጨርሱት። ጥያቄ ካለዎት በስራ ቦታዎ ያለ የመደብር አስተናባሪ (ሾፕ ስቱወርድ) ያናግሩ፤ ወይም ለቋሚ የዩኒየን ተወካይዎት ይደውሉ። በእዚህ ዶክመንት ላይ የተዘረዘሩት መብቶችዎ እና ጥቅማ ጥቅሞችዎ የተነፈጉዎት ከመሰልዎትም ስለ ጉዳዩ ማነጋገር የሚገባዎት እነዚህን ሰዎች ነው።

ከማክበር ሰላምታ ጋር፣

ጄፍ ትሬገር፣
ፕሬዚዳንት ዩ.ኤፍ.ሲ.ደብሊው. ሎካል 832

ሜፕል ሊፍ ፉድስ ኮርፖሬሽን

ማውጫ

	አንቀጽ	ገጽ
የቅሬታዎች አቀባበል	22	39
የቀድሞ (ሌጋሲ) ፈንዶች አመዳደብ ለብራንደን ሰራተኞች		53
አፔንዲክሶች፣ ሪፈራል	30	46
የሐዘን ክፍያ	19.08	37
የብራንደን ማበረታቻ (ኢንሴንቲቭ) ፕሮግራሞች	ሌተር #6	82
ቡሌቲን ቦርዶች	24	43
የዜግነት ጉዳይ ማስፈፀሚያ ፈቃድ (ሊቭ)	19.11	38
የፅዳት ጊዜ	5.12	10
የካምፓኒ እና ዩኒየን ትብብር-መደብር አስተናባሪዎች	25	43
ኮምፓሽኔት ሊቭ	19.10	38
ኮርፖሬት አሰልጣኝ	13.02	24
የዩኒየን ክፍያዎች ክፍያ	3	2
ዲሲፕሊን	21	38
የዶክተር ኖቶች	አፔንዲክስ A-4	54
የዶመስቲክ ቫዮለንስ እና የስቶከር ሊቭ	19.12	38
ኤርጎኖሚክስ	16.14	32
ኤክስፓይሬሽን እና እድሳት	34	48
የቤተሰብ ኃላፊነት ፈቃድ (ሊቭ)	19.09	38
የፌደራል ኢሚግሬሽን ሕግጋት	33.06	48
የመጀመርያ እርዳታ ጣቢያ	ሌተር #5	81
የውጭ ሃገር ሰራተኛ ፕሮግራም	33	47
የውጭ ሃገር ሰራተኛ መባረር	33.04	48
ጄነራል በዓላት	11	21
የቅሬታ ምርመራ	25.05	43
የጤና እና ደህንነት ኮሚቴ	16.02	29
የጤና እና ደህንነት ትብብር	16.13	32
ጤና እና ደህንነት	16	29
ጤና እና ደህንነት የጥርስ ህክምና ፕላን/ጡረታ ፕላን	አፔንዲክስ A	51
ጤና እና ደህንነት፣ ሪፈራል	20	38
የስራ ሰዓታት	5	3
የኢሚግሬሽን ፔፐርወርክ	33.01	47
ሐዘንን የሚመለከቱ መረጃዎች	22.02	39
በስራ ላይ የሚከሰት ጉዳት	12.02	23
የአስተናባሪ ማስተዋወቂያ	25.03	43
ስራ ቅየራ - አዲስ ስራ ማስተዋወቅ	አፔንዲክስ D-2	70
በአንድ ካታጎሪ ውስጥ የሚደረጉ የስራ ሮቴሽኖች	10	20
ጆይንት ኢምፕሎይመንት ፕሮጀክት	ሌተር #4	81
ጆይንት ሌበር ማኔጅመንት ኮሚቴ	32	47
የጁሪ ዲዩቲ ፈቃድ (ሊቭ)	19.06	36

ኪል ፍሎር የምግብ እና እረፍት ጊዜያት	ሌተር #7	82
ቢለዋ መሞረድ	16.11	31
ሌይኦፍ እና ከሌይኦፍ መመለስ	8	17
ሌይኦፍ ማስታወቂያ/ትርጉም	8.01	17
የሊድ ሃንድ ፕሪሚየም	13.01	23
የሊድ ሃንድ/የኮርፖሬት አሰልጣኝ፣ የማብቂያ ቀናት	26.03	44
ሊቭ ኦፍ አብሰንስ (ፈቃድ)	19	33
ሎከሮች	29	45
ጥገና እና የፓወርሃውስ ላይሰንስ እድሳቶች	አፔንዲክስ B-5	57
የጥገና ረዳትነት እና የአፕሬንቲስሺፕ ፕሮግራሞች	ሌተር #1	75
የጥገና ደመወዝ ሰርቬይ	አፔንዲክስ B-6	57
የሰምንቱ መጨረሻ የጥገና ፕሮግራሞች	አፔንዲክስ F	74
የማኔጅመንት መብቶች እና ስራዎች	15	28
የነፍሰ ጡርነት/የወላጅነት ፈቃድ (ሊቭ)	19.04	34
የምግብ እና የእረፍት ሰዓታት	5.10	7
MFCW የጥርስ ህክምና ፕላን	አፔንዲክስ A-2	52
MFCW ትምህርት እና ስልጠና ትረስት ፈንድ፣ ሪፈራል	28	45
MFCW ትምህርት እና ስልጠና ትረስት ፈንድ	አፔንዲክስ C	59
የድርድር ዩኒት ባህሪያት	1	1
ጥቃት እና መድልዎ አይኖርም	2.04	2
ኦፍ-ሺፍት ፕሪሚየም	13.03	24
ኦንላይን መለጠፊያ ፕሮሰስ	ሌተር #3	81
ኦሪየንቴሽን፣ አዲስ ተቀጣሪ	25.06	44
ኦቨርታይም	6	10
የፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች የስራ ሰዓታት	5.08	4
የክፍያ ጊዜ - ዳይሬክት ዲፖዚት	27	44
የፔይሮል ስህተቶች	27.02	45
የጡረታ ፕላን	አፔንዲክስ A-3	52
ግላዊ እረፍቶች	5.11	9
ግላዊ ፈቃድ (ከ1-4 ቀናት)	19.05	36
ፕሪሚየም ክፍያዎች	13	23
የፕሮቤሽን ወቅት	4	2
መከላከያ አልባሳት/በካምፓኒው የሚቀርቡ መሳሪያዎች	16.09	30
በየጊዜው ፕሮግራም የሚያዝለት ኦቨርታይም	6.05 2)	12
የማቃለያ ሬቶች	26	44
የዲሲፕሊን ሬፍረንሶች መወገድ	21.05	39
የኦቨርታይም መጠይቅ	6.05	11
መከባበር የሰፈነበት የስራ ቦታ አንቀጽ 31	ሌተር #2	80
መከባበር የሰፈነበት የስራ ቦታ	31	46
አደገኛ ስራን ያለመስራት መብት	16.07	30
የደህንነት ጫማዎች	16.12	31
ፕሮግራም የተያዘለት ኦቨርታይም	6.05 1)	11
ፕሮግራም የተያዘላቸው የአስራ ሁለት ሰዓታት ፈረቃዎች	አፔንዲክስ E	72
የስራ ፕሮግራም አወጣጥ እና አለጣጠፍ	5.09	4
የዳኛ አመራረጥ	23	41
ሲኒዮሪቲ	7	15

ሲኒዮሪቲ፣ ፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች	7.07	17
የመደብር አስተናባሪ እረፍት	19.01	33
አድማዎች እና ሎክአውቶች	17	33
የጊዜ መጠበቂያዎች	5.09(4)	6
የመሳሪያዎች ፈቃድ	16.10	31
የትሬድ አፕሬንቲስሺፕ ክፍፍሎች	አፔንዲክስ B-2	57
ትርጉም	33.02	47
UFCW አርማ ስቲከሮች	2.05	2
UFCW/ሜፕል ሊፍ ፉድስ ኮርፖሬሽን የጥቅማ ጥቅም ትረስት ፈንድ	አፔንዲክስ A-1	51
የዩኒየን ተወካይ የፋብሪካ ጉብኝቶች	18	33
የዩኒየን መደብር	2	1
ፕሮግራም ያልተያዘለት ኦቨርታይም - ከአንድ (1) ሰዓት የሚበልጥ	6.05 3)	12
ፕሮግራም ያልተያዘለት ኦቨርታይም - አንድ (1) ሰዓት ወይም ከዛ በታች	6.05 4)	13
ክፍት የስራ ቦታዎች/የክፍፍል ማስታወቂያዎች	9	18
ቫኬሽን ፕሮግራም አወጣጥ	14.08	26
ቫኬሽን፣ ጄነራል	14.17	28
ቫኬሽን፣ ፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች	14.14	27
ክፍያ የማይቋረጥባቸው ቫኬሽኖች	14	24
የደመወዝ ክፍፍል ካታጎሪዎች	አፔንዲክስ D	60
የደመወዝ ሬቶች	አፔንዲክስ B-1	55
ደመወዞች፣ ሪፈራል	12	23
ደመወዝ/ክፍፍል	አፔንዲክስ B	55
የምስክር ክፍያዎች	19.07	37
ስራ ፕሮግራሞች	5.09(5)	6

የሚያበቃበት ቀን፡ ዲሴምበር 31፣ 2024

ስምምነት አድራጊዎች፡

ሜፕል ሊፍ ፉድስ ኮርፖሬሽን፣
በማኒቶባ ክፍለ ሀገር ብራንደን ከተማ ውስጥ ቢዝነስ በማካሄድ ላይ ያለ አካለ ኮርፖሬሽን ነው። በእዚህ ስምምነት ውስጥ ከዚህ በኋላ "ካምፓኒው" እየተባለ ይጠራል።

እና፣

የተባበሩ ምግብ እና ንግድ ሰራተኞች ዩኒየን፣ ሎካል ቁጥር 832፣
በተባበሩ ምግብ እና ንግድ ሰራተኞች ኢንተርናሽናል ዩኒየን ቻርተር የሚደረግ ነው። በእዚህ ስምምነት ውስጥ ከዚህ በኋላ "ዩኒየኑ" እየተባለ ይጠራል።

ጉዳዩ፡ ካምፓኒው እና ዩኒየኑ ተባብረው በካምፓኒው እና ይህ ስምምነት በሚሸፍናቸው ተቀጣሪዎቹ መካከል የመስማማት መንፈስ የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን የመመስረት እና የመጠበቅ፣ በመካከላቸው የሚነሱ ግጭቶችን በፍትሃዊነት እና በስምምነት የማብረጃ መንገዶችን የማቅረብ፣ እና ቅልጥፍናን እና የተሻሉ አሰራሮችን የማበረታታት ፍላጎት አላቸው።

ስለሆነም ዩኒየኑና ካምፓኒው በጋራ እንደሚከተለው ተስማምተዋል፡

አንቀጽ 1 የድርድር ዩኒት ባህሪያት

1.01 ካምፓኒው ዩኒየኑን እንደ ብቸኛው የተቀጣሪዎች የጋራ ድርድር ተወካይ አድርጎ ለመቀበል ተስማምቷል። ተቀጣሪዎች ማለት በስራ ተቆጣጣሪነት እና ከዛ በሚበልጥ ማዕረግ ካሉት፣ ከደህንነት ሰራተኞች፣ ከቢሮና ከጥራት ቁጥጥር ሰዎች እና በ Act. ከተቀሩት በስተቀር ሁሉንም በማኒቶባ ክፍለ ሀገር ብራንደን ከተማ የሚገኘው ፋብሪካ ሰራተኞችን ያጠቃልላል።

አንቀጽ 2 የዩኒየን መደብር

2.01 ካምፓኒው በ**አንቀጽ** 1 በተቀመጠው መሰረት ግዴታቸውን የሚወጡትን የዩኒየን አባላት ብቻ በድርድር ዩኒት ውስጥ በተቀጣሪነት ለማስቀጠል ይስማማል። ካምፓኒው የዩኒየኑ አባላት ያልሆኑ አዲስ ተቀጣሪዎችን የመቅጠር ወይም የቀድሞ ሰራተኞችን መልሶ የመቅጠር ነፃነት ይኖረዋል። ይህም ተፈጻሚ የሚሆነው እነዚህ ሰራተኞች በፉል-ታይምም ሆነ በፓርት-ታይም ቢቀጠሩ ለዩኒየን አባልነት ብቁ መሆናቸው እና በዩኒየኑ ይፋዊ የአባልነት ማመልከቻ ቅጽ በመጠቀም በተቀጠሩ በአስር (10) ቀናት ውስጥ ለአባልነት ማመልከት እና በሠላሳ (30) ቀናት ውስጥም አባል መሆን የሚችሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

2.02 ካምፓኒው እያንዳንዱን አዲስም ሆነ በድጋሚ የተቀጠረ ሰራተኛ በሚቀጥርበት ጊዜ የዩኒየን ክፍያን እና የመግቢያ ክፍያን በተመለከተ ተቀጣሪው የሚኖሩትን ኃላፊነቶች የሚያትት የቅጽ ደብዳቤ ለተቀጣሪው ለማቅረብ ተስማምቷል።

2.03 ካምፓኒው አንድ ሰራተኛ ለመጀመርያ ጊዜም ሆነ በድጋሚ በተቀጠረ በአስር (10) ቀናት ውስጥ የተቀጣሪውን ጨርሶ የተሞላ የዩኒየን አባልነት ማመልከቻ ቅጽ ለዩኒየኑ **በኤሌክትሮኒክስ** ለመላክ ተስማምቷል። የአባልነት ማመልከቻ ቅጹ የማሳተሚያ ወጪ በዩኒየኑ የሚሸፈን ይሆናል። የጋራ ስምምነቱ ለሚጸናበት ጊዜያት በሙሉ የአባልነት ማመልከቻው ስራ ላይ ይውላል።

2.04 ማንኛውም ተቀጣሪ ህጋዊ የዩኒየን ስራዎችን በመስራቱ፣ ወይም ከስራ ሰዓታት ውጪ በዩኒየን ኮሚቴ ውስጥ አገልግሎቶችን በማበርከቱ፣ ወይም ማንኛውንም አይነት ይህን ስምምነት የሚጥስ ድርጊት ለዩኒየኑ ሪፖርት በማድረጉ ምክንያት ሊባረርም ሆነ መድልዎ ሊደርስበት አይገባም።

2.05 <u>UFCW አርማ ስቲከሮች</u>

ተቀጣሪዎች ከፈለጉ አንድ (1) የ UFCW አርማ ስቲከር የደህንነት ቆባቸው ላይ መለጠፍ ይፈቀድላቸዋል። እነዚህ ስቲከሮች የዩኒየኑን ስም እና አስፈላጊውን ሎካል ቁጥር ለመለየት ብቻ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ይሆናል። የእነዚህ ስቲከሮች ስፋት ከ 1.2 ኢንች በ 1.2 ኢንች ሊበልጥም ሆነ በካምፓኒው የሚሰጡ ወይም የሬጉሌሽን ሌብሎችን ሊሸፍን አይገባም። እነዚህ ስቲከሮች ልክ እንደ ማንኛውም የካምፓኒ ወይም የሬጉሌሽን ስቲከር ሁሉንም ደንቦችን ማሟላት ይኖርባቸዋል። ይህ በተፈጸመበትም ጊዜ ስቲከሩ በቦታው መለጠፉን እና በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆኑን ማረጋገጥ የተቀጣሪው ኃላፊነት ነው።

<u>አንቀጽ 3 የዩኒየን ክፍያዎች ክፍያ</u>

3.01 ካምፓኒው ከተቀጣሪው ደመወዝ ላይ የዩኒየን ክፍያዎችን እና የመግቢያ ክፍያዎችን በአባላቱ **ወይም በስራ አስፈጻሚ ቦርዱ** ከሁለቱ አማራጮች **እንደ አግባብነቱ** በአንዱ አማካኝነት ድምጽ ባገኘ መልኩ ለመቁረጥ ተስማምቷል። በተጨማሪም ካምፓኒው እነዚህን የዩኒየን ክፍያዎች አዲስ ወይም እንደገና ከሚቀጠሩ ሰራተኞች የመጀመርያ ደመወዝ ላይ ያለ ጥያቄ ለመቁረጥ ተስማምቷል። በማንኛውም ወር ተቀናሽ የሚደረጉ ገንዘቦች **በኤሌክትሮኒክስ አማካይነት በዳይሬክት ዲፖዚት** በካምፓኒው ለዩኒየኑ ዋና ገንዘብ ያዥ በሃያ (20) ቀናት ውስጥ የካምፓኒውን የአራት (4) ወይም አምስት (5) ሳምንታት የአካውንቲንግ ወቅት ማብቂያ ተከትሎ ሊላክ ይገባል። የሚላከውም የኮምፒውተር ኤሌክትሮኒክ ፋይል በመጠቀም በየወሩ ወይም በየአራት ሳምንቱ ክፍያው የተቆረጠባቸውን የተቀጣሪዎች ስም፣ የሶሻል ኢንሹራንስ ቁጥር እና የፋብሪካ ቁጥር ከእያንዳንዱ የክፍያ መጠን ጋር በማካተት ይሆናል።

<u>አንቀጽ 4 የፕሮቤሽን ወቅት</u>

4.01 አዲስ ተቀጣሪዎች ለፉል-ታይም ተቀጣሪነት ሃያ ሁለት (22)፣ ለፓርት-ታይም ተቀጣሪነት ደግሞ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ (980) ሰዓታትን በፕሮቤሽን ላይ መቆየት ይኖርባቸዋል። ካምፓኒው በፈለገበት ጊዜ ማንኛውንም በፕሮቤሽን ላይ ያለ ተቀጣሪ

ከላይ በተቀመጡት የጊዜ ገደቦች ውስጥ ማባረር ይችላል። የተባረረ ተቀጣሪም በእዚህ ስምምነት ላይ ያሉት የቅሬታ እና የዳኝነት አንቀጾች የተጠቃሚነት መብት አይኖረውም። ከላይ የተጠቀሰውን ተመርኩዘው ያልተጠቀሰውን የሚጨምሩ ድርጊቶች በካምፓኒው እና በዩኒየኑ የጋራ ስምምነት የሚፈጸሙ መሆን አለባቸው።

4.02 ፕሮቤሽን ላይ ያሉ ሁሉም ተቀጣሪዎች ስማቸው የተለጠፈበት ሰማያዊ ሄልሜት የፕሮቤሽን ጊዜያቸው እስኪያበቃ ድረስ እንዲለብሱ ይገደዳሉ።

<u>አንቀጽ 5 የስራ ሰዓታት</u>

5.01 መደበኛው የፉል-ታይም ተቀጣሪዎች የስራ ሳምንት አርባ (40) ሰዓታት ይሆናል። ይህም በማኔጅመንት ፕሮግራም በሚያዝላቸው አምስት (5) ተከታታይ የስምንት (8) ሰዓት ፈረቃዎች ወይም አራት (4) ተከታታይ የአስር (10) ሰዓታት ፈረቃዎች የሚሰራ ነው። የሆግ እጥረት ቢያጋጥም፣ ማሽኖች ቢበላሹ፣ ወረርሽኝ ቢመጣ፣ ከካምፓኒው ቁጥጥር ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች ቢከሰቱ፣ መሳሪያዎች ቦታ ቢቀያየር፣ ወይም የገበያው ሁኔታ ቢለዋወጥ የፉል-ታይም ተቀጣሪዎች በሳምንት ከአርባ (40) ላነሱ ሰዓታት ሊሰሩ እንደሚችሉ ካምፓኒው እና ዩኒየኑ ተስማምተዋል።

5.02 በአንቀጽ 5.10 ከተጠቀሱት የምግብ እና የእረፍት ሰዓታት በስተቀር የአንድ የፉል-ታይም ተቀጣሪ ፈረቃ ተከታትለው በሚመጡ የስራ ሰዓታት ይዋቀራል።

5.03 በስራ ሳምንት ውስጥ አምስት የስምንት ሰዓታት ፈረቃዎች ፕሮግራም የተያዘለት የፉል-ታይም ተቀጣሪ ከእነዛ የስራ ቀናት በአንዱ ጄነራል በዓል ቢያርፍ እና ፋብሪካው በእዛ ቀን ቢዘጋ ሰራተኛው በዚያ ሳምንት ለሠላሳ ሁለት (32) ሰዓታት የሚሰራ እና የአርባ (40) ሰዓታት ክፍያ የሚከፈለው ይሆናል። አንድ ጄነራል በዓል ከአንድ የፉል-ታይም ተቀጣሪ የስራ ፕሮግራም ውጪ ቢያርፍ ተቀጣሪው በዛ ሳምንት ለሰራባቸው ሰዓታት በሙሉ እና ለበዓሉ ተጨማሪ የስምንት (8) ሰዓታት ክፍያ ተደምሮ የሚከፈለው ይሆናል። ሁለት ጄነራል በዓላት በተመሳሳይ የካላንደር ሳምንት ቢያርፉ ከላይ የተቀመጠውን መንገድ የሚከተል የአከፋፈል ስርዓት ለሁለቱም በዓላት ተፈጻሚ ይሆናል።

5.04 በስራ ሳምንት ውስጥ አራት የአስር ሰዓታት ፈረቃዎች ፕሮግራም የተያዘለት የፉል-ታይም ተቀጣሪ ከእነዛ የስራ ቀናት በአንዱ ላይ ጄነራል በዓል ቢያርፍ እና ፋብሪካው በእዛ ቀን ቢዘጋ ሰራተኛው በዚያ ሳምንት ለሠላሳ (30) ሰዓታት የሚሰራ እና የአርባ (40) ሰዓታት ክፍያ የሚከፈለው ይሆናል። አንድ የፉል-ታይም ተቀጣሪ በሳምንት አራት የአስር ሰዓታት ፈረቃዎች ቢሰራ እና ጄነራል በዓሉ ከእነዛ የስራ ቀናት ውጪ በሆነ ቀን ቢያርፍ ለተቀጣሪው ተጨማሪ የስምንት (8) ሰዓታት ስራ ክፍያ ለጄነራል በዓሉ ከሰራባቸው ከሌሎቹ ሰዓታት ክፍያ በተጨማሪ የሚከፈለው ይሆናል። ሁለት ጄነራል በዓላት በተመሳሳይ የካላንደር ሳምንት ቢያርፉ ከላይ የተቀመጠውን መንገድ የሚከተል የአከፋፈል ስርዓት ለሁለቱም በዓላት ተፈጻሚ ይሆናል።

በስራ ሳምንት ውስጥ የአስራ ሁለት ሰዓታት ፈረቃዎች ፕሮግራም የተያዘለት የፉል-ታይም ተቀጣሪ ከእነዛ የስራ ቀናት በአንዱ ላይ ጄነራል በዓል ቢያርፍ እና ፋብሪካው በእዛ ቀን ቢዘጋ ሰራተኛው የስራ ሳምንቱ በአስራ ሁለት ሰዓታት የሚቀነስለት እና የአስራ ሁለት (12) ሰዓታት የጄነራል በዓል ክፍያ የሚከፈለው ይሆናል። አንድ የፉል-ታይም ተቀጣሪ የአስራ ሁለት ሰዓታት ፈረቃዎች የሚሰራ ከሆነ እና ጄነራል በዓሉ ከእነዛ የስራ ቀናት ውጪ በሆነ ቀን ቢያርፍ ያ ተቀጣሪ

ተጨማሪ የአስራ ሁለት (12) ሰዓታት ስራ ክፍያ ለጄነራል በዓሉ ከሰራባቸው ከሌሎቹ ሰዓታት ክፍያ በተጨማሪ የሚከፈለው ይሆናል። ሁለት ጄነራል በዓላት በተመሳሳይ የካላንደር ሳምንት ቢያርፉ ከላይ የተቀመጠውን መንገድ የሚከተል የአከፋፈል ስርዓት ለሁለቱም በዓላት ተፈጻሚ ይሆናል።

5.05 ሁሉም ተቀጣሪዎች ከአስቸኳይ ጊዜ ወይም በካምፓኒው እና ተቀጣሪቆቹ ስምምነት ካልሆነ በስተቀር ፕሮግራም በተያዘላቸው ፈረቃዎች መካከል ቢያንስ የአስራ ሁለት (12) ሰዓታት እረፍት ሊኖራቸው ይገባል። አስቸኳይ ጊዜ ማለት ምንኛውም ያልተጠበቀ የሰራተኞች መቅረት በህመም፣ ጉዳት፣ ማሽን ብልሽት፣ ወይም ከካምፓኒው ቁጥጥር በሆኑ ሁኔታዎች ሲመጣ ተብሎ ይተረጎማል።

5.06 ካምፓኒው ለተቀጣሪዎች በየሳምንቱ ሁለት (2) ወይም ሦስት (3) ተቀታታይ ቀናት እረፍት የሚሰጥ ይሆናል። ይህም ለስምንት ሰዓታት የአምስት ቀን ፈረቃ ወይም ለአስር ሰዓታት የአራት ቀን ፈረቃ እንደ አግባብነቱ የሚፈጸም ይሆናል። ይህ ደንብ ተቀጣሪው ተጨማሪ ፈረቃዎችን ለትርፍ ሰዓት ክፍያ ብሎ ለሚሰራበት ጊዜያት አያገለግልም።

5.07 ተቀጣሪዎች ለስምንት ሰዓታት የአምስት ቀን ፈረቃ ነው የሚሰሩት ወይስ ለአስር ሰዓታት የአራት ቀን ፈረቃ የሚለውን ቢያንስ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ወይም ልክ ቅጥር እንደተጀመረ ለፉል-ታይም ተቀጣሪዎች ሊያሳውቅ ካምፓኒው ተስማምቷል። የካምፓኒው ስራ እሁድ እና ቅዳሜን የሚያጠቃልል የሰባት ቀን የስራ ሳምንት ይሆናል። በሃያ አራት (24) ሰዓታት የስራ ቀን ውስጥ ሦስት (3) ፈረቃዎች የቀን ፈረቃ፣ የከሰዓት ፈረቃ፣ እና የማታ ፈረቃ ተብለው ይገኛሉ።

5.08 <u>የፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች የስራ ሰዓታት</u>

ካምፓኒው የስራ ኃይሉን እስከ ሃያ (20%) ፐርሰንት ድረስ እንደ ፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች ሊቀጥር ይችላል። የዚህ ፐርሰንት ስሌት በየአራት (4) የካላንደር ሳምንቱ የሚደረግ ሲሆን የሚመሰረተውም በእያንዳንዱ ሳምንት በድርድር ዩኒት ውስጥ በሚገኙት ተቀጣሪዎች ድምር ቁጥር ላይ ይሆናል። ይህ የፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች ፐርሰንት በማንኛውም ሳምንት ከሃያ (20%) ከበለጠ እንዲበልጥ ያደረጉት የፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች ብዛት ለሚያክሉት በአገልግሎት እድሜ ለሚበልጡት ክህሎት የሌላቸው የፓርት-ታይም ሰራተኞች ለሰሩባቸው ሰዓታት በሙሉ የፉል-ታይም ክህሎት የሌላቸው ሰራተኞች ክፍያ እንዲከፈላቸው ይደረጋል። (ማለትም ካምፓኒው በድርድር ዩኒት ውስጥ 1,000 ተቀጣሪዎች ቢኖሩት እና በአንድ ሳምንት 210 ተቀጣሪዎች ፓርት-ታይም ቢሆኑ፣ አስሩ በአገልግሎት ዘመን የሚበልጡት የፓርት-ታይም ሰራተኞች በዚያ ሳምንት ለሰሩበት ሰዓታት የሚከፈላቸው ክፍያ የፉል-ታይም ክህሎት የሌላቸው ተቀጣሪዎች የሚከፈላቸውን ይሆናል)

የፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች በሳምንት ከአርባ (40) ሰዓታት ለሚያንስ ጊዜ የስራ ፕሮግራም ሊወጣላቸው ይችላል። ነገር ግን ከአራት (4) ሰዓታት ለሚያንስ ፈረቃ ሊጠሩም ሆነ ፕሮግራም ሊያዝላቸው አይችልም።

5.09 <u>የስራ ፕሮግራም አወጣጥ እና አለጣጠፍ</u>

(1) ፕሮግራም የሚወጣው በካምፓኒው ለፉል-ታይም ተቀጣሪዎች በየዲፓርትመንቱ ውስጥ ያላቸውን ክፍፍል እና ሲኒዮሪቲን መሰረት በማድረግ ሲሆን ለፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች ደግሞ በዲፓርትመንት እና ሲኒዮሪቲ ይሆናል። ፉል-ታይምም ሆነ ፓርት-ታይም ፕሮግራም የሚወጣላቸው

ከላይ እንደተጠቆመው የሚሆነው ተቀጣሪው መደበኛ የስራ ኃላፊነቶቹን የመወጣት ብቃት እስካለው ድረስ ብቻ ነው። ፋብሪካው በሚከተሉት ዲፓርትመንቶች ይከፋፈላል፡

1. ሆግ ሪሲቪንግ
2. ፍሮንት ኢንድ ኤ.ኤም.
3. ፍሮንት ኢንድ ፒ.ኤም.
4. ድሬሲንግ ፍሎር ኤ.ኤም.
5. ድሬሲንግ ፍሎር ፒ.ኤም.
6. ኬሲንግስ ሩም ኤ.ኤም.
7. ኬሲንግስ ሩም ፒ.ኤም.
8. ስቶማክ እና ቺትስ ኤ.ኤም.
9. ስቶማክ እና ቺትስ ፒ.ኤም.
10. ላርድ፣ ሚውኮሳ እና ኢንኤዲብል ኤ.ኤም.
11. ላርድ፣ ሚውኮሳ እና ኢንኤዲብል ፒ.ኤም.
12. ላርድ፣ ሚውኮሳ እና ኢንኤዲብል ናይትስ
13. ባይፕሮዳክትስ ኤ.ኤም.
14. ባይፕሮዳክትስ ፒ.ኤም.
15. ድራይ ጉድስ፣ ሪሲቪንግ፣ ጃኒቶሪያል፣ ፕላንት ሰርቪስስ ኤ.ኤም.
16. ድራይ ጉድስ፣ ሪሲቪንግ፣ ጃኒቶሪያል ፒ.ኤም.
17. ላውንድሪ ኤ.ኤም.
18. ላውንድሪ ፒ.ኤም.
19. ላውንድሪ ናይትስ
20. **ኮንቨርቸን**፣ ኤም ኢ ፒ፣ ኤም ኤስ ፒ፣ ሮል ስቶክ፣ ፖርክ ቾፕ ኤ.ኤም.
21. ኮንቨርቸን፣ ኤም ኢ ፒ፣ ኤም ኤስ ፒ፣ ሮል ስቶክ፣ ፖርክ ቾፕ ፒ.ኤም.
22. ክራዮቫክ ኤ.ኤም.
23. ክራዮቫክ ፒ.ኤም.
24. ብሎክ ቴብል ኤ.ኤም.
25. ብሎክ ቴብል ፒ.ኤም.
26. ፒክኒክ ላይን ኤ.ኤም.
27. ፒክኒክ ላይን ፒ.ኤም.
28. በት ላይን ኤ.ኤም.
29. በት ላይን ፒ.ኤም.
30. ሎይን ላይን ኤ.ኤም.
31. ሎይን ላይን ፒ.ኤም.
32. ቤሊ ላይን ኤ.ኤም.
33. ቤሊ ላይን ፒ.ኤም.
34. ፓክ፣ ቦክስ ሩም፣ ደምፐርስ ኤ.ኤም.
35. ፓክ፣ ቦክስ ሩም፣ ደምፐርስ ፒ.ኤም.
36. ሬይልስ ኤ.ኤም.
37. ሬይልስ ፒ.ኤም.
38. ሺፒንግ ኤ.ኤም.
39. ሺፒንግ ፒ.ኤም.
40. ሺፒንግ ናይትስ
41. ሳኒቴሽን ከት
42. ሳኒቴሽን ኪል
43. ሳኒቴሽን ኦቨርሄድስ
44. ሳኒቴሽን ዊክኤንድ
45. ፍሪዘር፣ ቺል ሩም ኤ.ኤም.
46. ፍሪዘር፣ ቺል ሩም ፒ.ኤም.
47. ፍሪዘር ናይትስ
48. ሪሰርች ኤንድ ዴቨሎፕመንት
49. ካፊቴሪያ ኤ.ኤም.
50. ካፊቴሪያ ፒ.ኤም.
51. ሜይንተናንስ
52. ፓወርሃውስ/ ቄስትዋተር

ካምፓኒው በእዚህ የጋራ ድርድር ስምምነት አገልግሎት ዘመን ውስጥ ተገቢነት ላላቸው የቢዝነስ ምክንያቶች ሲባል አዲስ ዲፓርትመንቶችን የመፍጠር ፍላጎቱን ከሠላሳ የማያንሱ ምክንያታዊነት ያልጎደላቸው ቀናት አስቀድሞ ለዩኒየኑ እስካሳወቀ ድረስ

(30) አዲስ ዲፓርትመንቶችን የመፍጠር ስልጣን አለው። የስራ ምዘና ኮሚቴው ተሰብስቦ በዲፓርትመንቱ ውስጥ ያሉትን የስራ ክፍፍሎች ይመዝን እና ሁሉም ስራዎች በክፍት ስራ ማስታወቂያ ፕሮሰስ ከተሞሉ በኋላ ዲፓርትመንቱ ስራ መጀመር ይችላል።

(2) ካምፓኒው ለሁሉም የፉል-ታይምም ሆነ የፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች የሳምንቱን አጠቃላይ የስራ ፕሮግራም ዘወትር በፊተኛው ሳምንት ከሐሙስ ሳያልፍ በዋናው ሆልዌይ በዲፓርትመንት ይለጥፋል። ፕሮግራሙ እስከ ሐሙስ 6፡00 ፒ.ኤም. ድረስ ካልተለጠፈ በጊዜው ስራ ላይ ያለው ፕሮግራም ለሚቀጥለው ሳምንትም ያገለግላል። ለቢዝነሱ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ካምፓኒው እንዲሰሩ ፕሮግራም ያልተያዘላቸውን የፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች የመጥራት መብት አለው።

(3) እንደ ስኖው ስቶርም፣ ጎርፍ፣ የማሽን ብልሽት እና ሌሎች የተፈጥሮ ክስተቶችን በመሳሰሉ አስቸኳይ ጊዜያት ወቅት የተቀጣሪዎች ፕሮግራም ያለ ማስታወቂያ ሊቀየር ይችላል። ከነዚህ ሁኔታዎች በስተቀር ካምፓኒው እና ተቀጣሪው የጋራ ስምምነት ሳይኖራቸው እና አርባ ስምንት (48) ሰዓታት አስቀድሞ ማስታወቂያ ሳይወጣ ፕሮግራም ቢቀየር የአራት (4) ሰዓታት ተጨማሪ ከፍያ በቀጥታው የጊዜ ሬት ስሌት ካሳ የሚደረግ ይሆናል።

(4) <u>የጊዜ መጠበቂያዎች</u>

ካምፓኒው ተቀጣሪዎች የራሳቸውን ሰዓታት ለፔይሮል ስሌት እንዲመዘግቡ ለማስቻል የግድግዳ ሰዓቶችን እና የጊዜ ሰዓቶችን የሚያቀርብ ይሆናል። ተቀጣሪዎች ስራ መጀመሪያቸው እና ማብቂያቸው ላይ እንዲሁም የምግብ ሰዓት መጀመሪያ እና ማብቂያቸው ላይ የየራሳቸውን ሰዓት እና መሰል መዝገቦች እንደ ካምፓኒው ትእዛዝ መመዝገብ ይኖርባቸዋል። ሁሉም የጊዜ መጠበቂያዎች ሲንክሮናይዝ ይደረጋሉ።

(5) <u>ስራ ፕሮግራሞች</u>

ለጥገና ካልሆነ በስተቀር የስራ ፕሮግራሞች ሮቴሽን ፈረቃ ሳይሆኑ በመደበኛ ያልተቆራረጡ ፈረቃዎች ይዋቀራሉ። ስዊንግ ፈረቃዎች የሚሰሩት በጋራ ስምምነት ብቻ ነው። ይህም ስምምነት ያለ ምክንያት ሊደበቅ አይችልም። ሁለቱም ወገኖች የፋብሪካውን በቅልጥፍና የመስራት እና የተቀጣሪዎቹን ደህንነት መጠበቅ አስፈላጊነት በመገንዘብሊያደርጉት የሚገባ ይሆናል።

(6) የጥገና ቡድኖች በሚከተሉት ፈረቃዎች ፕሮግራም ይያዝላቸዋል፡

ሮቴሽን የሌለባቸው ቀናት - (ከሰኞ እስከ አርብ)
ሰኞ እስከ አርብ - የቀኖች እና ከሰዓቶች ሮቴሽን
የሳምንቱ ቀናት ማታዎች (ከሰኞ እስከ አርብ - ወይም ከእሁድ እስከ ሐሙስ)
የሳምንቱ መጨረሻ የቀን ፈረቃ - በሐሙስ እና ረቡዕ መካከል ፕሮግራም የሚያዝለት

ከላይ በተቀመጡት ፈረቃዎች ላይ የሚደረጉ ማንኛውቸም ለውጦች ከመተግበራቸው በፊት ለዩኒየኑ የሚነገሩ ይሆናል። እነዚህ ቡድኖች በጋራ ስምምነት ወይም የትርፍ ሰዓት ክፍያ ታስቦላቸው ካልሆነ በስተቀር ለተቃራኒ ቡድኖች እንዲሸፍኑ አይደረግም። በሕመም ወይም ቫኬሽን ጊዜ ተቀጣሪዎች (በሲኒዮሪቲ) ለጎደለው ተቃራኒ ቡድን ለአጭር ጊዜ በምትክነት እንዲሸፍኑ ሊጠየቁ ይችላሉ። በሰራተኛ እጥረት ጊዜ ተቀጣሪዎች ለአጭር ጊዜ በመጋራት መርህ ለአጭር ጊዜ በምትክነት እንዲሸፍኑ ሊጠየቁ ይችላሉ።

የጥገና ተቀጣሪን በጊዜያዊነት በጥገና ዲፓርትመንቱ ውስጥ ለሚገኝ ሌላ የስራ መደብ ለመመደብ ሲያስፈልግ በሲኒዮሪቲ ተቀጣሪዎቹ ይጠየቃሉ። ፈቃደኛ ካልተገኘም በሲኒዮሪቲ ከሁሉም ከሚያንሱት ወደ የሚበልጡት በቅደም ተከተል ተቀጣሪዎች ይመደባሉ። ካምፓኒው አንድ የጥገና ሰራተኛ የጎደለ መደብን እንዲሸፍን የሚጠየቅበትን የጊዜ ርዝማኔ ለይቶ ያስቀምጣል።

የሚመለከታቸው ዘርፎች ፕሮግራሞች በወር አንዴ ለአምስት (5) ሰዓታት ጊዜ ይለጠፋሉ። ማንኛቸውም የፕሮግራም ለውጦች ወይም ትሬድ ጭማሪዎች ቢያንስ አርባ ስምንት (48) ሰዓታት አስቀድመው ለሚቀጥለው የስራ ሳምንት የመጀመሪያ ቀን በማስታወቂያ ይታወጃሉ።

ይህ ስምምነት ከሚጸድቅበት ቀን አንስቶ የጥገና ዲፓርትመንቱ አዲስ ተቀጣሪዎች የአስራ ሁለት (12) ሰዓታት የሳምንቱ መጨረሻ ፈረቃ ፕሮግራም ሊያዝላቸው ይቻላል። አሁን ላይ ያሉት ጥገና ተቀጣሪዎች የአስራ ሁለት (12) ሰዓታት የሳምንቱ መጨረሻ ፈረቃዎችን እንዲሰሩ ከካምፓኒው ጋር በጋራ እስከተስማሙ ድረስ ፕሮግራም ሊወጣላቸው ይችላል።

የአስራ ሁለት (12) ሰዓታት የሳምንቱ መጨረሻ ፈረቃ የሚሰሩ ጥገና ተቀጣሪዎች በእዚህ ስምምነት አፔንዲክስ F ይሸፈናሉ።

(7) አንድ ተቀጣሪ ለአስቸኳይ ጊዜ በማኔጅመንት ለስራ በሚጠራበት ጊዜ ተቀጣሪው በየአንድ ተኩል (1½) ሰዓቱ ቢያንስ የሦስት (3) ሰዓታት ካሳ ይደረግለታል። በመሆኑም በእንደነዚህ አይነት ጥሪዎች የሚውሉ የስራ ሰዓታት ከአርባ (40) ሰዓታት በላይ የተሰሩ የትርፍ ሰዓት ክፍያዎችን ለማስላት አያገለግሉም።

(8) መጥፎ የአየር ሁኔታ ተከስቶ ብራንደን ትራንዚት ቢዘጋ ወይም ቢያረፍድ፣ ወይም መንገዶች (በዲፓርትመንት ኦፍ ሃይዌይስ፣ በ RCMP፣ ወይም በብራንደን ፖሊስ አገልግሎት) ከብራንደን ከተማ ወጣ ብለው ቢዘጉ እና ተቀጣሪው በስራ ገበታ ላይ በጊዜም ሆነ ጨርሶ መገኘት ቢያቅተው ያ ተቀጣሪ ለዲሲፕሊን እርምጃ አይጋለጥም። መቅረቱም እንደ አቴንዳንስ ቦነስ ከመሳሰሉ ማንኛውም አይነት ጥቅማ ጥቅሞች አያስቀረውም።

5.10 <u>የምግብ እና የእረፍት ሰዓታት</u>

እረፍቶቹ እንደ ለቢዝነሱ አስፈላጊ ሆነው እንደሚገኙት ሁኔታዎች እንደሚለያዩ የታወቀ ነው።

(1) የአራት ሰዓታት እና ከአራት (4) እስከ አምስት (5) ሰዓታት (አምስትን ጨምሮ) ዕለታዊ ፈረቃ አንድ ክፍያ የሚታሰብለት የእረፍት ወቅት ይኖረዋል።

(2) ከአምስት (5) ሰዓታት በላይ ነገር ግን ከሰባት (7) ሰዓታት በታች የሆነ ዕለታዊ ፈረቃ የሚሰራ **ተቀጣሪ** አንድ (1) ክፍያ የሚታሰብለት የእረፍት ወቅት እና አንድ (1) ክፍያ የማይታሰብለት የሠላሳ (30) ደቂቃ መመገቢያ ወቅት ይኖረዋል።

(3) ከሰባት (7) ሰዓታት በላይ እና እስከ ስምንት (8) ሰዓታት ድረስ የሆነ ዕለታዊ ፈረቃ የሚሰራ **ተቀጣሪ** አንድ (1) ክፍያ የማይታሰብለት የሠላሳ (30) ደቂቃ መመገቢያ ወቅት እና ሁለት (2) ክፍያ የሚታሰብላቸው የአስራ አምስት (15) ደቂቃ የእረፍት ወቅቶች ከእያንዳንዱ ከምግብ ወቅት በፊት እና በኋላ በሚመጣ ወቅት መሃል ከሠላሳ (30) ደቂቃ በፊት ወይም እስከ ሠላሳ (30) ደቂቃ በኋላ በሚኖረው ጊዜ ፕሮግራም ይያዝለታል።

(4) የአስር (10) ሰዓታት ፈረቃ የሚሰሩ ተቀጣሪዎች አንድ (1) ክፍያ የማይታሰብለት የሠላሳ (30) ደቂቃ መመገቢያ ወቅት እና ሁለት (2) ክፍያ የሚታሰብላቸው የአስራ አምስት (15) ደቂቃ የእረፍት ወቅቶች ክፍያ ከሚታሰብለት አንድ የአስር (10) ደቂቃ እረፍት ወቅት ጋር ተደምረው ይሰጣቸዋል። (ይህ የአስር ደቂቃ እረፍት ወቅት የዕለቱ የመጨረሻ እረፍት ሊሆን ይገባዋል)

(5) እነዚህ የመመገቢያ እና የእረፍት ወቅቶች የሚወሰዱበት ሰዓት በማኔጅመንት ፕሮግራም የሚወጡ ይሆናል። ክፍያ የሚታሰብላቸው የእረፍት ወቅቶች ከእያንዳንዱ ከምግብ ወቅት በፊት እና በኋላ በሚመጣ ወቅት መሃል ከሠላሳ (30) ደቂቃ በፊት ወይም እስከ ሠላሳ (30) ደቂቃ በኋላ በሚኖረው ጊዜ ውስጥ ይሆናሉ። የሰባት (7) ሰዓታት ወይም ከዚያ በላይ ዕለታዊ ፈረቃዎችን የሚሰሩ ተቀጣሪዎች የመመገቢያ ወቅት ፈረቃው ከተጀመረ ከሦስት እስከ አምስት ሰዓታት ባሉት ጊዜያት ውጪ ሊጀምር አይችልም።

(6) አንድ ተቀጣሪ የስምንት (8) ወይም አስር (10) ሰዓታት ፈረቃውን ከመጨረሱ በፊት ወይም እንደጨረሰ ኦቨርታይም እንዲሰራ ከተገደደ እና ካምፓኒው ክፍያ የማይታሰብበት የመመገቢያ ወቅት ካላዘጋጀ ተቀጣሪው ክፍያ የሚታሰብለት የአስራ አምስት (15) ደቂቃ የእረፍት ወቅት የመጀመሪያው ፈረቃ ባለቀ በግማሽ ሰዓት ጊዜ ውስጥ ይመደብለታል። ይህ የሚሆነው ግን ኦቨርታይሙ ለሁለት (2) ሰዓታት ወይም ከዛ በላይ ከሆነ ብቻ ነው። ኦቨርታይም በተሰራበት ፈረቃ እያንዳንዱ ተጨማሪ ሦስት (3) ሰዓታት ከማለፋቸው በፊት እረፍት ይሰጣል።

(7) ካምፓኒው እና ዩኒየኑ ካምፓኒው የሚመድባቸው የእረፍት ወቅቶች አስራ አምስት (15) ደቂቃ እንዲሆን ተስማምተዋል። ያልተቋረጡ የአስር (10) ደቂቃ እረፍቶች ደግሞ የዕለቱ የመጨረሻ እረፍትሆነው ለባለ አስር ሰዓታት ፈረቃዎች የሚሰጡ ይሆናል። የእረፍት ጊዜ የማይሰጥ ከሆነ ተቀጣሪው ተጨማሪ የአስራ አምስት (15) ደቂቃ ክፍያ በተገቢው የኦቨርታይም ሬት ይከፈለዋል።

(8) የጥገና እረፍት እና መመገቢያ እረፍቶች በፕሮዳክሽን አካባቢ የሚወሰዱ ይሆናሉ። ይህም የጥገና ሽፋን በፍሎሩ ላይ በማንኛውም ጊዜ እንዲኖር ያረጋግጣል። ፍሌክስ እረፍቶች እና ምሳ ሊድ ሃንድ ወይም ሱፐርቫይዘር ፈቃድ በመጠየቅ ለራስ በራስ የሚሰጡ መሆን አለባቸው። ለአስቸኳይ ጊዜ የብልሽት ምክንያቶች የእረፍት ወይም የመመገቢያ ወቅቶች በካምፓኒው ቢቋረጡ ካምፓኒው የእረፍት ወቅቶቹን ለሌላ ጊዜ የማስተላለፍ ወይም ለታጣው የእረፍት ጊዜ ካሳ በመክፈል የማለፍ ምርጫ አለው። አንድ ተቀጣሪ ትኩስ ምግብ አዘ ተመግቦ ሳይጨርስ ከተቋረጠ ካምፓኒው ለተቀጣሪው የምግብ ቫውቸር በመስጠት ይክሰዋል።

(9) የሚከተሉት ሁኔታዎች በሚከሰቱበት ጊዜ የመመገቢያ እና የእረፍት ወቅቶች ከሠላሳ (30) ደቂቃ ታይምፍሬም ውጪ በሆነ መልኩ ሊስተካከሉ እንደሚያስፈልግ ግንዛቤ አለ፡

a) ከአንድ (1) ሰዓት በላይ የሚፈጁ ብልሽቶች

b) የሆነች እጥረት

c) ከካምፓኒው ቁጥጥር ውጪ የሆኑ እንደ ጎርፍ፣ እሳት፣ ወዘተ የመሳሰሉ ከባድ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች

ከላይ በተመለከቱት ምክንያት የእረፍት ወቅቶች ከመደበኛው ሠላሳ (30) ደቂቃ ታይምፍሬም ውጪ እንዲስተካከሉ ከተደረገ ካምፓኒው ዋና አስተናባሪውን ወይም ምክትል ዋና አስተናባሪውን (ህንጻው ውስጥ በጊዜው የተገኘውን አንዳቸውን) ስለ የእረፍት ወቅቶቹ መስተካከል እና ማስተካከል ስላስፈለገበት ምክንያት ያሳውቃል። ካምፓኒው እና ዩኒየኑ ማንኛቸውንም ከላይ ከተጠቀሱት ታይምፍሬሞች ውጪ ያሉ ለውጦችን የሚከታተሉ እና ከተቻለም ለውጦቹን ለመቀነስ እርምጃዎችን የሚወስዱ ይሆናል።

5.11 <u>ግላዊ እረፍቶች</u>

(a) ዩኒየኑ በግላዊ ጉዳዮች አስገዳጅነት ካልሆነ በስተቀር ተቀጣሪዎች በዕለቱ ውስጥ ተጨማሪ የእረፍት ጊዜ መጠየቅ እንደማይችሉ ተስማምቷል። ዩኒየኑ የእረፍት ወቅቶች አለአግባብ መጠቀሚያ ሊሆኑ እንደማይገቡ ተስማምቷል።

(b) ተቀጣሪዎች ካምፓኒው በተስማማባቸው መንገዶች ጊዜያቸውን ለግላዊ እረፍቶች በመጠቀማቸው ምክንያት ቅጣትም ሆነ መባረር ሊያጋጥማቸው አይችልም። ነገር ግን ከልክ ያለፈ አጠቃቀምን ለመግታት ሲባል የሚከተሉት እርምጃዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡

(i) ተቀጣሪዎች በእያንዳንዱ እረፍት ላይ የሚጠቀሙት ጊዜ ከሳምንታዊ የስራ ሰዓታቸው ላይ ይቀነስባቸዋል።

(ii) በህክምና ሰነድ በተደገፈ የጤና እክል ምክንያት ከተለመደው በላይ የመታጠቢያ ቤት ለመጠቀም የሚገደዱ ተቀጣሪዎች መታጠቢያ ቤት በመጠቀማቸው ከስራ ሰዓታቸው ላይ አይቀነስባቸውም።

(c) ዩኒየኑ ግላዊ እረፍቶችን ያለአግባብ የሚጠቀሙ ተቀጣሪዎችን ለመቆጣጠር ከካምፓኒው ጋር አብሮ ለመስራት ተስማምቷል።

5.12 **<u>የፅዳት ጊዜ</u>**

የካምፓኒው የHACCP ግዴታዎች ይሚሉ ዘንድ ተቀጣሪዎች ከፈረቃቸው ማብቂያ ቀደም ብሎ በቂ የፅዳት ጊዜ ክፍያ እየታሰበለት ይፈቀድላቸዋል። ተቀጣሪዎች የመንገድ ልብሳቸውን ከመልበሳቸው አስቀድመው ፓንች አውት ማድረግ ይኖርባቸዋል። ተቀጣሪዎች እንዲሰሩ በመገደዳቸው ምክንያት ከመደበኛው የፈረቃ ማብቂያ በኋላ የሚራዘመው የፅዳት ጊዜ ክፍያው የሚታሰበው ተቀጣሪው ከፈረቃው ማብቂያ በኋላ ለሚሰራት እያንዳንዷ ደቂቃ የመደበኛ ስራ ክፍያው አንድ ከግማሽ (1½) እጥፍ ተደርጎ ይሆናል።

5.13 አንድ ተቀጣሪ በማንኛውም ምክንያት በስራ ገበታው ላይ ለመገኘት ባይችል ከስራ መጀመሪያው ቢያንስ አንድ ከግማሽ (½) ሰዓት አስቀድሞ የቀረበትን ምክንያት እና ቀርቶ የሚቆይበትን ጊዜ ርዝማኔ ለካምፓኒው ማሳወቅ ይኖርበታል። ካምፓኒው ለዚህ የሚያገለግል ጥሪው ስለመፈጸሙ ማረጋገጫ የሚሰጥ ልዩ የደውሎ ማሳወቂያ ቁጥር/ቁጥሮች ሊኖሩት ይገባል። የቦነስ ክፍያ ጊዜው እስኪያልቅ ድረስ ሁሉም እነዚህ ጥሪዎች ተመዝግበው ይቀመጣሉ።

<u>አንቀጽ 6 ኦቨርታይም</u>

6.01 ተቀጣሪዎች ከመደበኛው የዕለት ስምንት (8)፣ አስር (10) ወይም የሳምንት አርባ (40) ስራ ሰዓታታቸው በተጨማሪ እንዲሰሩ ሊጠየቁ እና ተቀጣሪዎቹም በእዚህ ረገድ ካምፓኒውን ለመተባበር ሊስማሙ ይችላሉ። ነገር ግን ማንኛውም ተቀጣሪ ከምክንያታዊነት የራቀ መጠን ያለው ኦቨርታይም እንዲሰራ አይጠየቅም። በተጨማሪም ተቀጣሪው በቂና አሳማኝ ምክንያት ለካምፓኒው ካቀረበ ኦቨርታይም እንዲሰራ አይገደድም። እያንዳንዱ ተቀጣሪ ለኦቨርታይም እንዲገኝ የሚገባውን ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል። ተቀጣሪው የሚገባውን ጥረት እያደረገ እንዳልሆነ ካምፓኒው በሚሰማው ጊዜ በሚመለከተው ተቀጣሪ፣ በዩኒየኑ እና በካምፓኒው መካከል ስብሰባ የሚደረግ ይሆናል።

6.02 የአምስት (5) ቀን የስራ ሳምንት ላላቸው ተቀጣሪዎች ኦቨርታይም ለሰሩባቸው ሰዓታት በሙሉ የሬታቸውን አንድ ከግማሽ (1½) እጥፍ ወይም በቀን ከስምንት (8) ሰዓታት ወይም በሳምንት ከአርባ (40) ሰዓታት በላይ ለሰሩበት (የዩኒየን ፈቃዶችን ጨምሮ) ኦቨርታይሙ የተሰራው ከፈረቃቸው ፕሮግራም በፊትም ይሁን በኋላ የሚከፈላቸው ይሆናል። በሰባተኛው (7ኛው) ተከታታይ ቀን ላይ የሚሰሩ ሰዓታት በሙሉ ክፍያቸው ደብል ታይም (በሁለት እጥፍ) ይታሰባል።

የአስራ ስድስት (16) ሰዓት ወይም ከዛ በላይ ደብል ፈረቃ የሚሰራ ማንኛውም ተቀጣሪ በኦቨርታይሙ ላይ ለሚሰራባቸው ሰዓታት በሙሉ ደብል ታይም (ሁለት እጥፍ) ይከፈለዋል። ከአስራ ስድስት (16) ሰዓት በታች የሆነ ደብል ፈረቃ የሚሰራ ማንኛውም ተቀጣሪ በኦቨርታይሙ ላይ ለሚሰራባቸው ሰዓታት በሙሉ አንድ ከግማሽ እጥፍ (1½) ይከፈለዋል።

ከላይ የተቀመጡት እንዳሉ ሆነው አንድ የጥገና ሰራተኛ ለደብል ፈረቃ ፕሮግራም ተይዞለት የነበረ ቢሆን እና ሁለተኛው ፈረቃ ከማለቁ በፊት ወደ ቤቱ ቢሸኝ ሁለተኛው ፈረቃ ላይ ለሰራባቸው ለሁሉም ሰዓታት ደብል ታይም (ሁልት እጥፍ) ይከፈለዋል። አንድ የጥገና ያልሆነ ሰራተኛ ለደብል ፈረቃ ፕሮግራም ተይዞለት የነበረ ቢሆን እና ሁለተኛው ፈረቃ ከማለቁ በፊት ወደ ቤቱ ቢሸኝ ፕሮዳክሽን ሁለተኛው ፈረቃ ከማለቁ በፊት ካላለቀ በስተቀር እና

ከካምፓኒው ቁጥጥር ውጭ በሆነ ምክንያት ፈረቃው መቀነስ ከላስፈለገ በስተቀር ሁለተኛው ፈረቃ ላይ ለሰራባቸው ለሁሉም ሰዓታት ደብል ታይም (ሁልት እጥፍ) ይከፈለዋል።

6.03 የአራት (4) ቀን የስራ ሳምንት ላላቸው ተቀጣሪዎች ኦቨርታይም ለሰሩባቸው ሰዓታት በሙሉ የሬታቸውን አንድ ከግማሽ እጥፍ ወይም በቀን ከአስር (10) ሰዓታት ወይም በሳምንት ከአርባ (40) ሰዓታት በላይ ለሰሩበት የሚከፈላቸው ይሆናል። በስድስረኛው (6ኛው) እና በሰባተኛው (7ኛው) ተከታታይ ቀን ላይ የሚሰሩ ሰዓታት በሙሉ ክፍያቸው ደብል ታይም (በሁለት እጥፍ) ይታሰባል።

በቀን አስራ ሁለት (12) የስራ ሰዓታት የሚሰሩ ሰዎች ኦቨርታይም የዚህን ስምምነት አፔንዲክስ E በመከተል የሚከፈላቸው ይሆናል።

6.04 አንድ ተቀጣሪ ፕሮግራም ከተያዘለት የፈረቃ መጀመሪያ ጊዜ አስቀድሞ ለመምጣት ከተስማማ እና የተስማማውም ፈረቃ መጀመሪያው ሊደርስ ከአርባ ስምንት (48) ሰዓታት በታች ቀርቶት እያለ በወጣ ማስታወቂያ ከሆነ እስከ ፈረቃ መጀመሪያው ድረስ ለሚሰራቸው ሰዓታት በሙሉ የሬቱን አንድ ከግማሽ (1½) እጥፍ ለመክፈል ካምፓኒው ተስማምቷል። ይህ እንዳለ ሆኖ ተቀጣሪው መደበኛ የፈረቃ ሰዓታቱን በመደበኛ ሬት ሂሳብ እንዲሰራ ይጠበቅበታል።

6.05 <u>የኦቨርታይም መጠይቅ</u>

ኦቨርታይም አስፈላጊ ሲሆን የሚመለከተው ዲፓርትመንት ዩኒየን አስተናባሪ እና ተቀጣሪዎች ፈረቃቸው ከማለቁ በፊት በተቻለ ፍጥነት ሊነገራቸው ይገባል።

ኦቨርታይም በሚከተሉት መንገዶች ለተቀጣሪዎች ሊቀርብላቸው ይገባል።

1) <u>ፕሮግራም የተያዘለት ኦቨርታይም</u>

ፕሮግራም የተያዘለት ኦቨርታይም ማለት ስለመኖሩ ከአስፈላጊነቱ በፊት ካምፓኒው የሚያውቀው ነው። ይህም እንደ የሳምንቱ መጨረሻ ላይ ያለ ኦቨርታይምን እና ሌሎች ተቀጣሪዎች ቫኬሽን በመሄዳቸው፣ ፈቃድ በመውሰዳቸው፣ እና በመታመማቸው ምክንያት ከአንድ (1) ቀን ለሚበልጥ ጊዜ ሲቀሩ የሚመጣ ኦቨርታይምን ያካትታል።

ፕሮግራም የተያዘለት ኦቨርታይም በጋራ ስምምነት ሊሆን እና በሲኒዮሪቲ ቅደም ተከተል በክፍፍሉ እና በዲፓርትመንቱ ውስጥ በማንኛውም ፈረቃ ላይ ላሉት ሁሉም ተቀጣሪዎች ሊቀርብላቸው ይገባዋል። በመቀጠልም በሲኒዮሪቲ ቅደም ተከተል ከክፍፍሉ እና ከዲፓርትመንቱ ውጪ በማንኛውም ፈረቃ ላይ ላሉት ሁሉም ተቀጣሪዎች ይቀርብላቸዋል። አግባብነት ሲኖረው በዲፓርትመንቱ ውስጥ ያሉ ፈረቃዎችን ሁሉ ወደ አንድ በማምጣት ፕሮግራም የተያዘለት ኦቨርታይም እንዲቀርብ ይደረጋል።

ይህን ስልት በመጠቀም የተፈለገውን ያህል የበጎ ፈቃደኞች ቁጥር ለማግኘት ካልተቻለ በመቀጠል ከዲፓርትመንቱ ውጭ ላሉ እና ለተፈለገው ስራ ብቁ ለሆኑ የፋብሪካው ተቀጣሪዎች በሙሉ በማንኛውም ፈረቃ ላይ ቢኖሩም እንኳ በሲኒዮሪቲ ቅደም ተከተል ፕሮግራም የተያዘለት ኦቨርታይም ይቀርብላቸዋል።

እንደዚህም ተደርጎ ፕሮግራም የተያዘለት ኦቨርታይም ለመስራት የሚያስፈልገውን በቂ የበጎ ፈቃደኞች ቁጥር ለማግኘት ካልተቻለ ለ**አንቀጽ** 6.01 ተገዢ የሆኑት የዲፓርትመንቱ እጅግ ጁኒየር ተቀጣሪዎች

ለተፈለገው ስራ ብቁ እስከሆኑ ድረስ በማንኛውም ፈረቃ ላይ ቢኖሩም እንኳ በሲኒዮሪቲ ቅደም ተከተል የተፈለገውን ስራ ይሰራሉ። ነገር ግን ማንኛውም ተቀጣሪ ከምክንያታዊነት ያለፈ መጠን ያለውን ኦቨርታይም እንዲሰራ ሊገደድ አይገባም።

2) <u>በየጊዜው ፕሮግራም የሚያዝለት ኦቨርታይም:</u>

በየጊዜው ፕሮግራም የሚያዝለት ኦቨርታይም ከሚከተሉት እንደ አንዱ ይተረጎማል፡

- ለሴትአፕ፣ ፕሪኦፕ፣ ኮንደንሴሽን እና ናይፍ ኬጆች ሲባል ከፕሮዳክሽን በፊት ቢበዛ ለአንድ ሰዓት ተኩል (1½) የሚደረግ ተከታታይ ኦቨርታይም

- ለፖስትኦፕ እና ወለል ለማጽዳት ሲባል ከፕሮዳክሽን በኋላ ቢበዛ ለአንድ ሰዓት ተኩል (1½) የሚደረግ ተከታታይ ኦቨርታይም

ከፕሮዳክሽን በፊት የሚደረግ ተከታታይ ኦቨርታይም በሲኒዮሪቲ ቅደም ተከተል እና በዲፓርትመንት መደበኛ ፈረቃቸው የቀን ለሆኑ ተቀጣሪዎች ይቀርባል።

ከፕሮዳክሽን በኋላ የሚደረግ ተከታታይ ኦቨርታይም በሲኒዮሪቲ ቅደም ተከተል እና በዲፓርትመንት መደበኛ ፈረቃቸው የከሰዓት ወይም የማታ ለሆኑ ተቀጣሪዎች ይቀርባል።

ከፕሮዳክሽን በፊትም ሆነ በኋላ ተከታታይ ኦቨርታይሙን ለመስራት የሚያስፈልገውን ያህል ቁጥር ያላቸው በጎ ፈቃደኞች ማግኘት ካልተቻለ እጅግ ጁኒየር የሆኑት እና ለስራው ብቁ የሆኑት በፈረቃው ላይ ያሉት የዲፓርትመንቱ ተቀጣሪዎች **አንቀጽ** 6.01ን በመከተል በሲኒዮሪቲ ቅደም ተከተል አስፈላጊውን ስራ ይሰራሉ። ነገር ግን ማንኛውም ተቀጣሪ ከምክንያታዊነት ያለፈ መጠን ያለውን ኦቨርታይም እንዲሰራ ሊገደድ አይገባም።

ለሚመጣው ሳምንት ከፕሮዳክሽን በፊትም ይሁን በኋላ የሚያስፈልገው ሁሉም ተከታታይ ኦቨርታይም ለተቀጣሪዎች የሚቀርበው የሚመለከታቸውን ተቀጣሪዎች በእዚህኛው ሳምንት ከረቡዕ እኩለ ሌሊት ሳያልፍ በቀጥታ በማነጋገር ይሆናል። ካምፓኒው ከላይ በተቀመጠው ስልት የተመረጡትን ተቀጣሪዎች በተቻለ ፍጥነት ያሳውቃቸዋል። ነገር ግን ለሚቀጥለው ሳምንት የዚህን ሳምንት ሐሙስ እኩለ ሌሊት አሳልፎ ሊሆን አይችልም።

3) <u>ፕሮግራም ያልተያዘለት ኦቨርታይም - ከአንድ (1) ሰዓት የሚበልጥ፡</u>

ከአንድ (1) ሰዓት የሚበልጥ ርዝማኔ ያለው ሌላው ኦቨርታይም ሁሉ በጋራ ስምምነት ሊሆን እና በሲኒዮሪቲ ቅደም ተከተል በክፍፍሉ እና በዲፓርትመንቱ ውስጥ በማንኛውም ፈረቃ ላይ ላሉት ሁሉም ተቀጣሪዎች ሊቀርብላቸው ይገባዋል። **ዲፓርትመንቱ ላይ ፖስት የተደረጉ ሰራተኞች እዚያ ዲፓርትመንት ውስጥ በግዜያዊነት ተመድበው ከሚሰሩ ሰራተኞች አስቀድሞ ኦቨርታይም ይቀርብላቸዋል።**

ካምፓኒው ተቀጣሪዎች ኦቨርታይም እንዲሰሩ በቀጥታ እያነጋገረ ባለበት ሰዓት ለስራው ብቁ የሆኑት በፈረቃው ላይ ያሉት የዲፓርትመንቱ እጅግ ጁኒየር ተቀጣሪዎች ኦቨርታይም ለመስራት ፈቃደኛ በሆኑ ተቀጣሪዎች እስከሚተኩበት ሰዓት ድረስ ከመደበኛ የስራ ሰዓታቸው አልፈው

እንዲሰሩ ሊገደዱ እንደሚችሉ መገንዘብ ያሻል። በእዚህ ሁኔታ ጁኒየር ተቀጣሪዎች እንዲቆዩ ሲገደዱ ኦቨርታይም ከመስራት የሚያግድ አሳማኝ ግላዊ ምክንያት ያላቸው ተቀጣሪዎች ያለ ቅጣት ይለቀቃሉ።

በመቀጠልም በሲኒዮሪቲ ቅደም ተከተል ከክፍፍሉ እና ከዲፓርትመንቱ ውጪ በማንኛውም ፈረቃ ላይ ላሉት ሁሉም ተቀጣሪዎች ይቀርብላቸዋል። አግባብነት ሲኖረው በዲፓርትመንቱ ውስጥ ያሉ ፈረቃዎችን ሁሉ ወደ አንድ በማምጣት ፕሮግራም የተያዘለት ኦቨርታይም እንዲቀርብ ይደረጋል።

ይህን ስልት በመጠቀም የተፈለገውን ያህል የበጎ ፈቃደኞች ቁጥር ለማግኘት ካልተቻለ በመቀጠል ከዲፓርትመንቱ ውጭ ላሉ እና ለተፈለገው ስራ ብቁ ለሆኑ የፋብሪካው ተቀጣሪዎች በሙሉ በማንኛውም ፈረቃ ላይ ቢኖሩም እንኳ በሲኒዮሪቲ ቅደም ተከተል ፕሮግራም የተያዘለት ኦቨርታይም ይቀርብላቸዋል።

ካምፓኒው ተቀጣሪዎችን በቀጥታ የማነጋገሩን ሂደት የተጠበቀው የኦቨርታይም ርዝማኔ እንደታወቀ ለመጀመር እና በተቻለ ፍጥነት ለመጨረስ ተስማምቷል። ይህም የሚሆነው ጁኒየር ተቀጣሪዎች እንዲሰሩ የሚገደዱትን ኦቨርታይም ለመቀነስ እና የኦቨርታይም መጠኑን ለሲኒየሮች ለመጨመር ነው።

እንደዚህም ተደርጎ ፕሮግራም የተያዘለትን ኦቨርታይም ለመስራት የሚያስፈልገውን ያህል ቁጥር ያላቸው በጎ ፈቃደኞች ማግኘት ካልተቻለ እጅግ ጁኒየር የሆኑት እና ለስራው ብቁ የሆኑት በፈረቃው ላይ ያሉት የዲፓርትመንቱ ተቀጣሪዎች **አንቀጽ** 6.01ን በመከተል በሲኒዮሪቲ ቅደም ተከተል አስፈላጊውን ስራ ይሰራሉ። ነገር ግን ማንኛውም ተቀጣሪ ከምክንያታዊነት ያለፈ መጠን ያለውን ኦቨርታይም እንዲሰራ ሊገደድ አይገባም።

4) <u>ፕሮግራም ያልተያዘለት ኦቨርታይም - አንድ (1) ሰዓት ወይም ከእዚያ በታች</u>

የአንድ (1) ሰዓት ወይም ከእዚያ የሚያንስ ርዝማኔ ያለው ኦቨርታይም የሚቀርበው በጋራ ስምምነት ሊሆን እና በሲኒዮሪቲ ቅደም ተከተል ኦቨርታይሙ ባስፈለገበት ጊዜ በክፍፍሉ እና በዲፓርትመንቱ ውስጥ በፈረቃው ላይ ለሚገኙት ሁሉም ተቀጣሪዎች ሊቀርብላቸው ይገባዋል።

በመቀጠልም በሲኒዮሪቲ ቅደም ተከተል ከክፍፍሉ ውጪ ነገር ግን በዲፓርትመንቱ ውስጥ እና በፈረቃው ላይ ላሉት ሁሉም ተቀጣሪዎች ይቀርብላቸዋል።

እንደዚህም ተደርጎ ፕሮግራም የተያዘለትን ኦቨርታይም ለመስራት የሚያስፈልገውን ያህል ቁጥር ያላቸው በጎ ፈቃደኞች ማግኘት ካልተቻለ እጅግ ጁኒየር የሆኑት እና ለስራው ብቁ የሆኑት በፈረቃው ላይ ያሉት የዲፓርትመንቱ ተቀጣሪዎች **አንቀጽ** 6.01ን በመከተል በሲኒዮሪቲ ቅደም ተከተል አስፈላጊውን ስራ ይሰራሉ። ነገር ግን ማንኛውም ተቀጣሪ ከምክንያታዊነት ያለፈ መጠን ያለውን ኦቨርታይም እንዲሰራ ሊገደድ አይገባም።

ለአንቀጽ 6.05 ሲባል ጄነራል ሌበር 1 እና 2 ወደ አንድ (1) ክፍፍል ይደባለቃሉ፤ ሴሚ-ስኪልድ 1 እና 2 ወደ አንድ (1) ክፍፍል ይደባለቃሉ፤ እናም ስኪልድ 1 እና 2 ወደ አንድ (1) ክፍፍል ይደባለቃሉ። የጥገና ዲፓርትመንት ኦቨርታይም የሚቀርበው በትሬድ ይሆናል።

ማንኛውም ብቁ የሆነ ተቀጣሪ በእዚህ ሮቴሽን ላይ በስህተት ከአንድ ጊዜ በላይ ከተዘለለ ካምፓኒው ከላይ የተቀመጠውን አሰራር ተከትሎ ቢሆን ኖሮ ተቀጣሪው ያገኝ የነበረውን ክፍያ ለተቀጣሪው በካሳ መልክ ለመክፈል ካምፓኒው ተስማምቷል።

ለኦቨርታይም ብቻ የሚያገለግል የፋብሪካው የዲፓርትመንቶች ዝርዝር እንደሚከተለው ነው፡

1. ሆግ ሪሲቪንግ
2. ፍሮንት ኢንድ ኪል
3. ድሬሲንግ ፍሎር
4. ኬሲንግስ ሩም
5. ስቶማክ እና ቺትስ
6. ላርድ፣ ሚውከሳ እና ኢንኤዲብል
7. ባይፕሮዳክትስ
8. ድራይ ጉድስ፣ ሪሲቪንግ፣ **ጃኒቶሪያል**፣ ፕላንት ሰርቪስስ
9. ላውንድሪ
10. **ኮንቨርቸን**፣ ኤም ኢ ፒ፣ ኤም ኤስ ፒ፣ ሮል ስቶክ፣ ፖርክ ቾፕ
11. ክራዮቫክ
12. ብሎክ ቴብል
13. ፒክኒክ ላይን
14. በት ላይን
15. ሎይን ላይን
16. ቤሊ ላይን
17. ፓክ፣ ቦክስ ሩም፣ ደምፐርስ
18. ሬይልስ
19. ሺፒንግ
20. ሳኒቴሽን
21. ፍሪዘር ኤንድ ቺል ሩም
22. ሪሰርች ኤንድ ዴቨሎፕመንት
23. ካፌቴሪያ
24. ሜይንተናንስ
25. ፓወርሃውስ/ ዌስትዋተር

6.06 ማንኛውም አይነት የኦቨርታይም ፒራሚድ አሰራር አይኖርም።

6.07 ከጁን 1፣ 2020 ጀምሮ ካምፓኒው ከጃኒዋሪ 1 እስከ ዲሴምበር 25 የስምንት (8) ሰዓታት ፈረቃዎችን በመደበኛነት ለሚሰሩ ተቀጣሪዎች እስከ ሠላሳ ሁለት (32) ሰዓታት ድረስ፣ የአስር (10) ሰዓታት ፈረቃዎችን በመደበኛነት ለሚሰሩ ተቀጣሪዎች ደግሞ እስከ አርባ (40) ሰዓታት ድረስ የሚደርስ ኦቨርታይም ባንክ እንዲያደርጉ ይፈቅዳል። ጥቅም ላይ ያልዋለ ማንኛውም አይነት ባንክ የተደረገ ኦቨርታይም በዓመቱ ዲሴምበር 31 ላይ ክፍያ ይፈፀምለታል።

ባንክ የሚደረግ ኦቨርታይም አገልግሎት ላይ ሊውል የሚችለው ፕሮዳክሽን ለሌለባቸው ቀናት እና ክፍያ ለማይታሰብባቸው ግላዊ እረፍት ቀናት ብቻ ነው።

አንድ ተቀጣሪ ኦቨርታይም ባንክ ለማድረግ ቢፈልግ የሚከተለው አሰራር ተግባራዊ ይሆናል፡

1. **ፕሮዳክሽን ለሌለባቸው ቀናት ወይም ክፍያ ለማይታሰብባቸው ግላዊ እረፍት ቀናት ክፍያ እንዲታሰብ ሃያ አራት (24) ሰዓታት አስቀድሞ መጠየቅ ያስፈልጋል። ጥያቄውም ያለ በቂ ምክንያት ውድቅ አይደረግም።**

2. **እያንዳንዱ ተቀጣሪ ለእያንዳንዱ አመት ባንክ የሚደረግ የኦቨርታይም ምርጫውን ጃኒዋሪ 1 ላይ ማሳወቅ ይኖርበታል።**

3. **ኦቨርታይም እንደ መደበኛ ሰዓት፣ እንደ አንድ ከግማሽ (1½) እጥፍ ሰዓት፣ ወይም እንደ ሁለት (2) ሰዓት ደብል ኦቨርታይም ባንክ ሊደረግ ይችላል።**

4. **በእያንዳንዱ አመት ዲሴምበር 31 ላይ የሚቀረው ባንክ የተደረገ ኦቨርታይም በተሰበሰበበት ሬት ክፍያ ይፈፀምለታል።**

5. **አንድ ተቀጣሪ የባንኩ የመጨረሻው ኢንታይትልመንት ላይ ደርሶ ኦቨርታይም መስራት ቢቀጥል አመቱ እስኪያልቅ ድረስ ተጨማሪ ሰዓታት ባንክ አይደረጉለትም። ሁሉም ተጨማሪ ኦቨርታይምም ኧርን እንደተደረገ ተቆጥሮ ክፍያ ይፈፀምለታል።**

6. **ባንክ የተደረገ ኦቨርታይም የሚከፈለው ኦቨርታይሙ ባንክ በተደረገበት ወቅት ተቀጣሪው ይከፈለው በነበረው ሬት ነው።**

6.08 በብራንደን ትራንዚት የሚገለገል ተቀጣሪ ኦቨርታይም እንዲሰራ ሲገደድ ወይም በጊዜ ሲለቀቅ ወደ ቤቱ የሚሄደው ቀጣዩ ባስ እስኪመጣ ከአንድ (1) ሰዓት በላይ የሚፈጅ ከሆነ እና ሌላ የትራንስፖርት አማራጭ ከሌለ ካምፓኒው ትራንስፖርት አቅርቦ ቤቱ ያደርሰዋል።

<u>አንቀጽ 7 ሲኒዮሪቲ</u>

7.01 ሲኒዮሪቲ ማለት ለመጨረሻ ጊዜ ከተቀጠረበት ዕለት አንስቶ አንድ ተቀጣሪ በካምፓኒው ያለው ሲኒዮሪቲ ተብሎ ይተረጎማል። ለፉል-ታይም ተቀጣሪዎች ይህ ዕለት ለፉል-ታይም የስራ መደብ የተቀጠሩበት ቀን ነው። አንድ የፓርት-ታይም ተቀጣሪ በ**አንቀጽ** 4.01 እንደተጠቆመው የፕሮቤሽን ወቅቱ ሳያልቅ ለፉል-ታይም የስራ መደብ ቢመደብም ተቀጣሪው የከፊል እና የሙሉ ጊዜ ሰዓታቱ ተደምረው 980 ሰዓት እስኪሞሉ ድረስ የፕሮቤሽን ወቅቱን መጨረስ ይኖርበታል።

ሁለት ተቀጣሪዎች ስራ የጀመሩት ወይም የተቀጠሩት በተመሳሳይ ቀን ከሆነ የሲኒዮሪቲ ደረጃቸው የሚወሰነው የስራ ማመልከቻ ለካምፓኒው ባስገቡበት ቀን ይሆናል። የስራ ማመልከቻ ቀናቸውም ተመሳሳይ ከሆነ ደረጃቸው በልደት ቀን እና ወራቸው ይወሰናል።

7.02 ካምፓኒው የሲኒዮሪቲ ሊስት ለዩኒየኑ ለማቅረብ እና በተጨማሪም በፋብሪካው አንደኛ እና ሁለተኛ ፍሎሮች ላይ ሁሉም ተቀጣሪዎች ሊያገኙት በሚችሉበት ቦታ ላይ በየወሩ ለመለጠፍ ተስማምቷል። ተቀጣሪዎቹ የሚዘረዘሩት በሲኒዮሪቲ ከነዲፓርትመንታቸው (በጋራ ስምምነቱ **አንቀጽ** 5.09 ላይ በሚገኘው መሠረት) ይሆናል።

7.03 ሲኒዮሪቲ እንደተሰበረ እና ቅጥሩም እንደተቋረጠ የሚቆጠረው ተቀጣሪው፡

(1) በካምፓኒው ከተባረረ እና በእዚህ ስምምነት ላይ በተቀመጡት የቅሬታ እና የዳኝነት አሰራር ቅደም ተከተሎች አማካኝነት ወደ ስራው ካልተመለሰ፤

(2) በፈቃዱ ስራውን ከለቀቀ፤

(3) ከአስራ ሁለት (12) ወራት ለሚበልጥ ጊዜ በተከታታይ በሌይአፍ ከቆየ ወይም ከሌይአፍ እንዲመለስ ሲጠራ በ**አንቀጽ** 8 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልተመለሰ፤

(4) ተቀጣሪው ያለ አሳማኝ ምክንያት፣ የጽሑፍ ሊቭ ኦፍ አብሰንስ ሳይኖረው ከሦስት (3) የስራ ቀናት በላይ ከስራ ገበታው ላይ ከቀረ። ሆስፒታል መተኛት መይም ከካምፓኒው ጋር ለመገናኘት አለመቻል እንደ አሳማኝ ምክንያት ይቆጠራል፤

(5) ያለ አሳማኝ ምክንያት በተፈቀደለት ሊቭ ኦፍ አብሰንስ ማብቂያ ላይ ወደ ስራ ሳይመለስ ከቀረ። ሆስፒታል መተኛት መይም ከካምፓኒው ጋር ለመገናኘት አለመቻል እንደ አሳማኝ ምክንያት ይቆጠራል፤

(6) በሕመም ወይም ጉዳት ምክንያት ለሁለት (2) ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ካልሰራ፣ ነገር ግን በካምፓኒው እና ዩኒየኑ መካከል የጋራ ስምምነት ካለ የጊዜ ገደቡ ሊያጥር ወይም ሊረዝም ይችላል። በሕመም ወይም ጉዳት ከስራ የቀረ ተቀጣሪ ከመባረሩ በፊት ካምፓኒው እና ዩኒየኑ ተሰብስበው የባለጉዳዩ ተቀጣሪ ልዩ ሁኔታ ላይ ይወያያሉ። በእዚህ ሁኔታ ተቀጣሪው መባረሩ የሎንግ ተርም ዲስኦቢሊቲ (ኤል.ቲ.ዲ) ጥቅማ ጥቅም ከማግኘት አያግደውም። ሁለቱ ወገኖች በተቀጣሪው ስታተስ ላይ ለመስማማት ካልቻሉ ካምፓኒው ተቀጣሪውን የማባረር መብቱ ይጠበቅለታል። ዩኒየኑም የተቀጣሪውን መባረር ተገቢነት ላይ ቅሬታ የማቅረብ መብቱ ይጠበቅለታል። ተቀጣሪው ማንኛውም በካምፓኒው እና ዩኒየኑ መካከል መስማማት ላይ የተደረሰበት መባረር ፍትሓዊ ተደርጎ እንደሚወሰድ ይረዳል።

7.04 ተቀጣሪው ስራውን በብቃት የመወጣት ችሎታ እስካለው ድረስ የስራ እድገት፣ ሌይአፍ፣ የፈረቃ ምርጫ፣ ከሌይአፍ ተመልሶ የመጠራት፣ ከፉል-ታይም ወደ ፓርት-ታይም የመቀነስ፣ እና የቫኬሽን ፕሮግራምን የመምረጥ ጉዳዮች የሚወሰኑት በቀዳሚነት ሲኒዮሪቲን መሠረት በማድረግ ይሆናል።

7.05 በካምፓኒው ፈቃድ ወይም በካምፓኒው ትዕዛዝ የአንድ ተቀጣሪ ስታተስ ከፉል-ታይም ወደ ፓርት-ታይም ከተቀየረ የሲኒዮሪቲ ቀኑ ለመጨረሻ ጊዜ የተቀጠረበት ቀን ይሆናል።

የተቀላጠፈ የስራ ሂደትን ለማስቀጠል የአንድ ተቀጣሪ ስታተስ ከፉል-ታይም ወደ ፓርት-ታይም በሚቀየርበት ጊዜ ተቀጣሪው ወደፊት ለሚለቀቁ የፉል-ታይም የስራ መደቦች ለመቀጠር ከሌሎች ካምፓኒው ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ ከማውጣቱ በፊት ካመለከቱ ተቀጣሪዎች በፊት ቅድሚያ እንዲሰጠው መግባባት አለ።

7.06 የአንድ ተቀጣሪ ስታተስ ከፉል-ታይም ወደ ፓርት-ታይም ከመቀየሩ በፊት አንድ (1) ሳምንት አስቀድሞ ለማሳወቅ ካምፓኒው ተስማምቷል።

7.07 <u>ፓርት-ታይም</u>

ፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች ሲኒዮሪቲ የሚኖራቸው በፓርት-ታይም ሲኒዮሪቲ ዝርዝር ውስጥ ብቻ ሲሆን ፉል-ታይም ተቀጣሪዎች ግን በፓርት-ታይም ተቀጣሪዎችም ላይ ሲኒዮሪቲ ይኖራቸዋል። ለፕሮግራም አወጣጥ ሲባል የፓርት-ታይም ሰራተኞች ፕሮግራም የሚወጣላቸው ከፉል-ታይም ሰራተኞች በተናጠል ነው። ከላይ የተቀመጠው ፕሮግራም የሚወጣው በዲፓርትመንት እና በሲኒዮሪቲ ይሆናል። ይህም የሚሆነው ተቀጣሪው መደበኛ የስራ ኃላፊነቶቹን የመወጣት ብቃት እስካለው ድረስ ብቻ ነው። ካምፓኒው ከላይ እንደተጠቆመው አድርጎ የፓርት-ታይም ተቀጣሪዎችን ፕሮግራም በማውጣት ሲኒየር የፓርት-ታይም ሰራተኞች የሳምንቱ ፕሮግራም በሚወጣበት ጊዜ በቂ ሰዓታት ክፍት ሁነው ከተገኙ እስከ አርባ (40) ሰዓታት
ድረስ ፕሮግራም እንዲያዝላቸው ለማስቻል ተስማምቷል።

<u>አንቀጽ 8</u> <u>ሌይኦፍ እና ከሌይኦፍ መመለስ</u>

8.01 <u>ሌይኦፍ ማስታወቂያ / ትርጉም</u>

(a) በእዚህ **አንቀጽ** ላይ ሌይኦፍ ማለት ለሰባት (7) ወይም ከዛ በላይ ተከታታይ ቀናት የሚደረግ ሌይኦፍ ተብሎ ይተረጎማል።

(b) ከስድስት (6) ወራት የሚያንስ ሲኒዮሪቲ ያላቸው ተቀጣሪዎች ሌይኦፍ ከመደረጋቸው ሁለት (2) የስራ ቀናት አስቀድሞ እንዲያሳውቃቸው ካምፓኒው ተስማምቷል። የስድስት (6) ወራት ወይም ከዚያ በላይ ሲኒዮሪቲ ያላቸው ተቀጣሪዎች ሌይኦፍ ከመደረጋቸው በፊት ለእያንዳንዱ የአገልግሎት ዓመት ሁለት (2) የስራ ቀናት አስቀድሞ እስከ አምስት (5) የስራ ቀናት ድረስ በጽሑፍ እንዲያሳውቃቸው ካምፓኒው ተስማምቷል።

8.02 ሌይኦፍ እና ከሌይኦፍ ተመልሶ መጠራት በሲኒዮሪቲ ላይ ተመሥርቶ የሚደረግ ይሆናል። ማለትም መጨረሻ የተቀጠረው ሰራተኛ ቅድሚያ ሌይኦፍ የሚደረግ እና መጨረሻ ተመልሶ የሚጠራ ይሆናል። ይህ የሚሆነው ግን ሲኒየሩ ተቀጣሪ ስራውን በብቃት የመወጣት ችሎታው ካለው ወይም በተፈለገው ፍጥነት መልመድ የሚችል ከሆነ ብቻ ነው። በእንደዚህ መልኩ የመልመጃ ዕድል የተሰጣቸው ሰራተኞች የተመደበላቸውን ክፍፍል በአጥጋቢ ሁኔታ የመስራት ብቃት እንዳላቸው በአንድ (1) ሳምንት ጊዜ ውስጥ ማሳየት ይኖርባቸዋል።

ከላይ በተቀመጠው መስፈርት የፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች ከፉል-ታይም ተቀጣሪዎች አስቀድመው ሌይኦፍ የሚደረጉ ይሆናል።

ከላይ በተቀመጠው መስፈርት የፉል-ታይም ተቀጣሪዎች ከፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች አስቀድመው ከሌይኦፍ ተመልሰው የሚጠሩ ይሆናል።

8.03 በቢዝነስ መቀነስ ምክንያት ፉል-ታይም ተቀጣሪ ሌይኦፍ ቢደረግ ተቀጣሪው በሌላ ዲፓርትመንት ተመሳሳይ ክፍፍል ላይ የሚገኝ እጅግ ጁኒየሩን የፉል-ታይም ተቀጣሪ ማፈናቀል እና በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ስራውን በብቃት የመስራት ችሎታ እንዳለው በማሳየት ያንን ቦታ መውሰድ ይችላል። ነገር ግን በእዚህ አሰራር ዲፖርትመንቱ በቋሚነት በሚዘጋበት ወይም ስራው ከአሁን በኋላ አያስፈልግም በሚባልበት ጊዜ

ቀነ ገደቡ አንድ ሳምንት መሆኑ ቀርቶ ወደ አስር (10) የስራ ቀናት ይለወጣል። ከላይ በተቀመጠው መሠረት አንድ ጁኒየር የፉል-ታይም ተቀጣሪ በሌላ ሲኒየር ተቀጣሪ ሲፈናቀል ተፈናቃዩ በሌላ ዲፓርትመንት ውስጥ በራሱ ክፍፍል ፓርት-ታይም ሆኖ የመቀጠል ዕድል ይሰጠዋል። ይህም እጅግ ጁኒየሩን ተቀጣሪ በማፈናቀል፣ እጅግ ጁኒየሩን የፓርት-ታይም ተቀጣሪ በማፈናቀል፣ ወይም እጅግ ጁኒየሩን ዝቅ ባለ የክፍያ ሬት ውስጥ የሚገኝ የፉል-ታይም ተቀጣሪ በማፈናቀል ሊሆን ይችላል። አልያም የተቀጣሪው ምርጫ ከሆነ ሌይኦፍ ሊደረግ ይችላል።

8.04 ማንኛውም ተቀጣሪ መጨረሻ በሚታወቅበት አድራሻው ወደ ስራው እንዲመለስ መልዕክት ተልኮበት በአምስት (5) የካላንደር ቀናት ውስጥ ያለ ምንም አሳማኝ ምክንያት ካልተመለሰ በፍቃዱ ከስራው እንደለቀቀ ተቆጥሮ ያለው የሲኒዮሪቲ መብት ይቋረጣል። እንደዚህ አይነት መልዕክት ለተቀጣሪው ሲላክ በተመሳሳይ ጊዜ የመልዕክቱ ቅጂ ለዩኒየኑ ሊላክ ይገባል።

አንቀጽ 9 ክፍት የስራ ቦታዎች / የክፍፍል ማስታወቂያዎች

9.01 የጄነራል ሌበር አንድ (ጂ.ኤል.1) ክፍፍል ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያዎች ዲፓርትመንቱን እና የፕሮግራም ሰዓታቱን እንዲጠቁሙ ተደርገው በየሳምንቱ የሚዘረዘሩ እና አፕዴት የሚደረጉ ይሆናል። ተቀጣሪዎች ለጄነራል ሌበር አንድ (ጂ.ኤል.1) ክፍፍል ክፍት የስራ ቦታ ካመለከቱ ሊስቱ በሚቀጥለው ሳምንት አፕዴት ከመደረጉ በፊት መጠይቃቸውን ማስገባት ይኖርባቸዋል። በመቀጠልም ካምፓኒው ስራውን የመስራት ብቃታቸው ላይ ተመርኩዞ ለቀጣዩ ክፍት የስራ መደብ የመቀጠር ዕድሉን ይሰጣቸዋል። ከላይ ለተጠቆመው የስራ መደብ አመልክተው ያለፉ ተቀጣሪዎች በስራ መደቡ ቢያንስ ለስድስት (6) ወራት ሳያገለግሉ ለሌላ ጄነራል ሌበር አንድ (ጂ.ኤል.1) ክፍፍል ክፍት የስራ ቦታ ማመልከት አይችሉም።

9.02 አዳዲስ ክፍፍሎች እና አሁን ባሉት ክፍፍሎች ውስጥ የሚመጡ ቋሚ ክፍት የስራ ቦታዎች ለሦስት (3) የስራ ቀናት ቡሌቲን ቦርድ ላይ
አዲሶቹ ክፍፍሎች ወይም ክፍት የስራ መደቦች በተፈጠሩበት በሰባት (7) የስራ ቀናት ውስጥ መለጠፍ ይኖርባቸዋል። ክፍፍሎቹ ወይም ክፍት የስራ ቦታዎቹ የሦስት ቀን መለጠፉ ባለቀ በአስር (10) የስራ ቀናት ውስጥ መሞላት ይኖርባቸዋል። ይህም የተቀሩት ተቀጣሪዎች የሚያስፈልገውን ስራ በአጥጋቢ እና ቅልጥፍና በተሞላበት ሁኔታ መስራት እስከሚችሉ ድረስ ማለት ነው። ያም ሆነ ይህ ግን ስራውን ያሸነፈው ተቀጣሪ የብቃት ማረጋገጫ ወቅት በሠላሳ (30) የስራ ቀናት ውስጥ መጀመር ይኖርበታል።

የመወዳደር ፍላጎት ያላቸው ተቀጣሪዎች ማስታወቂያው ላይ መፈረም ይኖርባቸዋል። ተቀጣሪዎች ስራውን ላለመቀበል መምረጥ የሚችሉት በካላንደር ዓመት ውስጥ ለሁለት (2) ጊዜ ብቻ ነው። ስራውን ለመቀበል የመረጡ ተቀጣሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ሂደቱን ከመጀመራቸው በፊት የስራ መደቡን የመመልከት ዕድሉ ሊሰጣቸው ይገባል። የብቃት ማረጋገጫ ሂደቱን ላለመጀመር ከወሰኑ ወደ ቀድሞ የስራ መደባቸው እንዲመለሱ ተደርጎ ይህ እንደ ስራውን ላለመቀበል እንደመምረጥ ይቆጠራል። የብቃት ማረጋገጫ ሂደቱን ለመጀመር ከወሰኑ ለሚቀጥሉት ዘጠኝ (9) ወራት ማንኛቸውንም ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያዎች ከመፈረም ይታገዳሉ።

ካምፓኒው የ**ክፍፍል** ማስታወቂያዎችን፣ የአመልካቾችን ዝርዝር እና **ክፍት ስራውን** ያሸነፉትን ግለሰቦች ስም ዝርዝር ለዩኒየኑ ዋና አስተናባሪ ያቀርባል። የአሸናፊው አመልካች ስም ቡሌቲን ቦርዱ ላይ ይለጠፋል።

ጊዜያዊ ክፍት የስራ መደቦችን **ለስድስት (6) ወር ወይም ከዚያ በታች**

ለሚሆን ጊዜ በመሙላት የሚፈጠሩ ክፍት የስራ ቦታዎች በማኔጅመንት አማካኝነት ሲኒየር ብቁ ተቀጣሪዎች የክፍፍሉን ክፍት ቦታ እንዲሞሉ ተደርጎ የሚሞሉ ይሆናሉ። **ርዝማኔያቸው ከስድስት (6) ወር በላይ የሆኑ ጊዜያዊ ክፍት የስራ ቦታዎች ማስታወቂያ ሊወጣላቸው ይገባል።**

የ**ክፍፍል** ማስታወቂያዎች ክፍፍሉን፣ የክፍያ ሬቱን፣ ዲፓርትመንቱን፣ በዲፓርትመንቱ ውስጥ ያሉት ክፍፍሎች ውስጥ ያሉትን ሁሉም የስራ አይነቶችን፣ የስራ ሰዓታትን፣ ማለትም የስራ መጀመሪያ እና ማብቂያ ሰዓታትን ከአጠቃላይ የዲፓርትመንቱ የስራ ሁኔታዎች ጋር ካምፓኒው እና ዩኒየኑ በተስማሙበት መሰረት አካትተው ሊይዙ ይገባል።

በካምፓኒው የተወገዱት ስኬታማ አመልካቾች በየካላንደር ዓመቱ አንዴ ለዘጠኝ (9) ወሩ እገዳ አይጋለጡም። ለጊዜያዊ ክፍት መደብ ያለፉ አመልካቾች የቀድሞው ሰራተኛ ወደ ስራው እስኪመለስ ድረስ በመደቡ ላይ መቆየት ይኖርባቸዋል። አልያም ካምፓኒው ካጸደቀው አስቀድመው ሊለቀቁ ይችላሉ።

በቅሬታ ሂደት አንድ ተቀጣሪ ወደ ስራው ቢመለስ በጋራ ስምምነት ካልሆነ በስተቀር ሲባረር ወደነበረበት የስራ መደብ ይመለሳል።

በሰራተኞች ካሳ ወይም በሳምንታዊ ኢንዴምኒቲ ወይም በወደ ስራ መመለሻ አከሞዴሽን ላይ በመሆናቸው የክፍቱን የስራ ቦታ ኃላፊነቶች እንዳይሰሩ ክፍቱ የስራ ቦታ ላይ ሰራተኛ ከተመደበበት ቀን አንስቶ ከሃያ አምስት (25) ለሚበልጡ ቀናት የሚያግዳቸው ተቀጣሪዎች የስራ ቦታው ምደባ በሚደረግበት ጊዜ ዕድሉ እንዲያልፋቸው ይደረጋል።

9.03 በእዚህ **አንቀጽ** ለተመለከተው ብቁ ለመሆን አንድ ተቀጣሪ ከምክንያታዊ ርዝማኔ ካለው የልምምድ ወቅት በኋላ የስራውን መደበኛ ኃላፊነቶች በብቃት የመወጣት ችሎታ ሊኖረው ይገባል። ይህም የሚፈተነው ካምፓኒው ለሲኒየር ተቀጣሪዎች ቢበዛ የሚከተለውን ርዝማኔ ያላቸውን ተከታታይ ስልጠናዎች/ብቃት ማረጋገጫዎች ሲሰጥ ይሆናል፡ ጄነራል ሌበር - አምስት (5) የተጠናቀቁ የስራ ቀናት፤ ሴሚ-ስኪልድ - አስር (10) የተጠናቀቁ የስራ ቀናት እና ስኪልድ - አስራ አምስት (15) የተጠናቀቁ የስራ ቀናት ተቀጣሪው ላመለከተው የስራ መደብ የሚመጥን እውቀት፣ ስልጠና፣ ችሎታ እና አካላዊ ብቃት እንዳለው ማሳያ ካምፓኒው ለተቀጣሪዎቹ ቢበዛ የሃያ (20) ቀናት ርዝማኔ ያለው ተከታታይ የስልጠና/ብቃት ማረጋገጫ ወቅት ለጥገና ረዳቶች እና ሉብሪኬተሮች እንዲሁም ቢበዛ ሦስት (3) ወር ርዝማኔ ያለው ደግሞ ከሌላ ትሬድ ክፍፍል ለሚመጡ ተቀጣሪዎች ይሰጣል።

ከላይ የተጠቆሙት የስልጠና/ብቃት ማረጋገጫ ወቅቶች ካምፓኒው አንድ ተቀጣሪ በሂደት ስራውን ያለ መመሪያም ሆነ እርዳታ ለመስራት የሚችል መሆን አለመሆኑን ለመመልከት የሚሰጠው ጊዜ እንደሆነ ካምፓኒው ይስማማል። **ለሴሚ-ስኪልድ ወይም ስኪልድ የስራ መደብ ለማለፍ እየሞከረ ያለ ተቀጣሪ ብቁነቱን ለማሳየት ተጨማሪ ጊዜ በሚያስፈልገው ጊዜ ለዩኒየኑ ካሳወቀ በኋላ እና ሁለቱም ወገኖች የጋራ ስምምነት ላይ ከደረሱ በኋላ በቅደም ተከተል የአስር (10) ወይም የአስራ አምስት (15) ቀናት ማራዘሚያ ይፈቀድለታል።**

የተመረጠው ተቀጣሪ በተባለው ክፍፍል ውስጥ ያለውን ስራ ባለፉት ሃያ አራት (24) ወራት ውስጥ ሰርቶ ከነበር እና አሁንም የተባለውን ስራ መስራት ከቻለ የመሞከሪያ ወቅት አስፈላጊ አይሆንም።

9.04 የፓርት-ታይም ተቀጣሪ ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሲከሰት የፉል-ታይም ተቀጣሪ ሊሆን ይችላል፡

(a) ከላይ በተቀመጠው 9.01 መሠረት የፓርት-ታይም ተቀጣሪው ለፉል-ታይም መደብ አመልክቶ ስራው ከተሰጠው፤ (ካምፓኒውእና ዩኒየኑ ፉል-ታይም ተቀጣሪዎች ከፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች አስቀድመው ለፉል-ታይም ስራ መደቦች እንደሚመረጡ ይስማማሉ) ወይም

(b) ፓርት-ታይም ተቀጣሪው በሦስት (3) የካላንደር ወራት ጊዜ ውስጥ ከፉል-ታይም ተቀጣሪ እኩል ሰዓታትን ሰርቶ ከሆነ እንደ ፉል-ታይም ተቀጣሪ ተቆጥሮ አንድ የፉል-ታይም ተቀጣሪ በጋራ ድርድር ስምምነቱ ውስጥ በሚገኘው ክፍፍል መሠረት የሚከፈለውን ክፍያ እና የሚያገኘውን ጥቅማ ጥቅም እንዲያገኝ ይደረጋል። ይህ ደንብ ተፈጻሚ የማይሆነው የፓርት-ታይም ሰራተኛው ከስድስት (6) የካላንደር ወራት ለማይበልጥ ጊዜ ብቻ ሌላ ተቀጣሪን በቫኬሽን፣ በሊቭ ኦፍ አብሰንስ፣ በሕመም ወይም በጉዳት፣ ወይም በሰራተኞች ካሳ ምክንያት ሊተካ እንደሆነ ተነግሮት ከሆነ ነው።

9.05 አዲስ ተቀጣሪዎች በአንቀጽ 9.03 የተቀመጠው የብቃት ማረጋገጫ ወቅት ተፈፃሚ ይደረግባቸዋል። አዲስ ተቀጣሪዎች በፕሮቤሽን ወቅታቸው እያሉ ለፈለጉበት የስራ መደብ እንዲወዳደሩ እና እንዲመደቡ አንድ ጊዜ ብቻ ይፈቀድላቸዋል።

አዲስ ተቀጣሪ ሰራተኛ በብቃት ማረጋገጫው ወቅት ለመጀመሪያ ምደባው ማለፍ ቢያቅተው ለዩኒየኑ ካሳወቀ በኋላ እና ሁለቱም ወገኖች የጋራ ስምምነት ላይ ከደረሱ በኋላ በቅደም ተከተል የአስር (10) ወይም የአስራ አምስት (15) ቀናት ማራዘሚያ ይፈቀድለታል። በዝግ ማስታወቂያ የተቀጠረ ሰራተኛ በብቃት ማረጋገጫው ማብቂያ ላይ ከፍ ለሚለው ስኪል መደብ ማለፍ ቢያቅተው የሚቻል ከሆነ ካምፓኒው ሰራተኛውን በፋብሪካው ውስጥ ወደሚገኝ ክፍት የጄነራል 1 መደብ ያዘዋውረዋል።

<u>አንቀጽ 10 በካታጎሪ ውስጥ የሚደረጉ የስራ ሮቴሽኖች</u>

10.01 የስራ ሮቴሽን ኮሚቴው በእያንዳንዱ **ክፍፍል** ውስጥ ያሉትን የስራ መደቦች ለይቶ ያስቀምጣል። ከዚያም ተቀጣሪዎች **በክፍፍላቸው** ውስጥ ባሉት ስራዎች ሮቴት እንዲያደርጉ ይፈቀድላቸዋል። ይህም የተሻለ ምርታማነትን፣ የስራ ላይ ደህንነትን፣ እና የስራ እርካታን ለማምጣት ሲባል የሚደረግ ነው። የስራ ሮቴሽን ኮሚቴው የሚመለከታቸውን ተቀጣሪዎች በማማከር “የስራ ባለቤትነት የሚባል ነገር የለም” በሚለው መርህ ላይ የተመሰረተ የስራ ሮቴሽን ለማውጣት ተስማምቷል። የጊዜው ርዝማኔ የስራ ሮቴሽንን አላማ ባልሳተ መልኩ በስራ ሮቴሽን ኮሚቴው የሚወሰን ይሆናል።

ካምፓኒው በዩኒየኑ የተመረጡ አራት (4) ተቀጣሪዎችን (ከአራቱ አንዱ የፉል-ታይም የዩኒየን ተወካይ ሊሆን ይችላል) እና በማኔጅመንት የተመደቡ አራት (4) የካምፓኒው ተወካዮችን የሚይዝ የስራ ሮቴሽን ኮሚቴ ለማዋቀር ተስማምቷል።

ለሮቴሽን የሚሆኑትን የእያንዳንዱ ክፍፍል የስራ መደቦች በሚለይበት ጊዜ ኮሚቴው የተቀጣሪዎቹን ደህንነት እና ኤርጎኖሚክ ፍላጎት፣ ሌሎች ስራዎችን የመስራት ችሎታቸውን፣ እና ከዚህ በፊት መሰል ስራ የሰሩበትን የጊዜ መጠን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል። ካምፓኒው ሁሉም ስራዎች ግዴታ ሮቴት መደረግ ሊኖርባቸው እንደማይችል ይስማማል።

ይህ ኮሚቴ ሮቴሽን በደንብ ተተርጉሞ እስኪተገበር ድረስ በሚኖረው ጊዜ ቢያንስ በካላንደር ወር አንዴ ሊሰበሰብ ይገባል። ከዚያም የሮቴሽን ሲስተሙ በሚገባው መልኩ እየሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲባል የመሰብሰቢያው ጊዜ ማስተካከያ ይደረግለታል። የዩኒየኑ ፕሬዚዳንት እና ዋናው ገንዘብ ያዥ በኮሚቴው ሊቀረፉ ያልቻሉ ችግሮችን በተመለከተ ከፋብሪካው ማናጀር እና የሰው ሃብት ሲኒየር ማናጀር ጋር ተባብሮ ለመስራት ተስማምተዋል።

ዩኒየኑ በፋብሪካው ዲፓርትመንቶች ውስጥ ያሉ ሮቴሽኖችን የሚመለከቱ ዶክመንቶችን በጠየቀ ጊዜ የሚቀርቡለት ይሆናል።

<u>አንቀጽ 11 ጄነራል በዓላት</u>

11.01 (a) ካምፓኒው ለሚከተሉት አስራ አንድ (11) ክፍያ የሚታሰብላቸው ጄነራል በዓላት የስምንት (8) ሰዓታት ክፍያ ለሁሉም ተቀጣሪዎቹ በየመደበኛ የክፍያ ሬታቸው ለመክፈል ተስማምቷል፡

ኒው ይርስ ዴይ	ሌበር ዴይ
ሉዊ ሪዬል ዴይ	ታንክስጊቪንግ ዴይ
ጉድ ፍራይዴይ	ሪሜምብራንስ ዴይ
ቪክቶሪያ ዴይ	ክሪስማስ ዴይ
ካናዳ ዴይ	ቦክሲንግ ዴይ
	ሲቪክ
ሆሊዴይ	

እና ሌሎች ማንኛቸውም በፌደራልም ሆነ ክልላዊ መስተዳድር የታወጁ ቀናት የአስር (10) ወይም አስራ ሁለት (12) ሰዓታት ፈረቃዎችን ወይም ተከታታይ አቨርታይም ለሚሰሩ ተቀጣሪዎች ባለፈው የአራት (4) ሳምንት ወቅት የነበራቸው አማካይ የፈረቃ ርዝማኔ ይሆናል።

(b) ከላይ በ11.01 (ሀ) የተጠቆሙት ጄነራል በዓላት በእዚህ የጋራ ስምምነት የአገልግሎት ዘመን ውስጥ የሚከበሩት **በሚያርፉበት የካላንደር ቀን** ይሆናል።

አንድ ጄነራል በዓል አንድ ተቀጣሪ ፕሮግራም በተያዘለት የስራ ሳምንት ውስጥ በስራ ቀን ላይ ካላረፈ **የሚከተለው ተግባራዊ ይሆናል**፡

- **ከሰኞ - አርብ ለሚሰሩ ተቀጣሪዎች፡**

    - **ቅዳሜ ላይ የሚያርፉ ጄነራል በዓላት በበዓሉ ዋዜማ ባለው ዕለተ አርብ ይታሰባሉ። ያ አርብም በዓል ከሆነ አንድ ቀን አስቀድሞ ያለው ዕለተ ሐሙስ ላይ ጄነራል በዓሉ ይታሰባል።**

    - **እሁድ ላይ የሚያርፉ ጄነራል በዓላት በበዓሉ ማግስት ባለው ዕለተ ሰኞ ይታሰባሉ። ያ ሰኞም በዓል ከሆነ አንድ ቀን ቀጥሎ ያለው ዕለተ ማክሰኞ ላይ ጄነራል በዓሉ ይታሰባል።**

- **ከሰኞ - አርብ ለማይሰሩ ተቀጣሪዎች፡**

    - እንደየምርጫው ተጨማሪ የስምንት (8) ሰዓታት ክፍያ፣ **(መደበኛ ፈረቃቸው አስር (10) ሰዓታት ለሆኑት የአስር (10) ሰዓታት ክፍያ፣ መደበኛ ፈረቃቸው አስራ ሁለት (12) ሰዓታት ለሆኑት የአስራ ሁለት** (12) ሰዓታት ክፍያ)፣ ወይም **ከሚቀጥሉት ሠላሳ (30) የካላንደር ቀናት** ውስጥ ተቀጣሪው እና ማኔጅመንት በተስማሙበት በአንዱ ክፍያ የሚታሰብለት የእረፍት ቀን መውሰድ ይችላል። ይህ የሚሆነው ግን ተቀጣሪው በአንቀጽ 11.04 መሠረት ብቁ እስከሆነ ብቻ ነው።

(c) ከእሁድ - አርብ እንዲሰሩ ፕሮግራም የተያዘላቸው ተቀጣሪዎች ጄነራል በዓሉ በዕለተ ሰኞ የሚያርፍ ከሆነ ለተቀጣሪዎቹ በዓሉ በዋዜማው ዕለተ እሁድ እንደሚያርፍ ተደርጎ ይታሰብላቸዋል።

11.02 የፉል-ታይም ወይም የፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች ለጄነራል በዓላት ክፍያ የሚሰጣቸው ኢንዲሰሩ ፕሮግራም ተይዞላቸው በነበረው የበዓሉ ዋዜማ ወይም ማግስት ያለ በህክምና ሰነድ የተረጋገጠ አሳማኝ ሕመም በገዛ ፈቃዳቸው ቀርተው ካልሆነ ብቻ ነው።

ካምፓኒውን ጠይቆ እና ተፈቅዶለት በሊቭ ኦፍ አብሰንስ ላይ ያለ ተቀጣሪ እንዲሰራ ፕሮግራም ተይዞለት በነበረው የበዓሉ ዋዜማም፣ የበዓሉ ማግስትም ላይ በስራ ገበታው ላይ ካልተገኘ የጄነራል በዓል ክፍያ አይከፈለውም። በተፈቀደለት ሊቭ ላይ ያለ ተቀጣሪ የጄነራል በዓል ክፍያ ስሌት ከዚህ በታች አንቀጽ 11.04 ላይ በተቀመጠው አሰራር መሠረት ይሆናል።

በሰምንታዊ ኢንዴምኒቲ ጥቅማ ጥቅም ወይም በሰራተኞች ካሳ፣ ወይም በሕመም ቀናት፣ ወይም ሌይኦፍ በመደረግ ምክንያት ለጄነራል በዓል ጥቅማ ጥቅም የሚያገኝ ማንኛውም ተቀጣሪ የጄነራል በዓላት ክፍያ አይገባውም።

11.03 ብቁ የሆኑ የፉል-ታይም ሰራተኞች በ11.01 በተቀመጠው መሠረት ምንም አይነት ቅነሳ በጄነራል በዓላት ክፍያቸው ላይ ሊደረግባቸው አይገባም፤ በእዚህ ስምምነት 5.03 እና 5.04 መሠረትም ሊከፈላቸው ይገባል።

11.04 አንድ ጄነራል በዓል ፕሮግራም ተይዞለት በነበረ መደበኛ ዕለት ላይ ሲያርፍ የፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች ላለፉት አራት (4) ሳምንታት በአማካይ በሰሩበት ዕለታዊ ሰዓታት ርዝመት መሠረት ካሳ ይከፈላቸዋል።

በዓሉ ስራ በሌለበት ቀን ካረፈ ብቁ የሆኑ የፓርት-ታይም ሰራተኞች ከበዓሉ በፊት የነበሩት የአራት (4) ሳምንታት ደመወዛቸውን አምስት (5%) ፐርሰንት አቨርታይምን ሳያጠቃልል የሚቀበሉ ይሆናል።

<u>አንቀጽ 12 ደመወዝ</u>

12.01 በእዚህ ስምምነት ላይ የተጠቃለሉት ተቀጣሪዎች ሚኒመም የሰዓት ደመወዝ ሬቶች በስምምነቱ አፔንዲክስ “B” ላይ እንደተቀመጠው ይሆናል። በአፔንዲክስ “B” ላይ የተቀመጡት የክፍያ ሬቶች ለክፍፍሎቹ ተግባራዊ የሚደረጉ ሚኒመም ሬቶች ናቸው። ካምፓኒው በአንድ ክፍፍል ውስጥ ለሚገኙ ተቀጣሪዎች ከክፍፍሉ ሬት አስበልጦ የመክፈል መብቱ የተጠበቀ ነው።

12.02 <u>በስራ ላይ የሚከሰት ጉዳት</u>

በፋብሪካው ውስጥ በመስራት ላይ እያለ የተጎዳ ተቀጣሪ ሊሰራባቸው ለነበሩት አደጋው በደረሰበት ቀን ለጠፉት የስራ ሰዓታት የክፍያ ቅነሳ አይደረግበትም። የተጎዳው ተቀጣሪ እንደ ፈረቃው ርዝማኔ ስምንት (8)፣ አስር (10) ወይም አስራ ሁለት (12) ሰዓታት በተጎዳበት ጊዜ እየሰራ በነበረበት የክፍፍል ሬት ይከፈለዋል። ተቀጣሪዎች በማኔጅመንት ከተጠየቁ ለፈረቃው ክፍያ መቀበያ እንዲያገለግል ከሐኪሙ የተጻፈ የሕክምና ማረጋገጫ እና ጉዳቱ ወደ ስራ ከመመለስ እንደሚያግድ ማስረጃ በማጻፍ ማቅረብ ግድ ይላቸዋል።

<u>አንቀጽ 13 ፕሪሚየም ክፍያዎች</u>

13.01 <u>የሊድ ሃንድ ፕሪሚየም</u>

በማኔጅመንት እንደ ሊድ ሃንድ የተመደበ ተቀጣሪ እንደ ሊድ ሃንድ ለሰራባቸው ሰዓታት በሙሉ በሰዓት ሰባ አምስት (75¢) ሳንቲም ሊከፈለው ይገባል። ከሃያ አምስት (25) ተቀጣሪዎች በላይ የሚይዙ ዲፓርትመንቶች በየፈረቃው አንድ ሊድ ሃንድ ይኖራቸዋል።

13.02 **<u>ኮርፖሬት አሰልጣኝ</u>**

በማኔጅመንት እንደ ኮርፖሬት አሰልጣኝ የተመደበ ተቀጣሪ እንደ ኮርፖሬት አሰልጣኝ ለሰራባቸው ሰዓታት በሙሉ በሰዓት ተጨማሪ ሃምሳ (50¢) ሳንቲም ሊከፈለው ይገባል። ብቁ ለመሆን አንድ ተቀጣሪ ሁሉንም ስራዎች የመስራት ችሎታ ሊኖረው ይገባል። ሁሉም የኮርፖሬት አሰልጣኝ መደቦች ፍላጎቱ ያላቸው ተቀጣሪዎች ያመለክቱ ዘንድ ይለጠፋሉ። ምደባው ግን በማኔጅመንት የሚፈፀም ይሆናል።

ይህ ፕሪሚየም ካምፓኒው ያዘዛቸውን ስልጠናዎች እንዲሰጡ ለተመደቡ ተቀጣሪዎችም ተፈፃሚ ይሆናል። እነዚህ የስልጠና ዕድሎች በዲፓርትመንቱ እና በፈረቃው ላይ ለሚገኙ ሲኒየር እና ብቁ የሆኑ ተቀጣሪዎች ይቀርባሉ።

13.03 **<u>ኦፍሺፍት ፕሪሚየም</u>**

ኦፍሺፍት ማለት የአንድ ተቀጣሪ አብዛኞቹ የፈረቃው ሰዓታት ከ 3፡00 ፒ.ኤም. እስከ 7፡00 ኤ.ኤም. በላው ጊዜ ውስጥ የሚያርፉበት ፈረቃ ተብሎ ይተረጎማል። ካምፓኒው ለማንኛውም ኦፍሺፍት ለሚሰራ ተቀጣሪ ከመደበኛ የክፍያ ሬቱ በተጨማሪ በሰዓት ሃምሳ አምስት (55¢) ሳንቲም ለመክፈል እና ከጃኒዋሪ 13 2020 ጀምሮ ወደ ስድሳ (60) ሳንቲም፣ ከጃኒዋሪ 1 2022 ጀምሮ ደግሞ ወደ ስድሳ አምስት (65) ሳንቲም ለማሳደግ ተስማምቷል።

<u>አንቀጽ 14</u> **<u>ክፍያ የማይቋረጥባቸው ቫኬሽኖች</u>**

14.01 ማንኛውም ተቀጣሪ ክፍያ ለማይቋረጥባቸው ቫኬሽኖች ብቁ ይሆን ዘንድ ሊያሟላቸው የሚገቡት የቫኬሽን መስፈርቶች በተከታታይ የአስራ ሁለት (12) ወራት ጊዜ ውስጥ ስራ የቀረባቸው ቀናት ከሠላሳ (30) አለማለፍ፣ የቀረባቸው ሲባል ግን የማያካትታቸው፡

(1) የቫኬሽኑን ወቅት

(2) ከስራ እንዲቀር ተቀጣሪው ከካምፓኒው ስልጣን ያገኘባቸው ወቆች (ዩኒየን ሊቭ ጨምሮ)፤

(3) ተቀጣሪው በ ደብሊው.ሲ.ቢ. ላይ ወይም በ ሾርት ተርም ዲሰኝቢሊቲ ላይ የነበረባቸው ጊዜያት፤

ከላይ በተቀመጠው መሠረት አንድ የፉል-ታይም ተቀጣሪ ክፍያ ለማይቋረጥበት ቫኬሽን ብቁ ሳይሆን ከቀረ በተፈቀደለት የቫኬሽን ወቅት ሊያገኘው የሚችለውን የቫኬሽን አላዋንስ ያልተከፈለበት የአጠቃላይ ደመወዙን ሁለት (2%) ፐርሰንት እንደ ቫኬሽን ክፍያ የሚቀበል ይሆናል።

14.02 ኤፕሪል 1 ሲደርስ ከአንድ (1) ዓመት የሚያንስ የፉል-ታይም ሲኒዮሪቲ የሚኖራቸው የፉል-ታይም ተቀጣሪዎች በቅጥር ጊዜያቸው ያገኙትን እስከ ኤፕሪል 1 የቫኬሽን አላዋንስ ያልተከፈለበት አጠቃላይ ደመወዝ አራት (4%) ፐርሰንት

የሚቀበሉ ይሆናል። እነዚህ ተቀጣሪዎች ከካምፓኒው ጋር የጋራ ስምምነት ላይ ካልደረሱ በስተቀር ለቫኬሽን ሲባል የእረፍት ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል። ይህም ክፍያ የማይታሰብለት እና እስከ ሁለት (2) ተከታታይ ሳምንታት ከኤፕሪል 1 እስከ ሴፕቴምበር 30 ካሉት ቀናት ውጪ ሊወሰድ የሚችል ነው።

14.03 በፉል-ታይም ሲኒዮሪቲ ላይ የተመሠረተ የፉል-ታይም ተቀጣሪዎች የቫኬሽን መብት ከታች በ14.19 ከተገለፀው በስተቀር እንደሚከተለው ይሆናል (ፓርት-ታይም ሰራተኞች ወደ ፉል-ታይም ሲሄዱ ለቫኬሽን እንዲያገለግል ብቻ የ2000 ሰዓታት ስራ ወይም ክፍያን የሚያክል የአንድ አመት ሲኒዮሪቲ ከሚሰጣቸው በስተቀር)፡

አንድ (1) ወይም ከዚያ በላይ ዓመታት ከኤፕሪል 1 በፊት - ክፍያ የሚታሰብለት የሁለት (2) ሳምንታት ቫኬሽን፤ አምስት (5) ወይም ከዚያ በላይ ዓመታት ከኤፕሪል 1 በፊት - ክፍያ የሚታሰብለት የሦስት (3) ሳምንታት ቫኬሽን፤ አስር (10) ወይም ከዚያ በላይ ዓመታት ከኤፕሪል 1 በፊት - ክፍያ የሚታሰብለት የአራት (4) ሳምንታት ቫኬሽን፤ አስራ ዘጠኝ (19) ወይም ከዚያ በላይ ዓመታት ከኤፕሪል 1 በፊት - ክፍያ የሚታሰብለት የአምስት (5) ሳምንታት ቫኬሽን።

14.04 ባለፉት አስር (10) ዓመታት ውስጥ የአምስት ዓመታት የቅጥር ርዝማኔ ያላቸው ተቀጣሪዎች ከመጨረሻው የቅጥር ቀናቸው አንስተው የአንድ (1) ዓመት ፉል-ታይም ሲኒዮሪቲ ሲያጠናቅቁ ክፍያ የሚታሰብለት የሦስት (3) ሳምንታት ቫኬሽን ሊያገኙ ይችላሉ።

14.05 የፉል-ታይም ተቀጣሪዎች ከጠየቁ እስከ ሦስት (3) ሳምንታት ድረስ ቫኬሽናቸውን ከኤፕሪል 1 እስከ ሴፕቴምበር 30 አከታትለው መጠቀም ይችላሉ (የአምስት (5) ሳምንታት ዓመታዊ ቫኬሽን ያላቸው ደግሞ እስከ አራት (4) ሳምንታት ድረስ አከታትለው መጠቀም ይችላሉ)። ይህ የሚሆነው በ14.06 እና 14.07 የተቀመጡት ካልሆኑ በስተቀር እና ይህ እንዳይሆን ተቀጣሪዎቹ ከካምፓኒው ጋር ካልተስማሙ በቀር ነው።

አንቀጽ 14.03ን ተመርኩዘው ክፍያ የሚታሰብለት ቫኬሽን የሚገባቸው ተቀጣሪዎች **ቫኬሽናቸውን ወደ የተናጠል ቀን ቫኬሽኖች ለመቆራረጥ እንዲችሉ** ቡክ ከማድረግ ሊቆጠቡ ይችላሉ። **ኤፕሪል 1 ላይ 10 ዓመት የማይሞላ የአገልግሎት ዘመን የሚኖራቸው ተቀጣሪዎች** ከሚገባቸው ቫኬሽን ላይ አንዱን (1) ሳምንት መቆጠብ እና ኤፕሪል **1 ላይ 10 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሚሆን የአገልግሎት ዘመን የሚኖራቸው ተቀጣሪዎች** ከሚገባቸው ቫኬሽን ላይ ሁለቱን (2) ሳምንት መቆጠብ ይችላሉ። እነዚህ **የሲንግል ቫኬሽን** ቀናት በካምፓኒው አስቀድመው መጽደቅ ይኖርባቸዋል። እንዲሁም በቢዝነሱ ፍላጎቶች እና በቫኬሽን ፕሮግራም መኖር ወይም በካምፓኒው ጥያቄውን የማስተናገድ አቅም ይወሰናሉ። የአንድ (1) ቀን ቫኬሽን ጥያቄዎች በ"ቀድሞ የመጣ ቀድሞ ይስተናገዳል" መርህ የሚጸድቁ ይሆናል። ይህም ከእያንዳንዱ ዓመት ኤፕሪል 1 አንስቶ አንቀጽ **14.08 ላይ ተመርኩዞ ይደረጋል።** ከአንድ (1) ሳምንት በሚያንስ ብሎክ የሚወሰድ ቫኬሽን ለ**አንቀጽ** 14.18 አይጋለጥም፣ ቅድሚያ ክፍያም አይሰጥም። ከፊል ቫኬሽን በቫኬሽኑ ዓመት መጨረሻ ላይ ክፍያ ይፈፀምለታል።

14.06 ክፍያ የሚታሰብለት የአራት (4) ሳምንታት ቫኬሽን የሚገባቸው የፉል-ታይም ተቀጣሪዎች ቫኬሽኖቹን በተከታታይ እንዲወስዱ ይፈቀድላቸዋል። ነገር ግን ይህ ካምፓኒው እና ተቀጣሪው የጋራ ስምምነት ከሌላቸው በስተቀር በጁን፣ ጁላይ፣ ኦገስት፣ ሴፕቴምበር፣ እና ዲሴምበር ወራት ውስጥ ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም።

14.07 ቫኬሽን ወቅቱ ለሁሉም ተቀጣሪዎች ሌላ ስምምነት በእነርሱ እና በካምፓኒው መካከል እስከሌለ ድረስ ከኤፕሪል 1 እስከ ማርች 31 ይሆናል።

14.08 **<u>ቫኬሽን ፕሮግራም አወጣጥ</u>**

ቫኬሽኖች እንደየቢዝነሱ ፍላጎት በማንኛውም ጊዜ በካላንደር ዓመቱ ውስጥ ሊሰጡ ይችላሉ። በአንድ ጊዜ እስከ ቫኬሽን እንዲወጡ የሚፈቀድላቸው ከአስር (10%) ፐርሰንት የማይበልጡ የዲፓርትመንቱ ሰራተኞች ብቻ ናቸው። **አስር (10%) ፐርሰንት የተባለው ቫኬሽን እንዲወጡ ፕሮግራም የተያዘላቸውን ሰራተኞች ብቻ እንጂ በሌላ ምክንያት የቀሩትን ተቀጣሪዎች አያጠቃልልም።**

በእያንዳንዱ ዓመት ጃኒዋሪ 1 ጀምሮ በየዲፓርትመንቱ ካምፓኒው በስራ ሱፐርቫይዘሩ አማካኝነት በየዲፓርትመንቱ የሚገኘውን እያንዳንዱን ተቀጣሪ የአንደኛው፣ ሁለተኛው እና ሦስተኛው ሳምንት ቫኬሽናቸው እንዴት ቢሆን እንደሚመርጡ በሲኒዮሪቲ ቅደም ተከተል ይጠይቃቸዋል። በተጨማሪም ተቀጣሪዎች ቀሪ የቫኬሽን ሳምንታት ካሏቸው ምርጫቸውን ሳምንት በሳምንት በ ኒዮሪቲ ቅደም ተከተል ያሳውቃሉ።

ብቁ ተቀጣሪዎች የሚገባቸውን ቫኬሽን ሁሉንም በአንድ (1) ጊዜ እንዲሰጣቸው መጠየቅ ይችላሉ። ለምሳሌ፡ ሁሉንም ሳምንታት በአንድ (1) የመጀመሪያ ቫኬሽን
“ምርጫ” በአንቀጽ 14.05 እና 14.06 መሠረት። ካምፓኒው የቀረቡለትን የቫኬሽን ጥያቄዎች ሁሉ ቢያጸድቅ ከአስር (10%) ፐርሰንት ገደቡ የሚያልፉ አይነት ከሆነ እና ካምፓኒው የሁሉንም የዲፓርትመንቱን ተቀጣሪዎች ጥያቄ ማስተናገድ ካልቻለ በሲኒዮሪቲ የሚፈታ ይሆናል። የዲፓርትመንቱ የአስር (10%) ፐርሰንት ገደብ ላይ እስኪደረስ ድረስ ለሲኒየር ተቀጣሪዎች ቅድሚያ እየተሰጠ የቫኬሽን ጥያቄዎች የሚስተናገዱ ይሆናል።

ይህም ፕሮሰስ ከዓመቱ ማርች 1 ዕለት ሳያልፍ መጠናቀቅ ይኖርበታል። የስራ ሱፐርቫይዘሩ እና ካምፓኒው በመቀጠልም ከላይ በተቀመጡት እና በጋራ ስምምነቱ የሲኒዮሪቲ ፕሮቪዥኖች በመመሥረት የጸደቀውን የቫኬሽን ፕሮግራም ከኤፕሪል 1 ሳያልፉ መለጠፍ እና እንደተለጠፈም ማቆየት ይኖርባቸዋል። ተቀጣሪውም የቫኬሽን ወቅታቸውን መጽደቅ ወይም ውድቅ መደረግ ማረጋገጫ በጽሑፍ መክል ከሱፐርቫይዘሩ የሚቀበል ይሆናል። የተባለው የጸደቀው ቫኬሽን ፕሮግራም አወጣጥም ሌላ ስምምነት በካምፓኒው እና ተቀጣሪ መካከል ከሌለ በስተቀር አይቀየርም። የተለጠፈው ቫኬሽን ፕሮግራምም የጸደቁ ማንኛቸውንም አዲስ ለውጦች ወይም አዲስ የተጨመሩ የቫኬሽን ሰዓታትን እንዲያሳይ በወር አንዴ አፕዴት ይደረጋል። ተቀጣሪው የጠየቀውን የቫኬሽን ጊዜ ለመስጠት ካምፓኒው ልባዊ ጥረት ያደርጋል። የቫኬሽን ምርጫ ፕሮሰሱ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚጠየቁ ቫኬሽኖች “መጀመሪያ የመጣ መጀመሪያ ይስተናገዳል” በሚለው መርህ ይስተናገዳሉ። ከቫኬሽን ምርጫ ፕሮሰሱ የቫኬሽን ጥያቄ የሚያቀርቡ ተቀጣሪዎች ለሱፐርቫይዘራቸው የተጻፈ ጥያቄ ያቀርቡና በመልሱ ከሱፐርቫይዘራቸው እሺታ ወይም እምቢታው በጽሑፍ ይደርሳቸዋል።

አስር (10%) ፐርሰንቱ ሲሰላ ቀጥሩ ወደላይ የሚጠጋጋ ይሆናል። በአንድ ዲፓርትመንት ውስጥ አራት (4) ተቀጣሪዎች ካሉ በአንድ ጊዜ ቢያንስ አንድ (1) ተቀጣሪ ቫኬሽን እንዲሄድ ይፈቀድለታል።

ካምፓኒው በሚፈቅድበት ጊዜ አስር (10%) ፐርሰንት ገደቡ የሚታለፍባቸው ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ።

14.09 በፉል-ታይም ተቀጣሪ ቫኬሽን ወቅት ላይ አንድ ጄነራል በዓል ቢያርፍ እና በዓሉ ተቀጣሪው ቫኬሽን ላይ ባይሆን ኖሮ ክፍያ የሚያገኝበት ከሆነ አንድ ተጨማሪ ቫኬሽን እንዲሰጠው፣ **የአንድ ተጨማሪ ቀን ክፍያ እንዲከፈለው፣ ወይም ደግሞ ቫኬሽኑ በአንድ ቀን እንዲራዘምለት** ይደረጋል። **ከእነዚህ ውስጥ የትኛው አማራጭ ይመረጣል የሚለው በጋራ ስምምነት የሚወሰን ይሆናል።** አንድ ተጨማሪ ቀን ቫኬሽን መስጠት ስራ ላይ ችግር የሚያመጣ ከሆነ ወይም ሌሎች የቫኬሽን ፕሮግራሞች ላይ ጣልቃ የሚገባ ከሆነ በእርሱ ፋንታ የስምንት ሰዓታት ክፍያ **(ወይም እንደፈረቃው ርዝማኔ አስር (10) ወይም አስራ ሁለት (12) ሰዓታት)** የሚሰጥ ይሆናል።

14.10 የአንድን ፉል-ታይም ተቀጣሪ የጸደቁ የቫኬሽን ፕሮግራሞችን ካምፓኒው ሁለት (2) ሳምንት አስቀድሞ ሳያሳውቅ ሊቀይር አይችልም። በተለይ ደግሞ ተቀጣሪው ለቫኬሽኑ ያቀዳቸው ክፍያ የፈጸመባቸው እና ክፍያውም የማይመለስባቸው ጉዳዮች ካሉ እና ደረሰኝ ወይም ማስረጃ ካቀረበ ፕሮግራሙ በካምፓኒው በፍጹም ሊቀየር አይችልም።

14.11 የፉል-ታይም ተቀጣሪ በከባድ ሕመም (የቀዶ ጥገና ዕለትን ሳያጠቃልል) ወይም በቫኬሽን ላይ በተከሰተ አደጋ ምክንያት በቤቱ ወይም በሆስፒታል እንዲውል በሐኪም ከታዘዘ የቫኬሽኑ ሒሳብ ወደ ስራ እስኪመለስ እንዲዘዋወርለት (ነገር ግን ከኤፕሪል 1 - ሴፕቴምበር 30 ካለው የቫኬሽን ወቅት ውጪ) መጠየቅ ይችላል።

14.12 ሌላ የጋራ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የፉል-ታይም ቫኬሽን ኢንታይትልመንት ከኤፕሪል 1 እስከ ማርች 31 ድረስ ከኤፕሪል 1ዱ የብቁነት ቀን ጋር እንዲገናኝ ተደርጎ መወሰድ አለበት።

ተቀጣሪዎች እስከ ሁለት (2) ሳምንታት የሚደርስ ያልተጠቀሙበትን የቫኬሽን ጊዜ ከዓመት ወደ ዓመት እንዲያስተላልፉ ይፈቀድላቸዋል።

14.13 ከአንድ (1) ዓመት በታች የሚሰሩ ቅጥራቸው የተቋረጠባቸው ተቀጣሪዎች የሚሰጣቸው የቫኬሽን ክፍያ መጠን የሚሆነው እሰ አሁን ከሰሩት ውስጥ ቫኬሽን ክፍያ ያላገኙበት ጠቅላላ ደመወዝ አራት (4%) ፐርሰንት ይሆናል።

<u>ፓርት-ታይም</u>

14.14 የፓርት-ታይም ሰራተኞች የሚያገኙት የቫኬሽን ክፍያ አላዋንስ መጠን የሚሆነው ባለፈው ዓመት ከጃኒዋሪ 1 እስከ ዲሴምበር 31 በአጠቃላይ ያገኙት ደመወዝ ላይ ተመስርቶ ይሆናል። የየዓመቱ የኤፕሪል ወርም በእዚህ መልኩ የሚሆን ይሆናል። ኢንታይትልመንት ከታች እንደተቀመጠው ካምፓኒው ጋር እስከ የዓመቱ ዲሴምበር 31 ድረስ የሚኖር ሲኒዮሪቲ ላይ ተመሥርቶ ይሆናል፡

ከአምስት (5) ዓመታት በታች	- 4%
አምስት (5) ዓመታት ነገር ግን ከአስር (10) ዓመታት በታች	- 6%
አስር (10) ዓመታት ነገር ግን ከአስራ ዘጠኝ (19) ዓመታት በታች	- 8%
አስራ ዘጠኝ (19) ዓመታት እና ከዚያ በላይ	- 10%

14.15 ባለፉት አስር (10) ዓመታት የአምስት (5) ወይም ከዚያ በላይ ቅጥር ዘመን ያላቸው ተቀጣሪዎች የቫኬሽን ክፍያ ላላገኙበት የቫኬሽን ወቅት የጠቅላላ ደመወዛቸውን ስድስት (6%) ፐርሰንት የሚቀበሉ ይሆናል።

14.16 ተቀጣሪው በጽሑፍ ጥያቄ ሲያቀርብ ለቫኬሽን ሲባል ክፍያ የማይታሰብለትን የእረፍት ጊዜ ሊሰጠው ካምፓኒው ተስማምቷል። ይህ የሚደረገው ለኢንታይትልመንት የሳምንት ብዛቶቹ ብቻ በተቀጣሪው የቫኬሽን ኢንታይትልመንት ፕሮግራም ላይ ተመሥርቶ ይሆናል። ሦስት (3) ተከታታይ ሳምንታት በኤፕሪል፣ ሜይ፣ ጁን፣ ጁላይ፣ ኦገስት ወይም ሴፕቴምበር ወራት ላይ የሚፈቀዱ ይሆናል። በካምፓኒው እና ተቀጣሪ መካከል ሌላ ስምምነት እስከሌለ ድረስ ሒሳቡ በሌላ በማንኛውም ወር በካምፓኒው የሚፈቀድ ይሆናል።

<u>አጠቃላይ</u>

14.17 “ጠቅላላ የተከፈለ ደመወዝ” የሚሉት ቃላት በእዚህ **አንቀጽ** ላይ በተጠቀሱበት ቦታ ሁሉ ትርጉማቸው በማኒቶባ ክፍለ ሃገር *የቅጥር ስታንዳርዶች ኮድ* ላይ የሚተረጎም ይሆናል።

14.18 ከሁለት (2) ሳምንታት አስቀድሞ ተቀጣሪው እስካሳወቀ ድረስ ካምፓኒው ለተቀጣሪው የቫኬሽን ክፍያውን አስቀድሞ ሊከፍለው ተስማምቷል።

14.19 የዚህን ስምምነት የሲኒዮሪቲ ፕሮቪዥኖች ተከትሎ ለእያንዳንዱ ተቀጣሪ የቫኬሽን ወቅቱን የመወሰን የካምፓኒው መብት የተጠበቀ ነው።

14.20 አንቀጽ 14 ላይ ያለውን የቫኬሽን ኢንታይትልመንት በሚመለከት ከላይ የተቀመጠው ሲኒዮሪቲ አንድ ተቀጣሪ ሌይኦፍ ላይ የነበረበትን ጊዜ አያካትትም።

14.21 በካምፓኒው ወደ ስራቸው የተመለሱ እና የሚገባቸውን የቫኬሽን ክፍያ ያገኙ ተቀጣሪዎች በተመለሱበት ዓመት ውስጥ የቫኬሽኑን መጠን ክፍያ ሳይታሰብላቸው በቫኬሽን መልክ መውሰድ ይችላሉ።

<u>አንቀጽ 15 የማኔጅመንት መብቶች እና ስራዎች</u>

15.01 የካምፓኒው ማኔጅ የማድረግ እና የስራ ኃይሉን የመምራት፣ ፕላን የማድረግ፣ የፋብሪካ ኦፕሬሽኖችን የመምራት እና የመቆጣጠር፣ የተቀጣሪዎችን ዲሲፕሊን እና ቅልጥፍና የማስጠበቅ፣ ተቀጣሪዎች የካምፕኒውን ህግ እና ደንቦች እንዲከተሉ የማድረግ፤ የመቅጠር፤ ሌይኦፍ የማድረግ ወይም የተቀጣሪዎችን የስራ ሰዓታት የመመደብ፤ የስራ እድገት የመስጠት፤ ተቀጣሪዎችን በበቂ ምክንያት ዲሞት፣ ዲሲፕሊን፣ ሰስፔንድ ወይም ዲስቻርጅ የማድረግ መብቶች እና ኃላፊነቶች ለማኔጅመንት በብቸኝነት የሚሰጡ ናቸው።

15.02 በፋብሪካው ውስጥ ስለሚሰሩት ምርቶች ብቸኛው ዳኛ ካምፓኒው ይሆናል።

15.03 ከላይ የተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም በእዚህ ስምምነት ላይ የተቀመጡትን ስፔሲፊክ ፕሮዚዥኖች ሊቀይር አይችልም።

15.04 ይህን ስምምነት በሚያስተገብርበት ወቅት ካምፓኒው በምክንያታዊነት፣ በፍትሓዊነት፣ በቅንነት፣ እንዲሁም ከዚህ ስምምነት ጋር በሚጣጣም ሁኔታ ሊሆን ይገባል።

አንቀጽ 16 ጤና እና ደህንነት

16.01 ሰራተኞች በቅጥራቸው ጊዜ ለደህንነታቸው እና ጤናቸው ሲባል ሊደረጉ የሚገቡ ነገሮችን ሁሉ ካምፓኒው እና ዩኒየኑ ሊያደርጉ ይገባል።

16.02 የጤና እና ደህንነት ኮሚቴ

ካምፓኒው እና ዩኒየኑ ከሁለቱም ወገኖች እኩል የተወካዮች ቁጥር ያለው ባለ አስራ ስድስት (16) አባላት የደህንነት ኮሚቴ ለማዋቀር ተስማምተዋል። የዚህ ኮሚቴ ስራ ለሁሉም ተቀጣሪዎች ደህንነት ያልተጓደለው የስራ ሁኔታ እንዳለ እንዲቀጥል ማድረግ ነው። የደህንነት ኮሚቴው ስብሰባዎች በየወሩ በመደበኛ የስራ ሰዓታት ላይ የሚደረጉ ይሆናሉ።

በሚቻልበት ጊዜ ሁሉ እነዚህ ስብሰባዎች በወሩ ሦስተኛው ሳምንት ላይ ይደረጋሉ። ማኔጅመንት ሲያጸድቀው የጤና እና ደህንነት ችግሮችን በመመርመር እና የጤና እና ደህንነት ስብሰባዎችን በመታደም የሚያልፍ ጊዜ ክፍያ የሚታሰብለት ጊዜ ይሆናል።

ካምፓኒው ለኮሚቴው/ሊቀመንበሩ ግዴታቸውን የሚወጡበት በቂ ጊዜ ለመፍቀድ ተስማምቷል።

16.03 የጤና እና ደህንነት ኮሚቴው ስለተሰበሩ ወይም የተጎዱ ማሽኖች በመደበኛ የኮሚቴ ስብሰባው ላይ ውይይት ያደርጋል።

16.04 ካምፓኒው ለሁሉም የደህንነት ካፒቴኖች እስከ **አራት (4)** መደበኛ የእረፍት ቀናት (**ሁለቱ (2ቱ)** በካምፓኒው የሚከፈሉ እና **ሁለቱ (2ቱ)** በዩኒየኑ የሚከፈሉ)፣ ለሁሉም የደህንነት ኮሚቴው አባላት ለሆኑት ደግሞ እስከ **አምስት (5)** መደበኛ የእረፍት ቀናት (ሁለቱ (2ቱ) በካምፓኒው የሚከፈሉ እና **ሦስቱ (3ቱ)** በዩኒየኑ የሚከፈሉ) ሴሚናሮችን፣ ኮርሶችን፣ ወይም ኮንፍረንሶችን ይታደሙ ዘንድ ለመስጠት ተስማምቷል። የእነዚህ እረፍት ቀናት ፕሮግራም አወጣጥ የሚወሰነው ካምፓኒውእና ዩኒየኑ በጋራ ተስማምተው ይሆናል።

16.05 ማንኛውም ተቀጣሪ በአንድ ቀን ውስጥ በመሃል ቢያንስ የአስር (10) ደቂቃ የማቀዝቀዣ ጊዜ ሳይሰጠው ከአንድ ኤክስትሪም የስራ ሁኔታ ወደ ሌላ ኤክስትሪም የስራ ሁኔታ (ለምሳሌ ከኪሊንግ ፍሎር ወደ ፍሪዘር ወይም ኩለር) ሊላክ አይችልም።

16.06 በሁሉም ፈረቃዎች ላይ ለሚሰሩ ሰራተኞች የመጀመሪያ እርዳታ በቅርብ ቦታ ሊኖር ይገባል። በካምፓኒውም ይሁን በዩኒየኑ የሚሰጠውን ስልጠና አጠናቀው የመጀመሪያ እርዳታ ለመስጠት ብቁ የሆኑ ተቀጣሪዎች ስም ዝርዝር በቡሌቲን ቦርዶች ላይ ይለጠፋል። እነዚህን ተቀጣሪዎችም በአደጋ ጊዜ ለመለየት ይረዳ ዘንድ በሄልሜታቸው ላይ ቋሚ የሆነ ስቲከር ይለጠፋል።

16.07 **<u>አደገኛ ስራን ያለመስራት መብት</u>**

አንድ ተቀጣሪ አንድ ስራ ለደህንነቱ ወይም ለጤናው አደገኛ ነው ብሎ እንዲያምን የሚያደርግ አሳማኝ ምክንያት ካለ እና ተቀጣሪውም እንደዚህ ብሎ ካመነ ተቀጣሪው በመጀመሪያ ስለ ጉዳዩ አሳሳቢነት ለሱፐርቫይዘሩ ሪፖርት ማድረግ አለበት። ሁኔታውን ለማስተካከል አስቸኳይ እርምጃ ካልተወሰደ ወይም የማስተካከያ እርምጃ አስፈላጊ እንዳልሆነ ተነግሮት ተቀጣሪው አሁንም ስራው ለደህንነቱ ወይም ለጤናው አደገኛ ነው በሚለው እምነቱ ከቀጠለ ካምፓኒው፣ የጤና እና ደህንነት ኮሚቴው ሰራተኛ ሊቀመንበር፣ እና ተቀጣሪው በጉዳዩ ዙርያ ምርመራ ማካሄድ ግድ ይላቸዋል። ከምርመራውም በኋላ ጉዳዩ ካልተስተካከለ፣ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም የመጣ ሰው ወደ ካምፓኒው ኦፕሬሽን መጥቶ ስራውን በአካል እስኪመረምረው ድረስ ተቀጣሪው ያንን ስራ ላለመስራት የመወሰን መብት አለው። በእዚህ የጊዜ ወቅት ተቀጣሪው ወደ ሌሎች በካምፓኒው ክፍት ሊሆኑ ወደሚችሉ አማራጭ የስራ መደቦች ሊዘዋወር ይችላል። ተቀጣሪው እነዚህን አማራጭ መደቦች ለመስራት እምቢ ካለ ከላይ ለተቀመጠው የጊዜ ወቅት ክፍያ አያገኝም።

16.08 መከላከያ መሳሪያዎች እና ሌሎች በ16.08 ላይ ያልተቀመጡ ተቀጣሪዎችን ከጉዳት በአግባቡ ለመጠበቅ አስፈላጊ ናቸው የተባሉ መሳሪያዎች በካምፓኒው የሚቀርቡ ይሆናል። በካምፓኒው የሚቀርቡትን መከላከያ መሳሪያዎች እና መገልገያዎች በተገቢው መጠን እና ትልቀት የሚያቀርብ አቅራቢ እስከተገኘ ድረስ በጥሩ ሁኔታ እና በተገቢው መጠን እና ትልቀት ይቀርባሉ። የመከላከያ ማሽኖችን እና መሳሪያዎችን እርጅና፣ እድሜ፣ መጠን ወይም ትልቀት በሚመለከት በአሳማኝ መልኩ አሳሳቢ የሆነ ጉዳይ እንደገጠመው አንድ ተቀጣሪ ለማኔጅመንት ሲናገር የጤና እና ደህንነት ኮሚቴው ጉዳዩን መርምሮ የመከላከያ ትንኖቹ እና መሳሪያዎቹ ተገቢውን ትልቀት እና በጥሩ ደህንነት ላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስፈልገውን እርምጃ ይወስዳል። መሰል ጉዳዮች የጤና እና ደህንነት ኮሚቴው ቀጣይ ስብሰባ ላይ የሚቀርቡ እና ግኝቶቹም ጉዳዩ የቀረበበት የጤና እና ደህንነት ኮሚቴ ስብሰባ በተደረገ በአራት (4) ሳምንታት ውስጥ ጉዳዩን ላመለከተው ተቀጣሪ ሪፖርት የሚደረጉ ይሆናል።

16.09 **<u>መከላከያ አልባሳት / በካምፓኒው የሚቀርቡ መሳሪያዎች</u>**

የታጠቡ ኩለር ኮቶች፣ ሱሪዎች (እንዳስፈላጊነቱም ሸሚዞች)፣ ኤፕረኖች፣ ፕላስቲክ ጫማዎች፣ የእርጥበት ልብሶች፣ “ማውስትራፖች”፣ ቢለዋዎች፣ ብረቶች፣ ስካባርዶች፣ የጭንቅላት ደህንነት እቃዎች፣ ከቨርኦሎች፣ ሜሽ ግለቮች፣ የፕላስቲክ ግለቮች፣ ሄይር ኔቶች፣ ባክላቫዎች፣ ቢርድ ኔቶች፣ የጥጥ ግለቮች፣ የክረምን ቢብ ከቨርኦሎች፣ የክረምት ሚቶች እና የፍሪዘር/ክረምት ጃኬቶች በካምፓኒው የሚቀርቡ እና እንደ አስፈላጊነቱ በሱፐርቫይዘሮች ሲፈቀድ ምትኮች የሚሰጡ ይሆናል። ተቀጣሪው ከላይ ለተጠቀሱት መገልገያዎች አቅርቦት ወይም ተክቶት የሚከፍለው ምንም ነገር አይኖርም።

በካምፓኒው የሚቀርቡትን መከላከያ አልባሳት እና/ወይም መገልገያዎች ተገቢውን መጠን እና ትልቀት የሚያቀርብ አቅራቢ እስከተገኘ ድረስ በጥሩ ሁኔታ እና በተገቢው መጠን እና ትልቀት ይቀርባሉ። ተገቢው ትልቀት ካልተገኘ የጤና እና ደህንነት ኮሚቴው የተስማማባቸውን ተቀጣሪዎች እንዲበቁ ተደርገው በልካቸው ይቀየራሉ። ሁሉም የደህንነት መሳሪያ ጥሩ ጥራት ያለው ይሆናል።

በካምፓኒው የሚቀርቡትን መከላከያ አልባሳት እና/ወይም መገልገያዎች አውቀው የሚያበላሹ ተቀጣሪዎች የመጠገኛ ወይም መተኪያ ወጪውን የመሸፈን ኃላፊነቱን ይሸከማሉ። የፍሪዘር ጃኬቶች፣ ቢለዋዎች እና ደህንነት መሳሪያዎች አተካክ ሱፐርቫይዘሩ ከፈቀደ በኋላ አንድ አስረክቦ አንድ በመውሰድ ይሆናል።

16.10 መሳሪያዎች

የትሬድ ተቀጣሪዎች የራሳቸውን መሳሪያዎች ማቅረብ ይኖርባቸዋል። የራሱን መሳሪያ እንዲጠቀም ለሚጠበቅበት እያንዳንዱ ተቀጣሪ ካምፓኒው የሦስት መቶ ($300) ዶላር የመሳሪያ አላዋንስ ከተቀጠረበት ቀን አንስቶ በየስድስት (6) ወራት ሊሰጥ ተስማምቷል።

16.11 ቢለዋ መሞረድ

ካምፓኒው በፈረቃ ላይ አንድ ተቀጣሪ የቢለዋ ሞራጅ እንዲሆን ካልመደበ ለቢለዋ መሞረጃ የሚሆን ሰዓት በፈረቃው ላይ ከክፍያ ጋር ለመስጠት ተስማምቷል።

16.12 የደህንነት ጫማዎች

የደህነት፣ የዘላቂነት፣ እና የጥራት መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ በፋብሪካው ላይ ላሉ ክልሎች ተስማሚ የሚሆነውን ጫማ የመወሰን የካምፓኒው መብት የተጠበቀ ነው። የጥራት እና የምግብ ደህንነት ስታንዳርዶችን ለማስጠበቅ ሲባል እነዚህ ጫማዎች በካምፓኒው ቅጥር ጊቢ ውስጥ መቅረት ይኖርባቸዋል። ተቀጣሪዎች ጫማዎቹን በጥሩ ሁኔታ መያዝ ይጠበቅባቸዋል።

ካምፓኒው ለእያንዳንዱ ተቀጣሪ ጥራት ያላቸውን የደህንነት ጫማዎች ወይም የፕላስቲክ ደህንነት ጫማዎች በነፃ በየዓመቱ እና በሚቀጥለው ዓመት፣ አስፈላጊ ከሆነ እና በሱፐርቫይዘራቸው ከጸደቀም ከዚያ ቀደም ብሎ ያቀርባል።

ካምፓኒው ጫማ ያቀረበላቸው ፕሮቤሽን ላይ ያሉ ተቀጣሪዎች ለስድስት (6) ወራት ለሪኢምበርስመንት ብቁ አይሆኑም።

ኩለር ውስጥ ያለው ፍሪዘር ውስጥ የሚሰሩት ተቀጣሪዎች እንደአስፈላጊነቱ የዊንተር ጫማ እና ምትክ ሶል ይቀርብላቸዋል።

ሬይሎች ውስጥ፣ ሺፒንግ/ሪሲቪንግ ዲፓርትመንት ውስጥ፣ ወይም ከህንጻው ውጪ የሚሰሩ ተቀጣሪዎች ከኦክቶበር 1 እስከ ኤፕሪል 30 ላሉት ወራት **ፍሪዘር ውስጥ የሚሰሩትን ተቀጣሪዎች አይነት** የዊንተር ጫማ እና ምትክ ሶል እንደአስፈላጊነቱ ይቀርብላቸዋል። የዊንተር ጫማዎች እና መተኪያ ሶሎች አተካክ ሱፐርቫይዘሩ ከፈቀደ በኋላ አንድ አስረክቦ አንድ በመውሰድ ይሆናል።

በስራቸው ወቅት መደበኛ ጫማዎችንም፣ ፕላስቲክ ጫማዎችንም እንዲጫሙ በካምፓኒው የሚገደዱ የ**ሳኒቴሽን እና ሌሎች** ተቀጣሪዎች ሁለቱም የጫማ አይነቶች ይቀርቡላቸዋል።

ተቀጣሪዎች ከመረጡ የራሳቸውን በ ሲ.ኤስ.ኤ የተረጋገጡ የደህንነት ጫማዎች ወይም የደህንነት ፕላስቲክ ጫማዎች መግዛት ይችላሉ። ካምፓኒውም የግዢ ማስረጃ ካመጡለት በኋላ እስከ አንድ መቶ ሰባ አምስት ($175) ዶላር ድረስ ወጪያቸውን በየዓመቱ አንድ ጊዜ ያወራርድላቸዋል። ይህ መጠን **ከጃኒዋሪ 1፣ 2021 በኋላ ወደ ሁለት መቶ ($200) ዶላር ያድጋል**።

ተቀጣሪዎች አሮጌ ጫማቸውን ሊመልሱ አይጠበቅባቸውም። ነገር ግን በተሰጣቸው በአንድ (1) ወር ጊዜ ውስጥ አዲሱን ጫማ ብቻ እንደሚጫሙ ይጠበቃል።

16.13 <u>የጤና እና ደህንነት ትብብር / የአደጋዎች እና ጉዳቶች ቅነሳ / ኤርጎኖሚክስ</u>

ካምፓኒው እና ዩኒየኑ ከጥምር የጤና እና ደህንነት ኮሚቴው ጋር በመተባበር በፋብሪካው የሚከሰቱ ጉዳቶችን ለመለየት እና መዝግቦ ለመከታተል ተስማምተዋል። ይህም የሚደረገው ተባብሮ በመስራት ሁሉንም አደጋዎች **እና ጉዳቶች፣ ሪፔቲቲቭ ስትሬይን ኢንጁሪዎችን ጨምሮ** ለማጥፋት በማሰብ ነው። ካምፓኒው የጉዳቱን አይነት፣ ቀን፣ ሰዓት፣ ቦታ ወዘተ የሚያትቱ የአደጋ ሪፖርት ቅጂዎችን በሙሉ ለመስጠት ተስማምቷል። **የመጀመርያ እርዳታ ጣቢያው ጉብኝቶችን ከነምክንያታቸው መዝግቦ ዳታውን በየዓመቱ ኮምፓይል በማድረግ ዩኒየኑ በጠየቀ ጊዜ ለዩኒየኑ ያቀርባል።**

ይህ መረጃ በየወሩ ለጤና እና ደህንነት ኮሚቴው የሚሰጥ ይሆናል። እነርሱም በጋራ ከካምፓኒው ጋር ተስማምተው ከስራ ሰዓታት ውስጥ ጊዜ በመምረጥ ተጨማሪ ምርመራ እና ከተጎጂ ተቀጣሪዎች ጋር ውይይት ያደርጋሉ፤ ወይም የስራ ሁኔታዎችን ያጤናሉ፣ ከዚያም የምርመራቸውን ውጤት የሚፈቀድ ከሆነ ወደ ማኔጅመንት ከአስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ ሃሳቦች ጋር ያቀርባሉ።

እነዚህን የቀረቡትን ማስተካከያዎችም ከግምት ውስጥ ለማስገባት እና እንደ አስፈላጊነቱም የራሳቸውን ኤክስፐርቶች በማምጣት ከፋብሪካው የጤና እና ደህንነት ኮሚቴ ጋር ሰብስቦ አደጋዎችን ለማጥፋት ለመርዳት፣ ካምፓኒው ሊተገብራቸው የሚችላቸው ኤርጎኖሚክ ለውጦችን ሃሳብ ለማቅረብ ካምፓኒው ተስማምቷል።

ኮሚቴው በሁሉም ጊዜያት ተቀጣሪዎች ደህንነቱ በተረጋገጠ እና ምርታማ በሆነ ሁኔታ እንዲሰሩ ያበረታታል።

16.14 <u>ኤርጎኖሚክስ</u>

በፋብሪካው ያሉትን የኤርጎኖሚክስ ችግሮች የኤርጎኖሚክስ ኮሚቴው የሚመለከታቸው ይሆናል። ኮሚቴው ቢያንስ ከሦስት (3) በዩኒየኑ ከተመረጡ አባላት (ከእነዚህ አንዱ (1ዱ) የፉል-ታይም የዩኒየን ተወካይ ሊሆን ይችላል) እና ሦስት (3) በካምፓኒው ከተመረጡ አባላት ይዋቀራል። የኤርጎኖሚክስ ኮሚቴው ጥቅም የተሻለ ምርታማነትን፣ የስራ ላይ ደህንነትን፣ የስራ እርካታን ለማበረታታት እና ሪፔቲቲቭ ስትሬይን ኢንጁሪዎችን ለመቀነስ ነው። ኮሚቴው የስራ ልማዶችን እና ፕሮሰሶችን (የላይን ስፒዶችን እና የላይን ስፒድ ቤንችማርኮችን ጨምሮ) የመገንዘብ፣ የመለየት፣ እና የመመርመር ስራ ይሰራል። ከዚያም አስፈላጊውን ምክር ማኔጅመንት እርምጃ ይወስድ ዘንድ ያቀርባል። ይህም በስተመጨረሻ ሪፔቲቲቭ አይነት የስትሬይን ኢንጁሪዎችን ይቀንሳል። ማንኛውም የጥምር የጤና እና ደህንነት ኮሚቴው አባል የአንድ ወርክስቴሽን ኤርጎኖሚክስ እንዲታይ ሊጠይቅ ይችላል።

አንቀጽ 17 ስትራይኮች እና ሎክአውቶች

17.01 በእዚህ ስምምነት የአገልግሎት ዘመን ውስጥ ምንም አይነት ስትራይኮች፣ ሎክአውቶች፣ የስራ ማቆሞች፣ ወይም የስራ ማጓተቶች እንደማይኖሩ የጋራ ስምምነት ላይ ተደርሷል።

አንቀጽ 18 የዩኒየን ተወካይ የፋብሪካ ጉብኝቶች

18.01 ስልጣኑ ያላቸው የዩኒየኑ የፉል-ታይም ተወካዮች የስራ ሁኔታዎችን ለማየት፣ ከአባላት እና ያልተፈረሙ ተቀጣሪዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ለማድረግ፣ እና የጋራ ስምምነቱ ነጥቦች እየተገበሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ፋብሪካውን መጎብኘት ይችላሉ።

ፋብሪካውን ከመጎብኘቱ በፊት እና ወደ ፋብሪካው በሚገባበት ጊዜ የዩኒየን ተወካዩ የማኔጅመንትን ተወካይ በማግኘት ፋብሪካውን ሊጎበኝ እንደሆነ እና ሁሉንም የደህንነት እና የጥራት ደንቦች እንደሚከተል ሊነግር ይገባል።

18.02 የዩኒየን ተወካይ አንድን ተቀጣሪ ቃለ መጠይቅ እንዲያደርግ የሚፈቀድለት ለሲፐርቫየሩ ካሳወቀ በኋላ እና እንደሚከተሉት ነው፡

(1) በማኔጅመንት በተፈቀደለት ብታ ላይ የሚደረግ ከሆነ፤

(2) በተቻለ ጊዜ ሁሉ በመመገቢያ ሰዓታት የሚደረግ ከሆነ ይህ አዋጭ ካልሆነ ግን፣

(3) በመደበኛ የስራ ሰዓታት ማኔጅመት ካልፈቀደ በቀር ለእንዲህ አይነት ቃለ መጠይቅ የሚወሰድ ከአስራ አምስት (15) ደቂቃ በላይ የሚሆን ጊዜ በካምፓኒው ጊዜ ላይ ሊሆን አይችልም።

18.03 ካምፓኒው ከዩኒየን ተወካዮች ጋር አብሮ በመስራት ግዴታቸውን እንዲወጡ እና የጋራ ድርድር ስምምነቱ ልይ የተቀመጡትን አስፈላጊ መረጃዎች እንዲያገኙ ለማድረግ ተስማምቷል።

አንቀጽ 19 ሊቭ ኦፍ አብሰንስ

19.01 **አንቀጽ** 25 ላይ በተቀመጠው መሠረት የመደብር አስተናባሪዎች የዩኒየን ጉዳዮች ላይ ይታደሙ ዘንድ ክፍያ የማይታሰብበት ሊቭ ኦፍ አብሰንስ (ፈቃድ) ይሰጣቸዋል። ይህም ካምፓኒው ሁለት (2) ሳምንት አስቀድሞ ስለ መጠይቁ እስከተነገረው ድረስ በዓመት እስከ **ሰባት (7)** ለሚደርሱ ቀናት ብቻ ይሆናል። የ**ሰባት (7)** ቀን ገደቡ ለዋና አስተናባሪው፣ ለረዳት ዋና አስተናባሪዎቹ፣ ለጤና እና ደህንነት ሊቀመናብርት እና ስራ አስፈፃሚ ቦርዱ ለመረጣቸው አባላት አያገለግልም። ለእነዚህ የዩኒየን ግዴታቸውን ለመወጣት የሚያስፈልጋቸው ጊዜ ይሰጣቸዋል። ድርድሮችን ለመታደም የሚሰጥ ፈቃድ ለእነዚህ ገደቦች ስሌት አያገለግልም።

19.02 አንድ (1) ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ሲኒዮሪቲ ያለው ማንኛውም ተቀጣሪ በየሁለት (2) ዓመቱ ክፍያ የማይታሰብለት እስከ ሁለት (2) ሳምንት የሚደርስ ፈቃድ (ሊቭ ኦፍ አብሰንስ) መጠየቅ ይችላል። ተቀጣሪዎች ያልተጠቀሙበትን ማንኛውም የቫኬሽን ጊዜ መጀመሪያ ወደ ማንኛውም ሊቭ ኦፍ አብሰንስ መጨመር ይኖርባቸዋል። ጥያቄው ሙሉ ዝርዝር አካትቶ በጽሑፍ መግባት አለበት። ማኔጅመንትም ይህንኑ ለየግለሰቡ የጥያቄያቸውን ምክንያት እና ጥያቄውን የማስተናገድ ችሎታቸውን እንደየስራው ፍላጎት ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይገባል። መሰል ጥያቄዎች ከሁለት (2) ሳምንታት አስቀድመው መጠየቅ ይኖርባቸዋል። የእነዚህ ጥያቄዎች አፈቃቀድ ያለ አሳማኝ ምክንያት በካምፓኒው ሊደበቅ አይችልም። እነዚህ ፈቃዶች በፕራዮሪቲ ከቫኬሽን ጥያቄዎች የሚያንሱ እና በ**አንቀጽ** 14.08 የሚተዳደሩ ይሆናሉ። ፈቃዶች (ሊቭስ ኦፍ አብሰንስ) ከቫኬሽን ጊዜ ጋር አንድ ላይ በማጣመር መወሰድ ይችላሉ።

አንድ ተቀጣሪ ከላይ የተጠቀሰውን ፈቃድ ካምፓኒውን ሳያሳውቅ ለሌላ ቀጣሪ ለመስራት ቢጠቀምበት በፈቃዱ እንደለቀቀ ይቆጠራል።

19.03 ከዩኒየኑ ሠላሳ (30) ቀናት አስቀድሞ የጽሑፍ ማሳወቂያ ከመጣ ካምፓኒው ለዩኒየኑ በፉል-ታይም የስራ መደብ ለተመረጠ ለአንድ (1) ተቀጣሪ እስከ አንድ (1) ዓመት የሚደርስ ፈቃድ (ሊቭ ኦፍ አብሰንስ) ለመስጠት ተስማምቷል። ይህን መሰል ፈቃድ (ሊቭ ኦፍ አብሰንስ) ያለ ክፍያ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ይሆናል። ነገር ግን ሲኒዮሪቲ ቢበዛ እስከ አንድ ዓመት ለሚደርስ ጊዜ እየተጠራቀመ ይቀጥላል። ተቀጣሪው ለካምፓኒው ለመስራት ከመመለሱ ሁለት (2) ሳምንታት አስቀድሞ ለካምፓኒው እንዲያሳውቀው ዩኒየኑ ተስማምቷል።

19.04 **<u>የነፍሰ ጡርነት/የወላጅ ፈቃድ</u>**

ለሰባት (7) ተከታታይ ወራት ወይም ከዚያ በላይ በካምፓኒው ተቀጥራ እየሰራች ያለች ሴት ተቀጣሪ ከካምፓኒው የነፍሰ ጡርነት ፈቃድ (ማተርኒቲ ሊቭ ኦፍ አብሰንስ) ለማግኘት ብቁ ትሆናለች። ይህች ተቀጣሪ ከተቻለ ከሚጠበቀው ውልደት አራት (4) ሳምንታት አስቀድማ፣ ካልተቻለ ግን ምንም ቢሆን ስራ ካቆመችበት ቀን ከሁለት (2) ሳምንታት በላይ ሳታሳልፍ የሚጠበቀውን የውልደት ቀን የሚጠቁም የህክምና ሰርተፊኬት አካትታ ለካምፓኒው በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርባታል። ይህች ተቀጣሪ የነፍሰ ጡርነት ፈቃዷ እንዳለቀ ወድያውኑ የወላጅነት ፈቃድ መውሰድ ካልፈለገች በስተቀር በወለደች በአስራ ሰባት (17) ሳምንታት ውስጥ በካምፓኒው ተመልሳ መቀጠር ይኖርባታል።

የነፍሰ ጡርነት ፈቃዷ እንዳለቀ ወድያውኑ ስራ ለመስራት የምታስብ ተቀጣሪ በጽሑፍም ማመልከት እና ወደ ስራ ለመመለስ ካሰበችበት ቀን ቢያንስ አራት (4) ሳምንታት አስቀድማ ለካምፓኒው ማሳወቅ ይኖርባታል። በጤናዋ ለስራ ብቁ እንደሆነች የሚመሰክር የሐኪም ሰርተፊኬት ለካምፓኒው ማቅረብ ይኖርባታል።

ሲኒዮሪቲ በነፍሰ ጡርነት ፈቃድ ላይም እየተጠራቀመ ይቀጥላል። ከፈቃዱ በፊት የተጠራቀሙ ጥቅማ ጥቅሞችም እንዳሉ ይቀጥላሉ።

<u>የወላጅነት ፈቃድ</u>

(1) <u>ኢንታይትልመንቶች</u>

ማንኛውም

(a) የ፡

(i) ልጅ ተፈጥሮአዊ እናት የሆነች ሴት ተቀጣሪ፣

(ii) ልጅ ተፈጥሮአዊ አባት ወይም አዲስ የተወለደ ህጻን ተንከባካቢ እና ህጋዊ አሳዳጊ የሆነ ወንድ ተቀጣሪ፣ ወይም

(iii) ክፈለ ሃገሩን ህግ መሠረት አድርጎ ህጻን በጉዲፈቻ የወሰደ፤ እና

(iv) ካምፓኒው ተቀጣሪ ሆኖ ከሰባት (7) ተከታታይ ወራት በላይ ያሳለፈ

(b) ከተቻለ ፈቃዱን ለመጀመር ከታሰበበት ቀን ቢያንስ አራት (4) ሳምንታት አስቀድሞ ቀኑን ጠቅሶ የወላጅነት ፈቃድ መጠይቅ ለካምፓኒው በጽሑፍ ያስገባ/ች፤

እስከ ስድሳ ሦስት (63) ተከታታይ ሳምንታት የሚደርስ የወላጅነት ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ነውና ሊፈቀድለት ይገባል።

(2) <u>የፈቃድ አጀማመር</u>

የወላጅነት ፈቃድ የህጻኑ/ኗ ልደት ወይም ጉዲፈቻ (ወይም ህጻኑ/ኗ ወደ ተቀጣሪው እንክብካቤ እና አሳዳጊነት የመጣ(ች)በትን ቀን) አንደኛ አመት አኒቨርሰሪ ሳያሳልፍ መጀመር አለበት። የወላጅነት ፈቃዱ የሚጀመርበትን ቀን ተቀጣሪው ይወስናል።

(3) <u>አርፍዶ የሚደረግ የወላጅነት ፈቃድ ማመልከቻ</u>

ከላይ በ19.04 1(ሀ) ስር የገባ ማመልከቻ በ19.04 1(ሀ) በተቀመጠው መሠረት ባይሆንም እንኳን በእዚህ **አንቀጽ** ስር ሙሉውን የ**ስድሳ ሦስት (63)** ሳምንት ፈቃድ ለማግኘት ይቻላል፣ ለካምፓኒው ማመልከቻ ሲገባም ሊፈቀድ ይገባል።

(4) <u>የተቀጣሪ ወደ ሥራ መመለስ</u>

በእዚህ አንቀጽ መሠረት የተሰጠው ፈቃድ ሲያበቃ ወደ ሥራው መመለስ የሚሻ ተቀጣሪ ፈቃዱ ሲጀመር ወደነበረበት የሥራ መደብ፣ ወይም ይህ መደብ ክፍት ካልሆነ የማይተናነስ ክፍያ እና ጥቅማ ጥቅም ወዳለው ሌላ ተመሳሳይ መደብ የሚመለስ ይሆናል።

(5) <u>ኢ.አይ. ጥቅማ ጥቅሞች</u>

ብቁ የሆኑ ተቀጣሪዎች በኢ.አይ. አክት ላይ የተቀመጠውን መጠን እና ርዝመት ያለውን የኢ.አይ. ጥቅማ ጥቅም ሊያገኙ ይገባቸዋል።

(6) ሲኒዮሪቲ በወላጅነት ፈቃድ ላይም እየተጠራቀመ ይቀጥላል። ከፈቃዱ በፊት የተጠራቀሙ ጥቅማ ጥቅሞችም እንዳሉ ይቀጥላሉ።

(7) በእዚህ አንቀጽ የሚሰጡት ጥቅማ ጥቅሞች ለአንድ ተቀጣሪ በነፍሰ ጡርነት ፈቃድ ከሚሰጡት ማንኛቸውም እና ሁሉም ጥቅማ ጥቅሞች በተጨማሪነት የሚሰጡ ናቸው።

(8) የነፍሰ ጡርነት/የወላጅነት ፈቃድ ዙርያ ለውጦች በማኒቶባ ክፍለ ሃገር *ኢምፕሎይመንት ስታንዳርድስ ኮድ* ላይ ከመጡ ካምፓኒው በአዲሶቹ ህግጋት ለመገዛት ተስማምቷል።

19.05 <u>ግላዊ ፈቃድ (ከ1- 4 ቀናት)</u>

በሚፈለግበት ቦታ ሁሉ ለተቀጣሪዎች ክፍያ የማይታሰብበት ግላዊ ፈቃድ (እስከ 4 ቀናት) ድረስ መፍቀድን ከግምት ውስጥ ለማስገባት ካምፓኒው ተስማምቷል። መጠይቁ የተቻለውን ጊዜ ያክል ቀደም ተብሎ በጽሑፍ መደረግ ይኖርበታል። ይህ አይነት መጠይቅ የሚጸድቀው የተጠየቀበትን ምክንያት፣ ጥያቄዎች በተቀጣሪ ተከታትለው የሚቀርቡበት ፍጥነት፣ እና በስራው አስፈላጊነት ላይ ተመሥርቶ ነው። ነገር ግን ያለ በቂ ምክንያት ውድቅ አይደረግም። ማንኛውም ለግላዊ ፈቃድ የሚውል ሰዓት ፈቃድ ተሰጥቶት እንደተቀረ ይቆጠራል፤ የተቀጣሪ አቴንዳንስ ቦነስ ላይም ተጽእኖ አይኖረውም።

19.06 <u>የጁሪ ዲዩቲ</u>

የፉል-ታይም ተቀጣሪዎች እና ባለፉት አራት (4) ሳምንታት በሳምንት በአማካይ ሃያ (20) ሰዓታት ሲሰሩ የነበሩ የፓርት-ታይም ተቀጣሪዎች ወደ ጁሪ ዲዩቲ/ምርጫ ሲጠሩ ስራ ቢሰሩ ኖሮ የሚያገኙት የስምንት (8) ሰዓታት ዕለታዊ ወይም አርባ (40) ሰዓታት ሳምንታዊ ክፍያ ከጁሪ ዲዩቲ/ምርጫ ከሚያገኙት ክፍያ ጋር ያለውን ልዩነት ያክል የሚከፈላቸው ይሆናል። የክፍያው መጠን የተቀጣሪውን ያለፉት አራት (4) ሳምንታት ክፍያ አማካይ በመውሰድ ይሆናል። ተቀጣሪው ለተቀረው የቀኑ ሰዓታት ከጁሪ ዲዩቲ/ምርጫ ተለቅቆ ከሆነ እና ወደ ስራ ገበታው ካልተመለሰ፣ ወይም ጁሪ ዲዩቲ/ምርጫው በተቀጣሪው የእረፍት ቀን ላይ ካረፈ ከላይ የተቀመጠው ተፈፃሚ አይሆንም።

19.07 **<u>የምስክር ክፍያዎች</u>**

ካምፓኒውን ወይም ዘውዱን ወክለው በምስክርነት ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ የሚጠበቅባቸው ተቀጣሪዎች ስራ ቢሰሩ ኖሮ የሚያገኙት የስምንት (8) ሰዓታት ዕለታዊ ወይም አርባ (40) ሰዓታት ሳምንታዊ ክፍያ ከምስክርነት ከሚያገኙት ክፍያ ጋር ያለውን ልዩነት ያክል የሚከፈላቸው ይሆናል።

በእረፍት ቀናቸው ካምፓኒውን ወክለው በምስክርነት ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ተቀጣሪዎች ቢያንስ የአራት (4) ሰዓታት ወይም ከላይ እንደተቀመጠው በእለቱ ቢሰሩ ኖሮ የሚከፈላቸውን ክፍያ ያገኛሉ። ይህ ካሳ የሚከፈለው በተቀጣሪው ቀጥተኛ ሰዓታዊ ሬት ይሆናል። እንደ የስራ ክፍያም አይቆጠርም።

19.08 **<u>የሐዘን ክፍያ</u>**

(a) ሁሉም ተቀጣሪዎች ቢበዛ ለሦስት (3) ተከታታይ የፕሮግራም የተያዘላቸው የስራ ቀናት ክፍያ የሚታሰብለት ፈቃድ ቅርብ ቤተሰብ ከሞተ የሚሰጣቸው ይሆናል። “ቅርብ ቤተሰብ” ማለት ባለቤት ወይም የኮመን ሎው ባለቤት፣ ወላጅ ወይም የእንጀራ ወላጅ፣ ልጅ ወይም የእንጀራ ልጅ፣ ወንድም ወይም እህት፣ ማዘር-ኢን-ሎው፣ ፋዘር-ኢን-ሎው፣ ሲስተር-ኢን-ሎው፣ ብራዘር-ኢን-ሎው፣ የልጅ ልጅ፣ እና አያት ማለት ነው።

(b) ቀብር ለመታደም ጉዞ ማድረግ ካስፈለገ እና የቀብሩ ቦታ ከተቀጣሪው መኖሪያ ቦታ ከአምስት መቶ (500) ኪሎ ሜትር በላይ ርቆ የሚገኝ ከሆነ የሐዘን ፈቃድ ፍቃዱ ሳይቋረጥ ክፍያ በማይታሰብላቸው እስከ ሁለት (2) በሚደርሱ የስራ ቀናት ሊራዘም ይችላል። ለሌላ ጉዳይ የሚውሉ ተጨማሪ ቀናት ፈቃድ በካምፓኒው እና በሚመለከተው ተቀጣሪ የጋራ ስምምነት ሊፈቀዱ ይችላሉ።

(c) ለሁሉም ተቀጣሪዎች የባለቤታቸው አያት፣ አክስታቸው ወይም አጎታቸው፣ የአክስት/አጎት ሴት ወይም ወንድ ልጅ በሚሞትበት ጊዜ እስከ አንድ (1) ቀን የሚደርስ ክፍያ የሚታሰብለት የእረፍት ቀን ሊሰጣቸው ይገባል።

(d) የሐዘን ፈቃድ በተቀጣሪው ቫኬሽን ላይ ቢያርፍ ያ የቫኬሽናቸው ወቅት ወደ ስራ ሲመለሱ ተቀጣሪው እና ሱፐርቫይዘሩ ተስማምተው ሊዘዋወር ይችላል።

(e) ካምፓኒው የሞት ማስረጃ ሊጠይቅ ይችላል። (ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች የሞት ሰርተፊኬት፣ የጋዜጣ ማስታወቂያ፣ መታሰቢያ ካርድ፣ ወይም ከሎካል ክለርጂ የሚመጣ ደብዳቤን ያካትታሉ።)

19.09 **<u>የቤተሰብ ኃላፊነት ፈቃድ</u>**

በተቀጣሪ ቅርብ ቤተሰብ ውስጥ ሕመም ወይም ጉዳት (በማኒቶባ *ኢምፕሎይመንት ስታንዳርድስ ኮድ* ላይ በተቀመጠው መሠረት) ቢከሰት ተቀጣሪው ከሦስት (3) ቀናት የማይበልጥ ክፍያ የማይታሰብለት ፈቃድ በካላንደር ዓመት አንዴ መጠየቅ ይችላል። ከጠየቀም ሊፈቀድለት ይገባል። ይህም ፈቃድ ተቀጣሪ የታመመውን የቤተሰብ አባል እንዲያስታምም ለማስቻል መሆን አለበት። በእነዚህ አጋጣሚዎች ካምፓኒው የተቻለውን ያክል ጊዜ ቀደም ተብሎ መነገር አለበት። በእዚህ **አንቀጽ** ስር አንድ ተቀጣሪ ማንኛውንም የቀኑን ክፍል በፈቃድ መልክ ቢወስድ ካምፓኒው ለዚህ **አንቀጽ** አተገባበር ያንን ቀን እንደ ፈቃድ የተወሰደበት ቀን ይቆጥረዋል። ማንኛውም ለቤተሰብ ኃላፊነት የሚውል ሰዓት ፈቃድ ተሰጥቶት እንደተቀረ ይቆጠራል፤ የተቀጣሪ አቴንዳንስ ቦነስ ላይም ተጽእኖ አይኖረውም።

19.10 **<u>ኮምፓሽኔት ሊቭ</u>**

በ*ማኒቶባ ኢምፕሎይመንት ስታንዳርድስ ኮድ* ኮምፓሽኔት ሊቭ ፕሮቪዥኖች መሠረት ፈቃድ ለመስጠት ካምፓኒው ተስማምቷል።

19.11 **<u>የዜግነት ጉዳይ ማስፈፀሚያ ፈቃድ</u>**

ካናዳዊ ዜግነት ለማግኘት ያመለከቱ ተቀጣሪዎች ክፍያ የማይታሰብበት የአንድ (1) ቀን ፈቃድ የዜግነት መሓላቸውን ይፈፅሙ ዘንድ ይሰጣቸዋል።

19.12 **<u>የዶመስቲክ ቫዮለንስ እና የስቶከር እረፍት</u>**

የ*ማኒቶባ ኢምፕሎይመንት ስታንዳርድስ ኮድ* ዶመስቲክ ቫዮለንስ ሊቭ ፕሮቪዥኖች ሴፕቴምበር 1፣ 2019 ላይ ባሉበት ሁኔታ መሠረት ፈቃድ ለመስጠት ካምፓኒው ተስማምቷል።

<u>አንቀጽ 20 ጤና እና ደህንነት</u>

20.01 የጤና እና ደህንነት ጥቅማ ጥቅሞች በእዚህ ስምምነት አፔንዲክስ A ውስጥ በሚገኘው መሠረት ይሆናሉ።

<u>አንቀጽ 21 ዲሲፕሊን</u>

21.01 በድርድር ዩኒት ውስጥ ያለ ተቀጣሪ የዲሲፕሊን ቃለ መጠይቅ ሲደረግበት (ካምፓኒው ተቀጣሪውን ለማረም ፣ ለምሳሌ በጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ በሰስፔንሽን፣ ወይም በዲስቻርጅ አስቦ) ተቀጣሪው የመረጠው ከዲፓርትመንቱ/ቷ የመጣ የመደብር አስተናባሪ በድርድር ዩኒቱ ውስጥ አጠገቡ ሊኖር ይገባዋል። አስተርጓሚ ካስፈለገ ሌላ የሚፈለገውን ቋንቋ ማስተርጎም የሚችል ተቀጣሪም ቃለ መጠይቁን ሊታደም ይገባል። አስተርጓሚው ከላይ ከተጠቀሱት ሰዎች በተጨማሪ ሊገባ የሚችለው

የዩኒየን አስተናባሪ የሚፈለገውን ትርጓሜ ለመስጠት የማይችል ከሆነ ብቻ ነው። እነዚህ ሰዎች (አስተርጓሚ ካስፈለገ አስተርጓሚውን ጨምሮ) ከቃለ መጠይቁ መጀመርያ አንስተው ሊታደሙ ይገባል። ሁሉም የዲሲፕሊን ስብሰባዎች የዲሲፕሊን ጉድለቱን ባመጣው ክስተት በአስራ አምስት (15) የስራ ቀናት ውስጥ መያዝ ይኖርባቸዋል። የዲሲፕሊን ስብሰባው ስለ ዲስቻርጅ (መባረር) ከሆነ ደግሞ ቀነ ገደቡ ወደ አስር (10) የስራ ቀናት ዝቅ ይላል። በእነዚህ ቀነ ገደቦች ላይ የሚደረጉ ማራዘሚያዎች በጋራ ስምምነት ብቻ የሚደረጉ ናቸው።

21.02 ተቀጣሪው የዚህ የዲሲፕሊን ፋይል ኮፒው ተሰጥቶት በግላዊ መዝገቡ ላይ የሚገባበት ይሆናል። የዲሲፕሊን ኮፒ ወደ ዩኒየኑ ቢሮም የሚላክ ይሆናል። የመደብር አስተናባሪ ወይም አባል እንደተፈለገ ካልተገኘ፣ ወይም የዲሲፕሊን ኮፒ ወደ ዩኒየኑ ቢሮ ካልተላከ፣ የሚሰጠው ዲሲፕሊን ውድቅ የሚደረግ እና በካምፓኒውም ጥቅም ላይ የማይውል ይሆናል። ተቀጣሪዎቹ ፕሮቤሽን ላይ ያሉ ተቀጣሪዎች ከሆኑ፣ ወይም የዲሲፕሊን ስብሰባ ሳይደረግ ከምርመራ በኋላ ሊሰጥ ለታቀደ ሰስፔንሽን ከሆነ ውክልና አስፈላጊ አይሆንም።

21.03 ባልተለመዱ አጋጣሚዎች ተቀጣሪን ስለመባረሩ በደብዳቤ ለማሳወቅ ሲያስፈልግ የዲሲፕሊን ኮፒ ካምፓኒው ወደ ዩኒየኑ ቢሮ ፋክስ ያደርጋል።

21.04 በ**አንቀጽ** 9 ላይ ከተቀመጠው የክፍፍል አለጣጠፍ ሂደት ውጪ በሆነ በማንኛውም መንገድ የአንድ ተቀጣሪ ደመወዝ ቢቀነስ ስለ ጉዳዩ ለመወያየት የመደብር አስተናባሪ ወይም የዩኒየን ተወካይ በማንኛውም ስብሰባ ላይ የሚገኙ ይሆናል።

21.05 **<u>የዲሲፕሊን ሬፍረንሶች መወገድ</u>**

ካምፓኒው ሁሉንም የዲሲፕሊን ሬፍረንሶች ከተቀጣሪው ግላዊ መዝገብ ላይ ከክስተታቸው ከሃያ አራት (24) ወራት በኋላ ይሰርዛል። ከዚህ ጊዜ በኋላ ካምፓኒው እነዚህን የዲሲፕሊን ጉድለቶች ተቀጣሪው ላይ በማንኛውም መልኩ ሊጠቀምባቸው አይችልም። ይህ የሃያ አራት (24) የካላንደር ወራት ጊዜ የሌይአፍ ወቅቶችን እና ክፍያ የማይታሰብላቸውን የፈቃድ (ሊቭ አፍ አብሰንስ) ወቅቶችን አያጠቃልልም።

<u>አንቀጽ 22 የቅሬታዎች አቀባበል</u>

22.01 ማንኛውም አቤቱታ፣ አለመግባባት ወይም የሃሳብ ልዩነት በካምፓኒው፣ በዩኒየኑ፣ ወይም ይህ ስምምነት በሚሸፍናቸው ተቀጣሪዎች መካከል በእዚህ ስምምነት ነጥቦች እና ፕሮቪዥኖች አተረጓጎም፣ አተገባበር፣ አሰራር፣ ወይም ጥሰት ክስ ዙርያ ሲነሳ እንደ ቅሬታ ይወሰዳል።

22.02 **<u>መረጃ</u>**

ዩኒየኑ የተቀጣሪን ክፍያ ሬት ለመወሰን የተከማቹትን የስራ ሰዓታት በተመለከተ መረጃ ሲፈልግ ካምፓኒው ተገቢው ሬት ይወሰን ዘንድ ላለፉት ሁለት (2) ዓመታት ወይም ከዚያ በላይ የተሰበሰቡትን መሰል መረጃዎችን በመስጠት ለመተባበር ተስማምቷል።

22.03 ተቀጣሪው የሰራውን ሰዓታት እና የተከፈለውን ክፍያ በሚመለከት ለሚነሳ ማንኛውም ቅሬታ ካምፓኒው ፈጥኖ ከጥያቄው በፊት የተፈፀሙትን ሁለት (2) የክፍያ ወቅቶች መረጃ ሊያቀርብ ይገባል። ከዚህ ረዘም ያለ ጊዜ መረጃ ከተጠየቀ መደበኛው የቅሬታ መስተንግዶ አሰራር ቅደም ተከተል ተግባራዊ ይደረጋል።

22.04 ዩኒየኑ ይህን አሰራር የአንድን ተቀጣሪ ቅሬታን የማይመለከት መረጃ ለመጠየቅ መጠቀሚያ ሊያደርገው አይገባም።

22.05 ማንኛውም ተቀጣሪ፣ ዩኒየኑ፣ ወይም ካምፓኒው ቅሬታ ሊያቀርብ ይችላል። ማንኛውም ቅሬታ ከመንስኤ ክስተቱ በአስራ አምስት (15) የስራ ቀናት ውስጥ (ወይም ጉዳዩ ዲስቻርጅን የሚመለከት ከሆነ ለመጨረሻ ጊዜ ከተሰራበት ቀን በአስር (10) የስራ ቀናት ውስጥ) ካልቀረበ ውድቅ ሊደረግ እና አቅራቢውም አካል ጉዳዩን ሊተወው ይገባል። የዲሲፕሊን ቅሬታን በተመለከተ፣ “መንስኤ ክስተቱ” በአንቀጽ 21.02 መሠረት ዩኒየኑ ማስታወቂያውን በፋክስ የተቀበለበት ቀን ይሆናል።

22.06 ሁሉም ቅሬታዎች በጽሑፍ ሊቀርቡ ይገባል።

22.07 የማንኛውም ተቀጣሪ ቅሬታዎች እና ጠቦች ማስተካከያ አሰጣጥ እንደሚከተለው ይሆናል፡

(1) ተቀጣሪው እና የዩኒየን ተወካዩ፣ ወይም የተቀጣሪው ቅርብ ሱፐርቫይዘር መካከል በሚደረግ ውይይት።

(a) አንድ ተቀጣሪ ቅሬታውን ወደ የዩኒየን ተወካይ ሲወስድ የቅሬታው ሂደት የመጀመሪያው እርምጃ እንደተወሰደ ይቆጠራል። ይህ የሚሆነው ግን የዩኒየኑ ተወካይ ቅሬታውን በጽሑፍ ከፋብሪካው ማናጀር ወይም የማናጀሩ ተወካይ ጋር ፋይል ካደረገ ብቻ ነው። የሰው ሃይል ማናጀሩ ወይም ተወካዩ ለቅሬታው በጽሑፍ በአምስት (5) የካላንደር ቀናት ጊዜ ውስጥ ለዩኒየኑ መልስ መስጠት ይኖርበታል። ከአምስት
(5) የካላንደር ቀናት በኋላ የዩኒየኑ ተወካይ ወደ ሁለተኛው እርምጃ መሸጋገር ይችላል።

(b) ተቀጣሪው ቅሬታ ወደ ቅርብ ሱፒሪየሩ ከወሰደ እና በአምስት (5) የካላንደር ቀናት ውስጥ አጥጋቢ መፍትሄ ላይ ካልተደረሰ፡

(2) የዩኒየኑ ተወካይ ወይም እርሱ የመረጠው ሰው ካምፓኒው የሌበር ሪሌሽን ጉዳዮችን እንዲሰራ ወደመረጠው የካምፓኒ ኦፊሺያል ጉዳዩን መውሰድ ይችላል። በእርምጃ አንድ ላይ ያለው ቅሬታ የጽሑፍ ምላሽ ዩኒየኑ በደረሰው በአስር (10) የካላንደር ቀናት ውስጥ ጉዳዩ ካልተወሰደ፣ እንደተተወ ተቆጥሮ የቅሬታ መስተንግዶ ሂደቱ ይቋረጣል።

22.08 አጥጋቢ መፍትሄ ላይ መድረስ ካልተቻለ ከሁለቱ ወገኖች አንዱ ጥያቄ በማቅረብ ከማንኛቸውም ወገን አንዱ የደረሰበትን ውሳኔ ከተቀበለበት ቀን በአስራ አራት (14) የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ (ከዚያ ሳያልፍ) ጉዳዩ ወደ በ**አንቀጽ** 23 መሠረት ወደተመረጠ ዳኛ ሊወሰድ ይችላል።

22.09 ካምፓኒው እና ዩኒየኑ ከዳኝነቱ ችሎት ቀን በሚቀድም በማንኛውም ጊዜ ሁለቱም የተስማሙበትን ሌላ አስታራቂ ቅሬታውን ለመፍታት ለሚያደርጉት ጥረት ለመጠቀም ተስማምተዋል። ይህ አስታራቂ ማንኛቸውም ወገን ያቀረቡትን መፍትሄ ሌላኛው እንዲቀበል የማስገደድ ስልጣንም ሆነ ኃይል እንደሌለው ሁለቱም ወገኖች ጠንቅቀው ይረዳሉ። ለዚህ አስታራቂ ሊወጡ የሚችሉ ሁሉም የጸደቁ ወጪዎች እና ክፍያዎች በመካከላቸው ሌላ ስምምነት እስከሌለ ድረስ በካምፓኒው እና በዩኒየኑ እኩል የሚሸፈኑ ይሆናሉ።

<u>አንቀጽ 23 የዳኛ አመራረጥ</u>

23.01 ከሁለቱ ወገኖች አንዱ ጉዳዩን ወደ ዳኝነት እንደሚወስዱት ከገለጹ በኋላ በ**አንቀጽ** 23.02 ላይ በተቀመጠው መሠረት ጉዳዩ ወደ አንድ ብቸኛ ዳኛ የሚላክ ይሆናል።

ቅሬታን ከዳኝነት ችሎት በፊት ለመፍታት ሲባል ከሁለቱ ወገኖች አንዱ ከማኒቶባ ክፍለ ሃገር ዕርቅ አገልግሎት ተቋም የቅሬታ አስታራቂ እርዳታ መጠየቅ ይችላል። በእዚህ የጋራ ስምምነት አገልግሎት ዘመን ውስጥ ሁለቱ ወገኖች ከማኒቶባ ክፍለ ሃገር ዕርቅ አገልግሎት ተቋም ከሚቀርቡ የቅሬታ አስታራቂዎች ውጪ ሌሎች አስታራቂዎችን ሊጠቀሙ ሊስማሙ ይችላሉ።

23.02 ቅሬታው ለዳኛው ከታች እንደተመለከተው በቅሬታው መንስኤ ክስተት ዕለት መሠረት ለሚከተሉት ግለሰቦች ፓናል ሪፈር ሊደረግ ይገባል፡

(1) ብሌይር ግሬሃም
(2) ሮበርት ሲምፕሰን
(3) ሮቢን ኬርሲይ
(4) ዳያን ጆንስ
(5) ጋቪን ውድ

የመጨረሻውን ዳኛ ስም ተከትሎ በመቀጠል፣ እና የፓናሉ መጨረሻ ላይ ከመጡ በኋላ በድጋሚ በፓናሉ መጀመሪያ ላይ በመቀጠል። ለመሰል አመዳደብ ሲባል ከዳኝነት ተትቶ የወጣ ጉዳይ ከዳኝነት ተትቶ እንዳልወጣ ይቆጠራል። የተመደበው ዳኛ ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም ካልቻለ የእርሱን **ወይም የእርሷን** ስም ተከትሎ የሚመጣው ግለሰብ እንደ ዳኛ ይመደባል።

23.03 ከሁለቱ ወገኖች አንዱ ጉዳዩን ለዳኝነት ሲያቀርብ ጉዳዩ ለሰስፔንሽን ወይም ተርሚኔሽን በሠላሳ (30) የስራ ቀናት ውስጥ፣ ለሌሎች ጉዳዮች ደግሞ
በዘጠና (90) ቀናት ውስጥ ሊሰማ ይገባዋል። በእዚህ ቀነ ገደብ ውስጥ ጉዳዩ ተሰሚ ሊሆን ይገባዋል።

ነገር ግን ሁለቱም ወገኖች በጋራ ከሠላሳ ወይም ዘጠና ቀናት ረዘም ለሚል ጊዜ ከተስማሙ፣ ወይም ከላይ ከተዘረዘሩት ስድስት ገላጋዮች አንዱም በሠላሳ ወይም ዘጠና ቀናት ገደቡ ውስጥ ለስብሰባ መገኘት የማይችል ከሆነ ገደቡ ሊራዘም ይችላል። ከሠላሳ ወይም ዘጠና የካላንደር ቀናት ወዲያ በጋራ መስማማት ካልቻሉ ጉዳዩ ወደተመረጠው ዳኛ ሪፈር ይደረጋል። ዳኛውም በጉዳዩ ላይ የመወሰን መብት ይኖረዋል። ምንም ቢሆን ግን ችሎቱ ከሠላሳ (30) የካላንደር ቀናት በሚበልጥ ጊዜ
ሊራዘም አይችልም። ዳኛው ውሳኔ ለመስጠት ለሰስፔንሽን ወይም ተርሚኔሽን ሠላሳ የካላንደር ቀናት፣ ለሌሎች የዳኝነት ጉዳዮች ደግሞ ዘጠና (90) ቀናት ይኖሩታል።

23.04 ዳኛው መገኖቹ የሚያቀርቡትን ክርክር እና ቁሳዊ ማስረጃዎች ሊቀበል እና ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ብሎም ያሉትን ችግሮች በደንብ ተረድቶ እስኪለይ ድረስ አስፈላጊ ያለውን ምርመራ ሊያደርግ ይገባል። ከውሳኔው ለመድረስ ዳኛው የዚህን ስምምነት ፕሮቪዥኖች መከተል እና መገዛት ይኖርበታል።

23.05 ተቀጣሪው ተርሚኔሽን፣ ዲስቻርጅ ወይም ሰስፔንሽን ገጥሞት ከሆነ ዳኛው የካምፓኒውን ውሳኔ የማስቀጠል፣ አልያም ተቀጣሪውን ከሙሉ፣ ከፊል፣ ወይም ምንም ክፍያ ጋር፣ ሲኒዮሪቲው ተቋርጦ ወይም ሳይቋረጥ፣ ወደ ቦታው የመመለስ፣ ወይም በሌላ አዋጭ ነው በሚለው መንገድ ጉዳዩን የመፍታት መብት ይኖረዋል።

23.06 የዳኛው ውሳኔ በሁሉም የሚመለከታቸው ወገኖች ዘንድ ፍጹም እና ገዢ ይሆናል።

23.07 ከላይ **አንቀጽ** 23.05 ላይ ከተቀመጠው ውጪ ዳኛው ማንኛቸውንም የዚህ ስምምነት ነጥቦች የመቀየር፣ የማስተካከል፣ ወይም የመለወጥ ስልጣን አይኖረውም። ሁሉም የሚቀርቡ ቅሬታዎች ሊገላገሉ የሚችሉ ችግሮችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል። የዚህን ስምምነት ፕሮቪዥኖች የሚቃረኑ ጉዳዮችን እና በእዚህ ስምምነት ያልተካተተ ወይም አገልግሎት ዘመኑ ውስጥ የማይነሱ ችግሮችን መሠረት ማድረግም ሆነ ማካተት አይችሉም።

23.08 በማንኛውም ቅሬታ ምክንያት የመደበኛ ስራ መቋረጥም ሆነ መስተጓጎል እንዳይኖር ይህ አንቀጽ ቅሬታዎችን የማስተናገጃ ሠላማዊ መንገድ ይሰጥ ዘንድ የሁለቱ ወገኖች እሳቤ ነው። ሁለቱ ወገኖች በእዚህ ስምምነት **አንቀጽ** 22 ፕሮቪዥኖች መሠረት በቅንነት ሊንቀሳቀሱ ይገባል።

23.09 የዳኛው ወጪዎች እና ክፍያዎች በዳኝነት ሂደቱ ተካፋይ ወገኖች እኩል የሚሸፈን ይሆናል።

አንቀጽ 24 ቡሌቲን ቦርዶች

24.01 ካምፓኒው በእዚህ ስምምነት አገልግሎት ዘመን ውስጥ ዩኒየኑ የራሱን የዩኒየን ቡሌቲን ቦርዶች (የትሬኒንግ ሴንተር ቡሌቲን ቦርዶችን ጨምሮ) ካምፓኒው እና ዩኒየኑ በተስማሙባቸው ቦታዎች በፋብሪካው ዙሪያ ይተክል ዘንድ እንደሚፈቅድ ተስማምቷል። አገልግሎቱም ተቀጣሪዎችን በቀጥታ የሚመለከቱ ማስታወቂያዎችን ለመለጠፍ ይሆናል። ከተለመደው ማስታወቂያ ውጪ የሆነ ማንኛውም ማስታወቂያ በቅድሚያ ከማኔጅመንት ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

አንቀጽ 25 የካምፓኒ እና ዩኒየን ትብብር-መደብር አስተናባሪዎች

25.01 ካምፓኒው የዩኒየኑን አንድ (1) የመደብር አስተናባሪ የመመደብ መብት እውቅና ይሰጣል። ካምፓኒው የዩኒየኑን በፈረቃ አንድ (1) ረዳት የመደብር አስተናባሪ የመመደብ መብት እውቅና ይሰጣል።

ዩኒየኑ ከሃምሳ (50) በላይ ተቀጣሪዎች ላሏቸው ዲፓርትመንቶች በፈረቃ ተጨማሪ አንድ (1) ረዳት የመደብር አስተናባሪ የመመደብ መብት ይኖረዋል። ከአንድ መቶ (100) በላይ አባላት ያለው የዘር ኮሚውኒቲ በፈረቃው ላይ የተመደበ አስተናባሪ የኮሚኒቲው አባል ከሌለው በፈረቃ ተጨማሪ አንድ (1) ረዳት የመደብር አስተናባሪ ከእዚያ የዘር ኮሚውኒቲ ውስጥ የመመደብ መብት ይኖረዋል።

25.02 የመደብር አስተናባሪዎችን ስም ዝርዝር እና ማንኛቸውንም ለውጦች ዩኒየኑ ካምፓኒውን በጽሑፍ ሊያሳውቅ ይገባል።

25.03 <u>የአስተናባሪ ማስተዋወቂያ</u>

ሱፐርቫይዘሩ፣ ኮርፖሬት አሰልጣኙ ወይም ካምፓኒው የመረጠው ተቀጣሪ አዲስ ተቀጣሪዎችን ከዲፓርትመንቱ የዩኒየን አስተናባሪ ጋር ማስተዋወቅ ይኖርባቸዋል።

25.04 አንድ ተቀጣሪ ባቀረባቸው የሕክምና ኖቶች፣ በደብሊው.ሲ.ቢ. ችግሮች፣ በፋንክሽናል ኧቢሊቲስ ኢቫሉዌሽንስ (ኤፍ.ኤ.ኢ)፣ በስራ ቦታ አከሞዴሽኖች፣ በወደ ስራ መመለስ ፕሮግራሞች ዙርያ ተቃርኖ ሲኖር ጥያቄ በማቅረብ ተቀጣሪው የዩኒየን ተወካይ ወይም የመደብር አስተናባሪ ወይም እነርሱ ከሌሉ ከዲፓርትመንቱ ተቀጣሪዎች አንዱ ተቀጣሪ በመረጠው የድርድር ዩኒት አጠገቡ ሊገኙለት ይገባል። አስተርጓሚ ካስፈለገም ሌላ የሚፈለገውን ቋንቋ ማስተርጎም የሚችል ተቀጣሪም ስብሰባውን ሊታደም ይገባል። አስተርጓሚው ከላይ ከተጠቀሱት ሰዎች በተጨማሪ ሊገባ የሚችለው የዩኒየን አስተናባሪ የሚፈለገውን ትርጓሜ ለመስጠት የማይችል ከሆነ ብቻ ነው። እነዚህ ሰዎች (አስተርጓሚ ካስፈለገ አስተርጓሚውን ጨምሮ) ከቃለ መጠይቁ መጀመርያ አንስተው ሊታደሙ ይገባል።

25.05 <u>የቅሬታ ምርመራ</u>

የዩኒየን ዋና የመደብር አስተናባሪ፣ ወይም እርሱ ከሌለ ረዳት ዋና የመደብር አስተናባሪው ማንኛውንም ቅሬታዎችን ለመመርመር ክፍያ የሚታሰብለት ፈቃድ በመደበኛ የስራ ሰዓታት ላይ ሊሰጣቸው ይገባል። ዋና የመደብር አስተናባሪው ወይም ረዳት ዋና

የመደብር አስተናባሪው ቅሬታዎችን ለመመርመር ፈቃድ ሲጠይቁ በስራ ሱፐርቫይዘራቸው እና በሰው ሃይል ተወካይ በኩል መጠየቅ አለባቸው። የስራ መስተጓጎል እንስከማያመጣ ድረስም ይህ ጥያቄ በቀረበ በአንድ (1) ሰዓት ጊዜ ውስጥ አስተናባሪው ይለቀቃል።

25.06 **<u>ኦሪየንቴሽን</u>**

ካምፓኒው የፉል-ታይም የዩኒየን ተወካዩን ወይም እርሱ የመረጠውን ሰው በቂ ሰዓት (ቢያንስ ስድሳ (60) ደቂቃዎች ለዶመስቲክ ሪክሩትመንት፣ ፎረይን ሪክሩትመንት ከሆነ ደግሞ ሁለት (2) ሰዓታት) መብታቸውን እና ግዴታቸውን ለአዲስ ተቀጣሪዎች በኦሪየንቴሽን ወቅት ለማስገንዘብ ይሰጣቸዋል።

25.07 ዋና አስተናባሪው በስራ ሰዓታት በአግባቡ መጠቀም የሚኖርበት ስልክ ከዩኒየኑ ይሰጠዋል።

<u>አንቀጽ 26 የማቃለያ ሬቶች</u>

26.01 ማንኛውም ከመደበኛ የስራ ክፍፍሉ የሚበልጥ ክፍያ ያለው ስራ ላይ በጊዜያዊነት የተመደበ ተቀጣሪ ለተመደበበት ሰዓታት ብቻ ከፍ የሚለውን የክፍያ ሬት የሚቀበል ይሆናል። ነገር ግን ከአራት ሰዓታት በላይ ከሰራ የፈረቃው ክፍያ በሙሉ ይከፈለዋል።

26.02 ማንኛውም ከመደበኛ የስራ ክፍፍሉ የሚያንስ ክፍያ ያለው ስራ ላይ በጊዜያዊነት የተመደበ ተቀጣሪ ግን ለተመደበባቸው ሰዓታት በሙሉ ከፍ የሚለው የክፍያ ሬቱ እየተከፈለው ይቀጥላል።

26.03 **<u>ሊድ ሃንድ / ኮርፖሬት አሰልጣኝ</u>**

ሊድ ሃንድ / ኮርፖሬት አሰልጣኝን ለማሳረፍ ለአንድ (1) ቀን ወይም ከዚያ በላይ የተመደቡ ተቀጣሪዎች ተገቢውን ፕሪሚየም ከመደበኛ ሰዓታዊ የክፍያ ሬታቸው በተጨማሪ ያገኛሉ።

<u>አንቀጽ 27 የክፍያ ጊዜ -- ዳይሬክት ዲፖዚት</u>

27.01 በድርድሩ ዩኒት ለሚሸፈኑ ተቀጣሪዎች በሙሉ ሳምንታዊ የክፍያ ጊዜ ለመስጠት ካምፓኒው ተስማምቷል። ካምፓኒው ተቀጣሪው በመረጠበት የገንዘብ ተቋም ለተቀጣሪው አካውንት በዳይሬክት ዲፖዚት ሊከፍል ይገባል። **ከፔይሮል ዲፖዚቱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ** ካምፓኒው የተቀጣሪዎችን የሳምንቱን ክፍያ ዝርዝር ትንተና ሊሰጥ ይገባል። **ትንተናው ሁሉንም ተከፋዮች እና ተቆራጮች ፕሪሚየም ክፍያዎችን፣ ኦቨርታይምን እና የተገኘን ቫኬሽን አካትቶ በግልጽ የሚዘረዝር ይሆናል።**

27.02 **<u>የፔይሮል ስህተቶች</u>**

እነዚህ ፔይ ስተቦች ለሁሉም ተቀጣሪዎች በድርድር ዩኒቱ **በኤሌክትሮኒክስ** በየሳምንቱ ከ**ረቡዕ** እኩለ ሌሊት ሳያልፉ ይሰጣሉ። ከአራት (4) የስራ ሰዓታት እና ከዚያ በላይ የሚሆን የክፍያ ስህተት ካምፓኒው ከሰራ ጥያቄ ተቀርቦ ስህተቱ ለሱፐርቫይዘር ሪፖርት በተደረገ በሦስት (3) የስራ ቀናት ውስጥ ወደ ተቀጣሪው አካውንት ካምፓኒው የተስተካከለውን መጠን ዲፖዚት የሚያደርግ ይሆናል። ካምፓኒው ከላይ ከተቀመጠው ገደብ የሚበልጥ መጠንም ሆነ የጊዜ ርዝማኔ ያላቸውን ማንኛቸውንም የፔይሮል ስህተቶች የሚጠቁም ወርሃዊ ሪፖርት ያዘጋጃል። ይህም በጆይንት ሌበር ሪሌሽን (ጄ.ኤል.አር.) ኮሚቴው የሚታይ ነው።

አንቀጽ 28 **ማኒቶባ ምግብ እና ንግድ ሰራተኞች፣ ሎካል ቁጥር 832 ትምህርት እና ስልጠና ትረስት ፈንድ**

28.01 የማኒቶባ ምግብ እና ንግድ ሰራተኞች፣ ሎካል ቁጥር 832 ትምህርት እና ስልጠና ትረስት ፈንድ በእዚህ ስምምነት አፔንዲክስ C ላይ በተቀመጠው መሠረት ይሆናል።

<u>አንቀጽ 29</u> **<u>ሎከሮች</u>**

29.01 ካምፓኒው ለሁሉም ተቀጣሪዎች የየራሳቸውን ሎከር ለመስጠት ተስማምቷል። ተለቅ የሚሉት ሎከሮች ክፍት ሲሆኑ ቅድሚያ በሳኒቴሽን ዲፓርትመንት፣ ሺፒንግ ዲፓርትመንት፣ ፍሪዘር ዲፓርትመንት፣ ጥገና ዲፓርትመንት ውስጥ ለሚሰሩት ተቀጣሪዎች እና የመደብር አስተናባሪዎች እና የጤና እና ደህንነት ካፒቴኖች ይሰጣል። የቦታ እና/ወይም ዞኒንግ ደንቦች ካምፓኒውን አኮሞዴት እንዲያደርግ ከማስቻል ሲያግዱ ካምፓኒው ዩኒየኑ ጋር በመመካከር እና አብሮ በመስራት ተገቢ እና ምክንያታዊ አማራጮችን ያመቻቻል።

29.02 መሰል ሎከሮች የሚገቡት በሚከተሉት ሁለት ሁኔታዎች ብቻ እንደሆነ ሁለቱም ወገኖች ይገነዘባሉ፡

(1) (a) ተቀጣሪ በተገኘበት፤ ወይም

(b) ተቀጣሪው ጠይቆ፣ የመደብር አስተናባሪ በተገኘበት፤ ወይም

(c) ቀጥተኛ አክሰስ ለሎከር ጽዳት፣ ቬሪፊኬሽን ኦዲት ወይም ኮንዲሽን ኢንስፔክሽን፣ አምስት የስራ ቀናት አስቀድሞ ዩኒየኑን እና ተቀጣሪዎችን በፋብሪካ ማስታወቂያ ለጥፎ በማሳወቅ፣ የመደብር አስተናባሪ ወይም የዩኒየን ተወካይ በተገኘበት፤ ወይም

(d) አፍሳይት ዲስቻርጅ (ለምሳሌ ያለፈቃድ በመቅረት፣ በመልቀቅ) የመደብር አስተናባሪ በተገኘበት

(2) የፖሊስ መኮንን በተገኘበት።

አንቀጽ 30 አፔንዲክሶች

30.01 ከዚህ የጋራ ድርድር ስምምነት ጋር የተያያዙት ሁሉም አፔንዲክሶች በሁለቱ ወገኖች መካከል ያለው የጋራ ድርድር ስምምነት አካል ተደርገው ይቆጠራሉ።

አንቀጽ 31 መከባበር የሰፈነበት የስራ ቦታ

31.01 ካምፓኒው እና ዩኒየኑ ፋብሪካው ከጥቃት፣ **መድልዎ እና ቡሊዪንግ** የጸዳ ሊሆን እንደሚገባ ተስማምተዋል። ካምፓኒው እና ዩኒየኑ **በተጨማሪም** እርስ በእርስ በመተባበር ጥቃትን፣ **መድልዎን እና ቡሊዪንግን** ከስራ ቦታ ለመከላከል እና ለማጥፋት ተስማምተዋል። **በተቻለ መጠን ዩኒየኑ የዩኒየን አባላትን ስለሚመለከት ስለማንኛውም ፎርማል ምርመራ ይነገረዋል። ሁለቱም ወገኖችም ይህን መረጃ አሳልፈው እንዲሰጡ በህግ ካልተጠየቁ በስተቀር በሚስጥር ይይዛሉ።**

መከባበር የሰፈነበት የስራ ቦታ ፖሊሲው በስራ ቦታ የሚለጠፍ እና ዝርዝር ነጥቦቹም በየዓመቱ በጤና እና ደህንነት ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ የሚገመገም ይሆናል።

31.02 ካምፓኒው የስኬቱ ቁልፍ አካል የሆኑት ተቀጣሪዎቹ በአጋጣሚዎቹ የሚገባቸው ክብር እና ፍትሓዊነት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ተስማምቷል።

ሁለቱ ወገኖች እንደ ጥቃት እና ክብር የጎደለው አያያዝ የመሰሉ የማይገባ ባህርያት ውንጀላዎች በ**አንቀጽ** 22 ስር ቅሬታ ሊቀርብባቸው እንደሚችል ተስማምተዋል። የቅሬታ አሰራሩን ተከትለው ችግሩን መፍታት ካልቻሉ ጉዳዩ በ**አንቀጽ** 23 መሰረት ወደ ዳኝነት ሊወሰድ ይችላል። ዳኛው የዚህ **አንቀጽ** ጥሰት መፈፀሙን ከደረሰበት **ሁለቱም ወገኖች በሌላ ነገር ካልተስማሙ በስተቀር** የጠብ አፈታት ሂደቱን ተከትሎ ጠቡን ይፈታል።

1) ጉዳዩ በቀጥተኛ እርቅ ፍቺ ካላገኘ አስታራቂው በጉዳዩ ላይ ያለውን አስተያየት በሪፖርት አስፍሮ የመፍትሄ ሃሳቦችን ይሰነዝራል።

2) በእዚህ ሂደት ያልተገባ ድርጊት እንዳደረጉ የተደረሰባቸው ግለሰቦች እንደካምፓኒው ፈቃድ እና ውሳኔ ይያዛሉ ወይም በአግባቡ ዲሲፕሊን ይደረጋሉ። መሰል እርምጃዎች ለዩኒየኑ ፕሬዝዳንት በሚስጥር ይጋራሉ።

31.03 ካምፓኒው እና ዩኒየኑ እያንዳንዳቸው ሁሉም ማኔጅመንት እና ማኔጅመንት ያልሆኑ ተቀጣሪዎች በስራ ቦታ ግንኙነታቸው ላይ አግባብ በሆነው በክብር እና በፍትሓዊነት ሊያዙ እና እርስ በእርሳቸውም እንዲሁ ሊያያዙ እንደሚገባቸው ያላቸውን የረጅም ዘመን እና ቀጣይነት ያለው ቆራጥነት ያረጋግጣሉ። ከላይ የተቀመጠው በምንም መልኩ ከሌሎች የጋራ ስምምነቱ ፕሮቪዥኖች ጋር ሊቃረን ወይም ተጽዕኖ ሊፈጥር አይችልም።

<u>አንቀጽ 32</u> **<u>ጆይንት ሌበር ማኔጅመንት ኮሚቴ</u>**

32.01 ካምፓኒው እና ዩኒየኑ የጋራ ችግሮቻቸውን የሚከታተል የጆይንት ሌበር ማኔጅመንት ኮሚቴ (ጄ.ኤል.ኤም) ለማቋቋም ተስማምተዋል። ስብሰባዎቹ በ**የዓመቱ** የሚደረጉ ይሆናል።

32.02 ኮሚቴው የካምፓኒውን ተወካዮች ማለትም የፋብሪካው ሲኒየር ኦፕሬቲንግ ማናጀሩን፣ ሲኒየር የሰው ሃብት (ኤች.አር) ማናጀሩን፣ የፉል-ታይም የዩኒየን ተወካዩን፣ ዋና አስተናባሪውን፣ እና ረዳት ዋና አስተናባሪዎቹን ጭምር ያካትታል።

32.03 በጋራ ስምምነት ሁለቱ ወገኖች ከላይ ከተጠቀሱት ሌሎች ስብሰባዎችን ሊያደርጉ ይችላሉ። የሌበር ሪሌሽኑ ምክትል ፕሬዝዳንት እና የዩኒየኑ ፕሬዝዳንት በዓመት አንድ ስብሰባ ለመታደም ጥረት ያደርጋሉ።

32.04 በጄ.ኤል.ኤም ስብሰባዎች ላይ የሚነሱትን ችግሮች ለመመልከት እና ለመቅረፍ ሁለቱ ወገኖች የተቻላቸውን ጥረት ያደርጋሉ።

32.05 ካምፓኒው እና ዩኒየኑ የጆይንት ሌበር ሪሌሽን (ጄ.ኤል.አር) ኮሚቴ ለማቋቋም ተስማምተዋል። ይህ ኮሚቴ የዩኒየን ተወካዩን፣ ዋና አስተናባሪውን፣ ረዳት ዋና አስተናባሪዎቹን፣ እና የሚመለከታቸውን የካምፓኒ ተወካዮች ይይዛል። የጄ.ኤል.አር ኮሚቴው የሌበር ሪሌሽኖችን የሚመለከቱ ችግሮችን በፍጥነት መፍታትን አላማ አድርጎ በወር አንዴ ስብሰባ ያደርጋል።

<u>አንቀጽ 33</u> **<u>የውጭ ሃገር ሰራተኛ ፕሮግራም</u>**

33.01 **<u>የኢሚግሬሽን ፔፐርወርክ</u>**

የኢሚግሬሽን ፔፐርወርካቸውን ያጠናቅቁ ዘንድ (ሁሉንም የሚመለከታቸውን የስራ ፈቃድ እድሳት ማመልከቻዎች እና ለቋሚ ነዋሪነት የሚያስፈልጉ ቅጾችን አካትቶ) የሚረዳ አድሚኒስትሬቲቭ ድጋፍ ለውጭ ሃገር ሰራተኞች ለመስጠት ካምፓኒው ተስማምቷል።

33.02 **<u>ትርጉም</u>**

ከአንድ መቶ (100) በላይ ለሚሆኑ ሰራተኞች የመጀመሪያ ቋንቋ ወደሆኑት ማንኛቸውም ቋንቋዎች ሙሉ ወጪውን ሸፍኖ የጋራ ድርድር ስምምነቱን ለማስተርጎም ካምፓኒው ተስማምቷል። በተጨማሪም ከአንድ መቶ (100) በላይ ለሚሆኑ ሰራተኞች የመጀመሪያ ቋንቋ ወደሆኑት ማንኛቸውም ቋንቋዎች የተቀጣሪዎች ሃንድቡክን ለማስተርጎም ካምፓኒው ተስማምቷል። ሌሎች መተርጎም አለባቸው የሚሏቸው ዶክመንቶች ካሉ ሁለቱ ወገኖች ወጪውን 50/50 ይጋራሉ።

33.03 ለውጭ ሃገር ሰራተኞች በሚያስፈልግበት ጊዜ ሁሉ ተርጓሚዎችን ለማቅረብ ካምፓኒው ተስማምቷል።

33.04 **<u>የውጭ ሃገር ሰራተኛ መባረር</u>**

ፕሮቤሽን ላይ ያልሆነ የውጭ ሃገር ሰራተኛ ቢባረር በተባረረ በስድስት (6) ወራት ጊዜ ውስጥ የተፋጠነ የዳኝነት ችሎት ለመያዝ ሁለቱ ወገኖች ተስማምተዋል። ዳኛው ውሳኔ እስኪሰጥም ድረስ ተቀጣሪው በብራንደን ይቆይ ዘንድ የሚያስፈልጉትን ሁሉንም ፔፐርወርክ ካምፓኒው ፕሮሰስ እያደረገ ይቀጥላል።

33.05 ይህ ስምምነት በጸደቀ በስድሳ (60) ቀናት ጊዜ ውስጥ ሁለቱ ወገኖች በፋብሪካው ውስጥ ለቃል ትርጉም የሚጠቅሙ አስተርጓሚዎች ስም ዝርዝርን ፈርመው ያጸድቃሉ።

33.06 **<u>የፌደራል ኢሚግሬሽን ሕግጋት</u>**

በእዚህ የተካተቱት የውጭ ሃገር ሰራተኞችን የሚመለከቱ ፕሮቪዥኖች በሙሉ የፌደራል ኢሚግሬሽን ሕግጋትን መሠረት አድርገው ሊሆኑ እንደሚገባ ሁለቱ ወገኖች ተስማምተዋል። በእነዚህ ፕሮቪዥኖች እና በፌደራል ኢሚግሬሽን ሕግጋት መካከል ተቃርኖ ቢኖር ሁለቱ ወገኖች ተሰብስበው የዚህ **አንቀጽ** ፕሮቪዥኖች ሕግን የሚከተሉ እንዲሆኑ አድርገው ማስተካከያ ያደርጋሉ።

<u>አንቀጽ 34</u> **<u>ኤክስፓይሬሽን እና ሪኒዋል</u>**

34.01 ይህ ስምምነት በዩኒየኑ ከጸደቀበት ቀን አንስቶ እስከ **ዲሴምበር 31፣ 2024** ድረስ ስራ ላይ ይውላል። ከዚያም ከሁለቱ ወገኖች ከአንዱ ከአገልግሎት ማብቂያ ቀኑ ወይም ከአኒቨርሰሪው ከሠላሳ (30) ቀናት ሳያንስ እና ከዘጠና (90) ቀናት ሳይበልጥ ቀደም ተብሎ ጥያቄ ከቀረበ እድሳት ይደረግለታል። በየአመቱ በአኒቨርሰሪው ወቅትም ከሁለቱ ወገኖች አንዱ ለሌላኛው በጽሑፍ ማመልከቻ አስገብቶ ስምምነቱ እንዲያበቃ ወይም እንዲከለስ ሊያሳውቅ ይችላል። ይህ ስምምነት በሚያበቃበት ቀን ከላይ እንደተጠቀሰው ድርድሮች ካልተጠናቀቁ ካምፓኒው እና ዩኒየኑ በተስማሙበት መሰረት ይህ ስምምነት አውቶማቲካሊ የሚራዘመው እስከ፡

(1) ሁለቱ ወገኖች በመካከላቸው ስምምነት እስኪደረስ፤

(2) በዩኒየኑ ለካምፓኒው ስራይክ የማወጅ ፍላጎቱን ሰባት (7) ካላንደር ቀናት አስቀድሞ በማሳወቅ ስትራይክ ሲታወጅ፣ ወይም

(3) በዩኒየኑ ለካምፓኒው ሎክአውት የማወጅ ፍላጎቱን ሰባት (7) ካላንደር ቀናት አስቀድሞ በማሳወቅ ሎክአውት ሲታወጅ።

34.02 ማንኛቸውም ወገን የሚፈልጋቸው ሁሉም የዚህ ስምምነት ክለሳዎች በጽሑፍ ማስታወቂያው በተሰጠበት በአስር (10) ቀናት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ይኖርባቸዋል።

34.03 የሚፈለገው የማቋረጫ ወይም የመከለሻ ማሳወቂያ ከሁለቱ ወገኖች ከማንኛቸውም ሲቀርብ፣ ከዚህ ጋር የሚያያዙ ድርድሮች በአፋጣኝ ተጀምረው በፍጥነት ይከናወናሉ። ይህም የሚቻል ከሆነ በማሳወቂያ ጊዜው ውስጥ በአጥጋቢ ሁለቱንም ወገኖች በሚያረካ ሁኔታ ይፈፀም ዘንድ ነው።

ለስምምነታቸውም ማሳያ እንዲሁን የሚከተሉት አካላት ይህን ስምምነት ፈርመው አጽድቀዋል።

ተፈረመ በእዚህ በ_____ኛው የ_____፣2020 ቀን።

ለዩኒየኑ፡

_____
ጽጌረዳ አለሙ

_____
ኤልሳ አልቫራዶ

_____
ሆሊ ጋወር

_____
ካትሪን ሀይስ

_____
ዊሊያም ኬልሶ

_____
ኪም ኖክስ ፓወርስ

_____
ማርቪን ላንዳቬርዴ

_____
ሜይ ሊ

_____
ሳም ማቲዮውስኪ

_____
አን ምክሌላን

_____
ሳንሚት ፓቴል

_____
ጄራርድ ኬዌዛንቼ

ለካምፓኒው፡

_____
ኬን ዛሬትዝኪ

_____
ሙኔሽ ሻርማ

_____
ብሪትኒ ሃልክሮው

_____
ኒኮሊን ዴይ

_____
ጄይ ባሹኪ

_____
ዴዚ ሲንግ

ዲን ሮድዌል

ጉርዲፕ ሲንግ ማን

ግሌን ስኪፐር

ሙሉቀን ተሾመ

ዳኒዬል ዬንስ

ብሬንዳ ብራውን

ሜሪ ቡቻን

ጀፍ ትሬገር

አፔንዲክስ A

ጤና እና ደህንነት የጥርስ ህክምና
ፕላን / ጡረታ ፕላን

A-1 ዩ.ኤፍ.ሲ.ደብሊው/ሜፕል ሊፍ ፉድስ ኮርፖሬሽን **የቤኔፊት ትረስት ፈንድ**

(a) ካምፓኒው እና ዩኒየኑ በቦርድ ኦፍ ትረስቲስ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚወሰነው መሠረት የጤና እና ደህንነት ጥቅማ ጥቅም ለማቅረብ በዩ.ኤፍ.ሲ.ደብሊው/ሜፕል ሊፍ ፉድስ ኮርፖሬሽን ቤኔፊት ትረስት ፕላን ተስማምተዋል።

